# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ድንግል ማርያም፡ ይህን፡ ራሷ፡ በቀጥታ፡ የሰጠቻቸውን ትእዛዝ፡ ወዲያው የፈጸሙት፡ እነርሱ፡ አገልጋዮቹ ብቻ አይደሉም፡ አምላክ የኾነው ልጇም፡ ያለአንዳች ተከታይ፡ ወይም፡ ተጨማሪ ጥያቄ፡ በፍጹም ታዛዥነት፡ ለፍጻሜ አበቃው እንጂ::

በዚህ፡ በእናቱ ትእዛዝ መሠረት፡አገልጋዮቹ፡ ወደእርሱ፡ ወደልጇ ቀርበው፡ "እናትህ፡ 'ልጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!' ብላ፡ ወደአንተ ላከችን፡ ምን እንድናደርግ ትወድዳለህ? እዘዘን!" ብለው፡ በፊቱ በቆሙ ጊዜ፡ ወደእናቱ ኼዶ፡ "ምነው እናቴ? ያልኩሽን አልተረዳሽልኝምን? ምነው እንዲህ አጋለጥሽኝ? 'አይኾንም!' ብዬሽ አልነበረምን?" አላለም:: የልቧን አሳብና ፍላጎት ስላወቀው፡ ከእርሷ፡ ተጨማሪ ምላሽ፡ ወይም ማብራሪያ ሳይጠይቅ፡ የእናቱን ትእዛዝ፡ ያለአንዳች ማመንታት ፈጸመ::

፯ኛ፡ የሰውን ዘርና ዓለሙን ኹሉ ሊያድን፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ የግብዣውን ጥሪ ተቀብሎና ራሱ ተገኝቶ እየተጋበዘበት ባለው፡ በዘመዶቹ ሠርግ ላይ፡ ይህን የመሰለ ችግር መድረሱን ሲያውቅ፡ ቀድሞውንስ ቢኾን፡ እንዴት ዝም አለ? ከዚህም በላይ፡ እናቱ፡ የሚቻለው መኾኑን እያወቀች፡ ለተቸገሩት ዘመዶቻቸው፡ ያን፡ እጅግ አስፈላጊና አስቸኳይ የኾነ እርዳታ እንዲያደርግላቸው ስትጠይቀው፡ ያን የመሰለ፡ ርኅራኄና ኀዘኔታ የጎደለው ያስመሰለውን፡ ከባድ የአሉታ ምላሽስ እንዴት ሊሰጣት ወድዶ መረጠ? ይህ የጌታ ኹኔታ፡ ለማያምን ቀርቶ፡ ለሚያምን ደካማም ቢኾን፡ ግራ የሚያጋባ ነገር ኾኖ ይታያል::

ነገር ግን፡ ለምን፡ እንዲህ ያለው ነገር እንዲደርስ ፈቃዱ እንደኾነ ለመረዳት፡ ቀደም ብሎ ወደተጠቀሰው፡ ወደመለኮታዊው ዕቅድና ዓላማ መለስ ብሎ ማስተዋልን ይጠይቃል:: ዕቅዱና ዓላማው እኮ፡ የእናቱን፡ ማንነትና ክብር ለመግለጥ ስለኾነ፡'መድረኩን፡ ለእርሱ ማንነትና ክብር መገለጫ, ሳይኾን፡ በሙሉ፡ ለእርሷ ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን መልቀቁን፡ በማስተዋል መመልከት ነው::

የቅድስት ድንግል ማርያም ክብርዋ፡ አማላጅነቷ ነው፤ ይኸውም፡ "የእናት ምልጃ፡ ፊት አያስመልስ! አንገት አያስቀልስ!" እንደሚባለው፡ ይህን የመሰለው መለኮታዊ ቸርነት፡ ይደረግላቸው ዘንድ፡ ሰዎች፡ በፍጹም ሃይማኖት ኾነው፡ በስሟ፡ ወደእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ልመና፡ በቋሚ ምልጃዋ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን ማስገኘቱ ነው::

የሰው ልጆች፡ ራሳቸውን፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት ካበቁ፡ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ጣልቃ ገብተው፡ የመለኮትን ምሕረት ለማስገኘት የሚቻሉበትን የአማላጅነት ሥልጣንን ሊሰጣቸው፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ እንደኾነ፡ በዚህ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቅድስት እናቱ፡ በድንግል ማርያም አሳሳቢነት በፈጸመው፡ በአዲሱ ኪዳን መለኮታዊ ድርጊቱ አረጋግጦ አሳይቷል:: ያሳየውም፡ ይህ የመለኮት ቸርነት፡ እየራሳቸውን፡ በሃይማኖትና በምግባር፡ ለዚህ ጸጋ ላበቁ ለሰው ልጆች ኹሉ ጭምር መኾኑን፡ እስካኹን፡ እናንተም አውቃችሁታል፤ ወደፊትም፡ በበለጠ ታውቁታላችሁ::

## ምዕራፍ ፮፤ በዓል:: ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

### ቃና ዘገሊላ:- የድንግል ማርያም: እመ አምላክነትና አማላጅነት: በይፋ የታወቀበት ሠርግ::

---

እንግዲህ: ለሰብአዊቷ እናት: ከመለኮት ልጇ የተሰጣት ሥልጣንና ክብር: ይህ ነው:: ታዲያ! ፈጣሪ: በሰብአዊ አእምሮ: ሊታሰብና በሰብአዊ አንደበት: ሊገለጽ፥ በሰብአዊ ዓቅምም ሊተገበር በማይቻል ቸርነቱና ጥበቡ ያደረገውን ይህን የፍጹም ለጋሥነቱን ሥራ፥ ከዚህ የተነሣም: ራሱ ሰው: በእርሷ ምክንያት ያገኘውን: የመጨረሻውን ታላቅ ሥልጣንና ክብር እያደነቁ በማመስገን ፈንታ: ሰዎች: በምድር ላይ: እርስ በርሳቸው የሚያካኺዱትን ምቀኝነት: ሳያፍሩ: በጸጋ ሰጪው መለኮት ልጇና በጸጋ ተቀባይዋ እናት ላይ ጭምር ሊያሳዩና ሊፈጽሙ ይገባልን? የለም፡ አይገባም::

ጥያቄ:- *የ"ቃና ዘገሊላ" እና የቅዱስ ሚካኤል በዓላት: በጥር ፲፪ ቀን: አብረው እንዲከበሩ የተደረገው ለምንድነው?*

መልስ:- የዚህ ምክንያቶች: የሚከተሉት ናቸው:-

፩ኛ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ከጥምቀቱ በኋላ: አምላክነቱ: ለመጀመሪያ ጊዜ: በይፋ የተገለጠው: በቃና ዘገሊላ ስለነበረ: ከጥምቀት በዓል ጋር ተያይዞና ቀጥሎ ሊከበር የሚገባና የሚያስፈልግ በመኾኑ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ: ቅድስት ድንግል ማርያም በተገኙበት: ቅዱስ ሚካኤልም: በዚያ: በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ እንዳልተለየ ስለሚታመን: የቃና ዘገሊላን በዓል: ከዚሁ ሊቀ መላእክት በዓል ጋር አብሮ እንዲከበር ማድረጉ: በእርግጥ: ተስማሚ: ተገቢና አመቺ ይኾናል::

፪ኛ: በጥር ፲፪ ቀን: የሚከበረው: የቅዱስ ሚካኤል በዓል: የይስሐቅና የርብቃ ልጅ የኾነው ያዕቆብ: የመንትያ ታላቁን: የዔሳውን ብኵርና: ከቡራኬ ጋር: ከአባታቸው ከይስሐቅ በማታለል ስለወሰደበት: ወንድሙ ሊበቀለው መፈለጉን ተረድቶ: ወደእናቱ ወንድም: ወደአጎቱ: ወደላባ አገር ኰብልሎ በኼደ ጊዜና እዚያ: በኖረበት ዘመን: ኋላም: ከሚስቶቹና ከልጆቹ፥ ከብዙ ከብትም ጋር ወደወላጆቹ አገር ተመልሶ: ከወላጆቹ ቦታ እስከደረሰበት ቀን ድረስ: ከእግዚአብሔር ታዝዞ: ሳይለየው የጠበቀውን ቅዱስ ሚካኤልን እናዘክርበታለን::

፫ኛ: የእሥራኤል ልጆች: በዘመነ አሪት: ለአርባ ዓመታት: በምድረ በዳ በሚፈተኑበት ጊዜ: የብሉይ ኪዳኗ ታቦተ ጽዮን: በመካከላቸው ሣለች: ዓቃቤ መልአክ ኾኖ: እርሷን ያገለግልና ሕዝቡን ይጠብቅ የነበረው: ይኸው ሊቀ መላእክት እንደነበረ ኹሉ: ዛሬም: ለጥምቀት በዓል: ከቤተ መቅደሱ: ወደባሕረ ጥምቀቱ ወርዶ፥ በዚያም ኹለት ሌሊት አድሮ: እንደሌሎቹ ታቦታት: በጥር ፲፩ ቀን ሳይኾን: በዓሉ በሚውልበት: በጥር ፲፪ ቀን: ወደመንበረ መቅደሱ ከሚመለሰው: ከአዲስ ኪዳኑ ታቦት ሳይለይ የሚያገለግለውን: የዚህኑ: የቅዱስ ሚካኤልን ተልእኮ እናስታውስበታለን::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

### የቅዱሳን አማላጅነት ተረጋግጦ የተመሰከረበት ኹኔታ።

ጥያቄ፡- *ከዚህ ቀደም ብለህ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለቅድስት ድንግል እናቱ ያደረገው መለኮታዊ ቸርነቱ፡ ለእርሷ ብቻ ሳይኾን፡ "እየራሳቸውን፡ በሃይማኖትና በምግባር፡ ለዚህ ጸጋ ላበቁ ለሰው ልጆች ኹሉ ጭምር መኾኑን፡ እስካኹን፡ እናንተም አውቃችሁታል፤ ወደፊትም፡ በበለጠ ታውቁታላችሁ።" ብለህ ስለሰጠኸን መግለጫ፡ ብታብራራልን?*

መልስ፡- እግዚአብሔር፡ ስለቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ፡ በገሃድ ያሳየውን የመሰለ፡ መለኮታዊ የቸርነት ድርጊቱን፡ በብሉዩ ኪዳንና በአዲሱ ኪዳን ዘመናትም መፈጸሙ ታይቷል፤ ከእነዚህም መካከል፡ አንዳንዶቹን፡ እንደሚከተለው፡ በምሳሌነት መጥቀሱ፡ አግባብና በቂ ይኾናል፡-

፩ኛ. የብሉዩን ኪዳን በሚመለከት፡ በኢትዮጵያ ኖሮ፥ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና በእርሷ ብቻ ተወስኖ፡ ከእርሷ ልጆችን ከወለደ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ፡ ወደግብፅ ልኮት፡ የእሥራኤልን ልጆች፡ ከባርነት ነጻ ባወጣቸው፡ በሙሴ ላይ ስለደረሰው ገድል የሚያስታውሰው ዜና መዋዕል ይገኛል።

አዎን! እሥራኤል፡ የቀይ ባሕርን፡ በአምላካቸው ተአምራዊ ኃይል ከተሻገሩ በኋላ፡ ሙሴ፡ ስለሚቀጥለው አካኼዳቸው፡ መለኮታዊዉን መመሪያ፡ ከፈጣሪው ለመቀበል፡ ወደደብረ ሲና ወጥቶ፡ በሱባዔ፡ ለአርባ ቀናት ቢዘገይባቸው፡ ወንድሙን አሮንን፡ "እንደአሕዛብ፡ በፊታችን የሚኼድ ጣዖት ካልሠራህልን!" ብለው አስጨንቀው፡ ላቆሙት የጥጃ ምስል መስገዳቸውና መሠዋታቸው ይታወሳል፤ እግዚአብሔርም፡ ይህን ግብራቸውን አውቆ፡ *"ይህ ሕዝብ፡ አንገተ ደንዳና ነው፤ አሁንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸውና እንዳጠፋቸው ተወኝ! አንተንም፡ ለታላቅ ሕዝብ መሪ አደርግሃለሁ!"* ባለው ጊዜ፡ ሙሴ፡ ስለሕዝቡ፡ በአምላኩ ፊት ጸልዮ እንዳማለደ፥ *"እግዚአብሔርም፡ በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፉ ነገር ራራ።"* በሚለው የአሪቱ ቃል መሠረት፡ ለሕዝቡ ምሕረትን እንዳስገኘ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ተረጋግጧል።[፻፺፪]

፪ኛ. የአዲሱን ኪዳን በሚመለከት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እናንተን የሚቀበል፡ እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል፡ የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን፡ በነቢይ ስም የሚቀበል፡ የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፤ ጻድቅንም፡ በጻድቅ ስም የሚቀበል፡ የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም፡ ከእነዚህ ከታናናሾቹ፡ ለአንዱ፡ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ፡ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፡ እውነት እላችኋለሁ፡ ዋጋው አይጠፋበትም።"* ሲል የተናገረው ቃል፡ እግዚአብሔር፡ ለበቁት የሰው ልጆች፡ በሕይወተ ሥጋም ሣሉ፥ በሕይወተ ነፍስም እያሉ ለሰጣቸው የማማለድ ጸጋ በቂ ማስረጃ ነው።[፻፺፫]

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

---

## አስተርእዮ ማርያም:

"አስተርእዮ ማርያም": ጥር ፳፩ ቀን የሚውለው: የቅድስት ድንግል ማርያም: የዕረፍተ ሥጋዋ መታሰቢያ በዓል ነው:: በዓሉ: እግዚአብሔር ወልድ: በሰውነት ተወልዶና ማንነቱ በይፋ ታውቆ በተገለጠበት: ከጥምቀቱ ጀምሮ ባለው ወራት ውስጥ ስለሚከበር: የ"አስተርእዮ ማርያም" ተብሏል::

የድንግል ማርያም: የዕረፍቷ÷ የትንሣኤዋና የዕርገቷ ዜና::

ጥያቄ:- *በጽንሰቷ የጀመርህልንን: የቅድስት ድንግል ማርያምን ዜና መዋዕል: እዚህ ላይ ቀጥለህልን: እስከመጨረሻውም አድርሰህልን: ስለእርሷ ያለንን እውቀት የተሟላ ብታደርግልን?*

መልስ:- እኛ ኢትዮጵያውያን: ቀድሞ: በሥነ ፍጥረት÷ ኋላም: በኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ: ብዛታቸው ሊቆጠር የማይቻል: መልካካም ነገሮችን ላበረከተልን ፈጣሪያችን: ለእግዚአብሔር እንደምናደርገው ኹሉ÷ "እናታችንና ንግሥታችን፥ ሃይማኖታችንና አገራችን" ስለኾነችው: ስለቅድስት ድንግል ማርያምም: በየሕሊናችን የምናስበው÷ በአንደበታችን የምንናገረውና በየሕዋሳታችን የምንፈጽመውም ኹሉ: በየሕይወታችን ውስጥ: አብሮን ሕያው ኾኖ ለዘወትር ባለማቋረጥ የሚካኼድ እንጂ: በአንድ ቀን ብቻ የተወሰነ አይደለም::

አኹንም: እዚህ ላይ አቅርቤ የማሰማችሁ ዜና መዋዕሏ: በተለይ: በአዲስ ኪዳኑ መጽሓፍ ውስጥ ተመዝግቦ የሚነበበውን÷ ልጇ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስካረገበትና መንፈስ ቅዱስ: በሓዋርያት ላይ እስከወረደበት ቀን ድረስ ያለውን ሳይኾን: ከዚያ በኋላ: በዚያው መልክና ይዘት የቀጠለው ምድራዊ ሕይወቷ: በ፷፬ ዓመታት ዕድሜዋ ካበቃበት የዕረፍቷ ቀን ተነሥቶ: የመጨረሻ የኾነውን ዜናዋን ብቻ ይኾናል፤ እርሱም: የዕረፍተ ሥጋዋን በዓል በምናከብርባት: በዚች ዕለት: እንዲህ በሚለው ቃል ይገለጻል::

የእመቤታችን ሥጋዊ ዕረፍቷ: ጥር ፳፩ ቀን: በዕለተ እሑድ ነው:: ፲፪ቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ሓዋርያት: የዕረፍቷን ቀን: ቀደም ብለው: በመንፈስ ቅዱስ ተረድተው: በሙሉ: በአጠገቧ ተሰባስበው ስለነበረ: ቃሏን አሰምታቸውና በረከቷን አሳድራባቸው: በሰላም አንቀላፋች:: እነርሱም: ሰውነቷን: በአጎበር አድርገው: ሊቀብሩ: ወደጌቴሴማኒ ተሸክመው ሲኼዱ: አይሁድ: እንደልማዳቸው: "ቀድሞ: ልጇን: 'ተነሣ! ዓረገ!' እያሉ: ሲያውኩን ይኖራሉ፤ ዛሬ ደግሞ: እርሷን: 'ተነሣች! ዓረገች!' እያሉ ሊያውኩን አይደለምን? ኑ! በእሳት እናቃጥላት!" ብለው ተነሡ:: "ታውፋንያ" የሚባል አይሁዳዊ: ተራምዶ: አስከሬኗ ያረፈበትን የአልጋውን አጎበር ጨበጠው:: ወዲያው: የእግዚአብሔር መልአክ: ኹለቱንም እጆቹን ቀጣው! እጆቹም: በአጎበሩ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## - "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ታውፋንያ፡ ሳያስበው፡ ድንገት በደረሰበት፡ በዚህ ጽኑ መቅሠፍት እጅግ ተደናግጦ፡ እዚያው በወደቀበት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ! "የእውነተኛው አምላክ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት፡ አንቺ፡ በእውነት፡ ድንግል ነሽ! ስለዚህ፡ እኔን በደለኛውን፡ ይቅር ትዪኝ ዘንድ፡ እለምንሻለሁ!" ሲል፡ በልቅሶና በዕንባ፡ ወደእመቤታችን ባቀረበው የልመና ጸሎቱ፡ በሐዋርያትም ምልጃ፡ እጆቹ ወደነበሩበት አካሉ ተመልሰውለት፡ ደኅና ኾነ።

ከዚህ በኋላ፡ መልአኩ፡ ሐዋርያው ዮሐንስን ጨምሮ፡ እመቤታችንን፡ በደመና ነጥቆ፡ ወደገነት ወሰዳት፡ እዚያም፡ በዕፀ ሕይወት ሥር አኖራት። ኋላ፡ ሐዋርያት፡ ዮሐንስን ሲያገኙት፡ "እመቤታችን እንደምን ኾነች?" አሉት። እርሱም፡ "በገነት፡ ከዕፀ ሕይወት ሥር ዐርፋለች!" አላቸው።

የቀሩት ሐዋርያት፡ "ዮሐንስ፡ ያን ድንቅ የእግዚአብሔርን ሥራ አይቶ፡ እኛስ፡ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን!? አቤቱ፡ ለእኛም ቸርነትህን አድርግልን!" ብለው፡ በነሐሴ መባቻ (መግቢያ= ፩ ቀን)፡ በአንድነት ኾነው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ የሱባዔ (የ፩ ሳምንት) ጾምና ጸሎት ጀመሩ። በኹለተኛው ሱባዔ ማብቂያ ዕለት፡ ነሐሴ ፲፬ ቀን እሑድ፡ የእመቤታችንን ትኩስ ሥጋ፡ መልአኩ፡ ከገነት አምጥቶ፡ ለሐዋርያት ሰጣቸው። እነርሱም፡ ልመናቸው ስለተፈጸመላቸው፡ ፈጣሪያቸውን፡ በጸሎት አመስግነው፡ በዚያችው ዕለተ እሑድ፡ ቅዱስ ሥጋዋን ወስደው ቀብረውታል።

እርሷም፡ በሦስተኛው ዕለት፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን፡ ማግሰኞ ተነሥታለች! የእመቤታችንን ትንሣኤ፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ"፡ ወይም፡ "እንደልጇ ትንሣኤ" ያሰኘው፡ ይህ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይታ የመነሣቷ እውነታ ነው።

ጥያቄ:- *ይህ ነገር እንዴት ነው? በእርግጥ አምነን እንቀበለው ዘንድ፡ እስኪ፡ ምሥጢሩን፡ ዘርዘር አድርገህ ግለጽልን? እመቤታችን፡ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይታ የተነሣችው ትንሣኤ፡ የክርስቶስን ትንሣኤ የሚመስል ነው ማለት ነውን?*

መልስ:- *እዎን! ነው። ይህን እውነታ፡ በተቻለኝ መጠን፡ እንዲህ በሚል ቃል ላብራራላችሁ:-*

**"በገነት የቆየችው የእመቤታችን ነፍስ፡ በገነት አብሩዋት እንዲቆይ ተደርጎ፡ በሐዋርያት የሱባዔ ምልጃ ምክንያት፡ ኋላ፡ በመልአኩ እጅ፡ ወደምድር ተመልሶላቸው፡ እሑድ ቀብረውት፡ እስከማግሰኞ በመቃብር ካረፈው ሥጋዋ ጋር፡ በሦስተኛው ቀን ተዋሕዳ፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች!" ማለት ነው። በዚህም፡ ቀደም ብሎ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፥ መቃብርና ትንሣኤ ተፈጽሞ የታየው መለኮታዊ ትንግርት መደገሙ፡ በእውን ተረጋገጠ።**

# ምዕራፍ ፯፡ በዓል።

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።

### የድንግል ማርያም፡ የዕረፍቷ÷ የትንሣኤዋና የዕርገቷ ዜና።

"መለኮት የተዋሓዳት፡ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በመስቀል ላይ፡ ራቁቱን ከተዘረጋው ሥጋዋ ተለይታ፡ ያሙኑ ነፍሳትን፡ ነጻ ሊታወጣ፡ ወደሲኦል ወርዳ ሣለች፡ ፣የ በመስቀል ላይ ቀርቶ የነበረው፡ መለኮት የተዋሓደው ሥጋዋ ደግሞ፡ በመቃብር ዐርፎ፡ ከቆየ በኋላ፡ በሦስተኛው ቀን፡ እሑድ፡ ሥጋውና ነፍሱ እንደገና ተዋሕደው፡ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ" ማለት ነው።

ይህ ኹሉ ሲኾን፡ ማለትም፡ በመጀመሪያው የሓዋርያት ሱባዔ ጊዜ፡ ሓዋርያው ቶማስ፡ በቦታው አልነበረም። ለሓዋርያት በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ እርሱም፡ እንደለመደው፡ ደመና ጠቅሶ፡ እግዚአብሔር ባወቀውና ባደረገው ምክንያት ዘግይቶ፡ በዚያ እየተጓዘ፡ ከሀገረ ስብከቱ፡ ወደወንድሞቹ ሓዋርያት ሲመጣ፡ እመቤታችንን፡ ስታርግ አገኛት። ያችም ዕለት፡ ትንሣኤዋ ብቻ ሳይኾን፡ ዕርገቷም፡ እንደልጇ ዕርገት፡ በ፵ኛው ቀን የተፈጸመባት፡ መስከረም ፳፩ ቀን፡ እሑድ ነበረች። ቶማስም፡ ከደመናው ሊወድቅ እስኪናወጽ ድረስ፡ ሰውነቱ ታውኮበት፡ "ቀድሞ፡ ሌሎቹ ወንድሞቼ ኹሉ ታድለው፡ የልጅሽን ትንሣኤ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ፤ አኹን ደግሞ፡ እነርሱ፡ ኹላቸው፡ ይኸው፡ ያንቺን ትንሣኤ ቀድመው ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁን?" ብሎ ማዘኑን ገለጸላት። እመቤታችንም፡ "አይዞህ! አትዘን፤ እኒያ ወንድሞችህ፡ ኹላቸውም፡ ትንሣኤዬን÷ ዕርገቴንም አላዩም፤ አንተ ግን፡ ታድለሃል፤ ኹለቱንም አይተሃልና። አኹንም፡ ኼደህ፡ 'ተነሣች! ዐረገች!' ብለህ ንገራቸው!" ብላ፡ ተገንዛበት የነበረውን ሰበን (ሽማ) ሰጥታ፡ ሰደደችው።

ቶማስ፡ ከቦታው ደርሶ፡ በሱባዔና በጉባኤ የሰነበቱትን ሓዋርያትን ሲገናኛቸው፡ "ኧረ! የእመቤታችን ነገር፡ እንደምን ኾነ?" ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፡ "ሥጋዋን ተቀብለን አግኝተን ቀበርናት!" አሉት። "መቼ?" አላቸው። "በነሓሴ መባቻ ሱባዔ ገብተን፡ በ፲፬ኛው ቀን!" አሉት። እርሱም፡ በመገረም፡ "ሞት በጥር÷ በነሓሴ መቃብር! ኧረ ተዉ! ይህ ነገር፡ አይመስለኝም!" አላቸው። ሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስም፡ "አንተ እንጂ፡ ልማድህ ነው! አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም፤ አንተ እየተጠራጠርህ፡ ሰውን ኹሉ፡ ስታጠራጥር ትኖራለህ፤ አኹንም፡ እውነቱን ልታውቅ ከወደድህ፡ ና እይ!" አለው። ቶማስም፡ የያዘውን ያውቃልና፡ ጸጥ ብሎ ይሰማቸዋል። ከዚህ በኋላ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ ተቆጥቶ ኼዶ፡ መቃብሩን ቢከፍተው፡ አጣት፤ እርሱም÷ አብረውት የነበሩት የቀሩት ሓዋርያትም ደንግጠው በያሉበት ቆሙ። በዚህ ጊዜ፡ ቶማስ፡ "'አታምኑኝም!' ብዬ ነው እንጂ፡ እመቤታችንስ፡ ደስ ይበላችሁ! ተነሥታለች! ዐርጋለች!" አላቸው። ከእርሷ ያገኘውን፡ የተገነዘችበትንም ሰበን ሰጣቸው። ሓዋርያትም፡ ያን በማየታቸው፡ ደስ ብሏቸው፡ ለበረከት ተካፈሉት።

ይህ በኾነ፡ ልክ፡ በዓመቱ፡ የቀሩት ሓዋርያት፡ "ቶማስ፡ ትንሣኤሽን÷ ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን? አቤቱ፡ እኛንም፡ ለዚህ ዕድል አብቅተህ፡ አሳየን!" ብለው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ ኹለተኛ የሱባዔ ጾምና ጸሎትን፡ ነሓሴ ፩ ቀን፡ በአንድነት ጀመሩ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ነሐሴ ፲፬ ቀን፡ ኹለት ሱባዔን ጨርሰው፡ በሦስተኛው ዕለት፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በጽርሐ አርያም፡ ራሱን፡ ሠራዒ (ዋና) ቄስ፥ ቅድስት እናቱን፡ እመቤታችን ድንግል ማርያምን፡ መንበር፡ ቅዱስ ጴጥሮስን፡ ንፍቅ (ረዳት) ካህን፡ ቅዱስ እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ፡ ቆርቦ፡ እርሷንም፡ እነርሱንም፡ አቍርቧቸዋል።

## ኪዳነ ምሕረት።

እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘው ዘለዓለማዊ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ "ኪዳነ ምሕረት" ይባላል። የዓመቱም በዓል፡ የካቲት ፲፮ ቀን ይውላል።

የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፡ የፈጣሪያቸውን ፈቃድ መተላለፋቸው፡ በየራሳቸውና በልጆቻቸው ላይ፡ የዲያብሎስን ግዞነት፡ የኃጢአትን ቀንበርና የሞትን ፍዳ አመጣባቸው። በየዘመናቱ፡ ለደጋጎች ልጆቻቸው የተሰጡት፡ አምላካውያት ቃል ኪዳናትና የ፭ሺ፭፻ ዓመታት ንስሓቸው ግን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ ከሰማየ ሰማያት ልዕልናው፡ ወደምድር አውርዶ፡ ሰው ለመኾን አበቃው፡ መለኮታዊውም ፈቃድ፡ በመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ስለተፈጸመ፡ ይህ፡ ፍቅርና ርኅራኄ፡ የሰው ልጆች፡ የእግዚአብሔር ልጆች የሚኾኑበትን፡ የመጨረሻውን ክብር አቀዳጃቸው፤ የኃጢአት ሥርየትንና የትንሣኤ ሕይወትን አስገኘላቸው። ይህ፡ የልጅነት ጸጋ፥ ይህ፡ የሥርየት ነጻነት፡ ይህ፡ የትንሣኤ ክብር፡ ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖር ዘንድ፡ በመለኮታዊ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ታተመ!

ማኅተሙም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ የተዋሐደውና በመስቀል ላይ የሠዋው፥ ዛሬም፡ እኛ፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን፡ በንስሓ ነጽተን፡ ከቅዳሴ ጸሎት በኋላ የምንቀበለው፡ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው። በእርሱ፡ በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነትና በእርሷ፡ በእናቱ፡ በድንግል ማርያም ሰውነት የተዋሕዶ ምሥጢር፡ ለፍጥረቱ ኹሉ፥ በተለይም፡ ለሰው ዘር፡ የተገኘው፡ ይህ ኹሉ ጸጋና በረከት፡ "ኪዳነ ምሕረት" ተብሎ፡ በያመቱ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን፡ በኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና በኪዳናውያት ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በጥልቅ መንፈሳዊ ተመስጦ ይከበራል።

## የአጽዋማት ሰንበታት።

እንደንዑሳን በዓላት ተቈጥረው የሚከበሩ፡ በጾም ወራት የሚውሉ፡ ሰንበታት አሉ፤ እነዚህም፡ "ዓቢይ ጾም"፥ ወይም፡ በሕዝባዊ አነጋገር፡ "ሁዳዴ" የሚባለው ጾም፡ ከመግባቱ በፊትና ከገባ በኋላ ያሉት፡ የእሑድ ሰንበታት ናቸው።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።

### የአጽዋማት ሰንበታት፦ መርዓዊ፣ ዘዘወረደ፣ ቅድስት።

---

ከእነዚህም፡ ቀዳሚዎቹ፡ "መርዓዊ" እና "ዘዘወረደ" የሚል ስያሜ የተሰጣቸው፡ ሰንበታት ናቸው፤ "መርዓዊ" የተባለው ሰንበት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ እንደሚነበበው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዕለተ ዓርብ የሚቀበለው የመስቀል መከራ፡ ለእርሱ፡ የሙሽርነቱ የሠርግ በዓል ስለኾነ፡ ይህችን ጽዋውን፡ እንደአርበኛ ወደሚቀበልባት፡ ወደኢየሩሳሌም የጀመረውን ጉዞ የሚያዘክረውና ከ"ጾመ ኢትዮጵያ" ቀጥሎ ያለው ዕለተ እሑድ ሲኾን፤ የዓቢይ ጾም መግቢያና ለ"ጾመ ሕርቃል" ሰኞ ዋዜማ የኾነው፡ ተከታዩ ዕለተ እሑድ፡ "ዘዘወረደ" ("ቅበላ") የተባለው ነው። ስለእነዚህና ከዚህ በኋላ ተያይዘው ስለሚቀጥሉት፡ "ቅድስት"፥ "ምኵራብ"፣ "መፃጉዕ"፡ ደብረ ዘይት"፡ "ገብር ኄር" እና "ኒቆዲሞስ" ስለተባሉት የእሑድ ሰንበታት፡ ከዚህ የሚከተሉት አጫጭር መግለጫዎች፡ በመጠኑም ቢኾን ያብራሩላችኋል፦

#### መርዓዊ።

በግእዝ፡ "መርዓዊ" ማለት፡ "ሙሽራ" ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱን፡ በሙሽራ መስሎ ተናግሩዋል፤ ይህም፡ *"የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት፡ ወደእርሱ ቀርበው፡ 'እኛና ፈሪሳውያን፡ ብዙ ጊዜ የምንጦመው፡ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት፡ ስለምንድር ነው?' አሉት፤ ጌታችን ኢየሱስም፡ እንዲህ አላቸው፡ 'ሚዜዎች፡ ሙሽራው፡ ከእነርሱ ጋር ሳለ፡ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን፡ ሙሽራው፡ ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፤ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።"* ደግሞም፡ *"በዚያን ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መብራታቸውን ይዘው፡ ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ፡ ዐሥር ቈነጃጅትን ትመስላለች!"* በሚሉት ቃሎቹ ይታወቃል።

መንፈስ ቅዱስን የተመሉ ቅዱሳን ጻድቃንም፡ እርሱን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በሙሽራ መስለው ተናግረዋል፤ ለዚህም፡ መጥምቁ ዮሐንስ፡ *"እናንተ፡ 'እኔ፡ ክርስቶስ አይደለሁም፤ ነገር ግን፡ ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ!' እንዳልሁ፡ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ። ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ፡ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን፡ በሙሽራው ድምፅ፡ እጅግ ደስ ይለዋል፤ እንግዲህ፡ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ፤ እርሱ፡ ሊልቅ፥ እኔ ግን፡ ላንስ ያስፈልጋል።"* ብሎ የተናገረው ቃል፡ አንዱ ማስረጃ ይኾናል።

ስለዚህ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደፊት፡ በዕለተ ዓርብ እንዲቀበለው፡ የሚጠብቀው መከራ፡ ለእርሱ፡ እንደሙሽርነት በዓል፥ መስቀሉም፡ እንደሠርግ አዳራሽ ተደርጎ፡ ትንቢቱ፡ በቅድሚያ፡ በቅዱሳን ነቢያት ስለተነገረና በቅዱሳት መጻሕፍት ስለተጻፈ፡ ከ"ጾመ ኢትዮጵያ" (ከነነዌ ጾም) በፊት ያለው፡ ዕለተ እሑድ ሰንበት፡ "መርዓዊ" ተብሏል።

በዚያች የሰንበተ ክርስቲያን እሑድ የሚዘመረው ምስባክ፡ ከዳዊት መዝሙራት፡ *"ወውእቱሰ፡ ከመ መርዓዊ፡ ዘይወጽእ እምጽርሑ፤ ይትፌሣሕ፡ ከመ ያርብን፡ ዘይሜርድ ፍኖቶ፤ እምአጽናፈ ሰማይ፡ ሙጻኡ!"* የሚለው ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"እርሱም፡ እንደሙሽራ፡ ከእልፍኙ ይወጣል፤ እንደአርበኛም፡ በጉዞው ሲፋጠን ደስ ይለዋል፤ መውጫውም፡ ከሰማይ ዳርቻ ነው!"* ተብሎ የሚተረጐመው፡ ይህም ቃል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በሕማማተ መስቀሉ የሚቀበላትን፡ የሙሽርነት ጽዋ መከራውን፡ አጣጥሞ ወደሚጨልጥባት፡ ወደኢየሩሳሌም የጀመረውን፡ ያን የግሥጋሤ ጉዞ የሚያከናውነው፡ እንዴት እንደኾነ፡ ያመላክታል፤ ይኸውም፡ አንድ ጀግና አርበኛ፡ ለአገሩና ለማንነቱ፥ ለሚኖርለትም ታላቅ ዓላማ፡ ደሙን እስከማፍሰስ በሚጠይቅ መሥዋዕትነት ተዋግቶ፡ የድል አክሊልን እንዲቀዳጅ ወደሚያበቃው የሰልፍ ሜዳ ለመድረስ፡ በፍጹም ቆራጥነት ከሚያደርገው ጥድፊያ ጋር በማመሳሰል መኾኑን፡ በትንቢቱ ቃል አፈጻጸም ስለታየ ነው።

ይህንም እውነታ፡ እንዲህ የሚለው፡ በዕለቱ የሚነበበው፡ የአዲስ ኪዳኑ የምሥራች ቃል ያረጋግጠዋል፦ *"ጌታችን ኢየሱስ፡ ...ዐሥራ ኹለቱን ደቀ መዛሙርቱን፡ ወደእርሱ አቅርቦ፡ እንዲህ አላቸው፦ 'እነሆ፡ ወደኢየሩሳሌም እንወጣለን፤ ስለሰው ልጅ፡ በነቢያት መጻሕፍት የተጻፈው ኹሉ፡ በእርሱ ላይ ደርሶ ይፈጸማል፤ ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፤ ይዘብቱበታል፤ ይሰድቡታል፤ ይተፉበታል፤ ይገርፉታል፤ ይገድሉታል። በሦስተኛዪቱም ቀን ይነሣል።' እነርሱ ግን፡ ከዚህ ንግግሩ፡ ያስተዋሉት ነገር የለም፤ ይህ የተናገረው ቃል፡ ለእነርሱ፡ ተሠውሮባቸው ነበርና፤ ምን እንዳለም፡ አላወቁም።"*[፻፴]

ዘዘወረደ።

"ጾመ ሕርቃል" የተባለው የዓቢይ ጾም መግቢያ የኾነው እሑድና ተያይዞ የሚቀጥለው ሳምንቱ፡ በግእዝ፡ "ዘዘወረደ" ይባላል። "ዘዘወረደ" የሚለው ቃል፡ "ረ" ላልቶ ሲነገር፡ "ወረደ" ከሚለው የግእዝ ቃል፡ "ረ" ጠብቆ ሲነገር፡ "ወረደ" በሚለው ኢትዮጵያኛው ቃል ይተረጐማል። "ዘዘወረደ" ማለትም፡ "በልዩ ልዩ መልክ መውረድን" ያመለክታል።

"ያ፡ በሰማያት የሚኖረው፥ በእሳትና መብረቅ፥ በከባድ ደመናና ነጐድጓድ፥ በበረታ የቀንደ መለከትም ድምፅ፡ ወደምድር የወረደውና በሙሴ መሪነት፡ በምድረ በዳ ለሚጓዙት የእስራኤል ልጆች፡ በሲና ተራራ የተገለጠው፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ 'እግዚአብሔር' ብለን የምንጠራው ፈጣሪና የማይታየው አምላክ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ሰው ኾኖና በበረት ተወልዶ፥ የመስቀል መከራን ተቀብሎና ሞቶ፥ ተቀብሮና ተነሥቶ፡ ፍጥረተ ዓለሙን፡ ከዲያብሎስ አገዛዝ፥ ከኃጢኣት ቀንበርና ከሞት ፍዳ ሊያድን፡ ከሰማየ ሰማያት ወረደ!" ለማለት፥ ደግሞም፡ ሙሴ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ምሳሌ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን ቃላት፥ ትእዛዛት እና/ወይም፡ ጽላት ይዞ፡ ከሲና ተራራ ወደእሥራኤል ሕዝብ የመውረዱን ዝክረ ነገር ለማስታወስ፡ "ዘዘወረደ" ተብሏል።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

### የአጽዋማት ሰንበታት:- መርዓዊ፣ ዘዘወረደ፣ ቅድስት::

---

ይህም: በብሉዩ ኪዳን: *"እግዚአብሔርም: በሲና ተራራ ላይ: ወደተራራው ራስ ወረደ! ...ሙሴም: ወደሕዝቡ ወረደ፤ እግዚአብሔር ያለውንም ቃል ነገራቸው:: ...ኹለቱንም የምስክር ጽላቶች: በእጁ ይዞ: ከተራራው ወረደ::"*÷ በአዲሱም ኪዳን: *"ወአልቦ ዘዓርገ ውስተ ሰማይ÷ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ: ወልደ እጓለ እመሕያው::"* ማለትም: *"በሰማይ ከሚኖረውና ከሰማይ ከወረደው የሰው ልጅ በቀር: ወደሰማይ የወጣ: ማንም የለም!"* በሚለው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ታውቋል:: ይኸው እሑድ: በሕዝባዊ ስያሜ: "ቅበላ" ይባላል::[፻፺፭]

## ቅድስት::

ለመደበኛው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ጾመ አርብዓ": መነሻ የኾነው: የመጀመሪያው እሑድ: "ቅድስት" ይባላል፤ ለእግዚአብሔር ይኾን ዘንድ: ተለይቶ የተቀመጠ፥ የተሰጠ፥ የቀረበ ነገር ኹሉ: "ቅዱስ" ስለሚባል: ይህች ዕለተ ሰንበት÷ ወይም: ሳምንት: በሴት አንቀጽ: "ቅድስት" ተብላለች::

ኢየሱስ ክርስቶስ: በቆሮንቶስ በረሃ: አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት የጾመውን ጾም በማስታወስ: እኛም: እርሱ ባስተማረን መንገድ እንጾማት ዘንድ: "የጌታ ጾም" ተብላና ተለይታ የተሰጠችን ጾም መኾኗን ለማመልከት÷ እንዲሁም: *"ቅዱስ"* የኾነውን አምላክ: ቃሉን ተከትለን: እኛም: እያንዳንዳችን: እየራሳችንን: በቅድስና አጽንተን ለማኖር: ግዳጅ ያለብን መኾኑን ለማሳሰብ: "ይህች ዕለተ ሰንበተ እሑድ÷ ይህች ሳምንትና ይህች አርባ ቀን: ለእግዚአብሔር የተለየች ናት" ለማለት: "ቅድስት" የሚለውን ስያሜ አግኝታለች::

ይህም: *"ወበከመ ጸውዐክሙ ቅዱስ ውእቱ÷ አንትሙኒ: ኩኑ ቅዱሳነ: በኵሉ ግዕዝክሙ! እስመ ጽሑፍ: ዘይብል: 'ኩኑ ቅዱሳነ: እስመ ቅዱስ አነ!'"* ማለትም: *"የጠራችሁ: እርሱ: እግዚአብሔር: ቅዱስ እንደኾነ: እንዲሁ: እናንተም: በአኗኗራችሁ ኹሉ: ቅዱሳን ኹኑ! 'እኔ ቅዱስ ነኝና: እናንተም: ቅዱሳን ኹኑ!' የሚል ቃል ተጽፏልና::"* ደግሞም: *"እስመ ኢጸውዐነ እግዚአብሔር: ለርኵስ: ዘእንበለ ለቅድሳት!"* ማለትም: *"እግዚአብሔር: ለቅድስና እንጂ: ለርኵሰት አልጠራንምና::"* በሚለው የአምላክ ቃል ታውቋል::

ኹለንተናችንን: ከክፋቱ ዓለም ለይተን: ራሳችንን: በጾም በመቀደስ: ሰውነታችንን: ለእግዚአብሔር ብቻ ልናስገዛ የሚገባን መኾኑን: ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ቃላት ጋር: በዚህች ዕለተ ሰንበት የሚዘመረው÷ የሚሰበከውና የሚነበበው: ከዚህ የሚከተለው: ሌላው: የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ: እንዲህ እያለ ያስረዳናል:-

፩ኛ: *"ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት፤ ወተሐሠዩ ሎቱ በረዓድ፤ አጽንዕዋ ለጥበብ: ከመ ኢይትመዓዕ እግዚአብሔር::"* ማለትም: *"ለእግዚአብሔር: ስለእርሱ: ደስ ብሏችሁ: በፍርሃትና በረዓድ ተገዙ! እንዳይቈጣም: ተግሣፁን ተቀበሉ!"*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*፪ኛ፡ "ለኹለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው፡ ማንም የለም፤ ወይም፡ አንዱን ይጠላል፥ ኹለተኛውንም፡ ይወድዳል፤ ወይም፡ ወደአንዱ ይጠጋል፥ ኹለተኛውንም፡ ይንቃል፡፡ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም፡፡"*

### ምኵራብ፡፡

በጾመ አርብዓ፡ ከ"ቅድስት" ቀጥሎ ያለው፡ የእሑድ ሰንበትና የተያያዘው ሳምንት፡ "ምኵራብ" ይባላል፤ "ቤተ መቅደስ"፥ ወይም፡ ክርስትናን የተቀበሉ ወገኖች፡ ተሰብስበው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚጸልዩበትና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ለመላው የሰው ዘር፡ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች የሚያገኙባት፡ የመድኃኔ ዓለምን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የሚቀበሉበት ቦታ፡ "ቤተ ክርስቲያን" እንደሚባል ማለት ነው፡፡ በሕገ ኦሪቱ እምነት ጸንተው የቀጠሉት አይሁድ፡ ዛሬም፡ የጸሎት ቦታቸውን፡ "ምኵራብ" እያሉ ይጠሩታል፡፡

የዚህ ስያሜ ምሥጢር፡ እንደሌሎቹ ኹሉ፡ ስፋትና ጥልቀት አለው፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር አብ፡ እውነተኛና የተቀደሰ ማደሪያው ይኾን ዘንድ፡ ጥንቱንም፡ በመለኮታዊ ቸርነቱና ጥበቡ፡ የሠራው፥ ኋላም፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በልጁ መሥዋዕትነትና የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለሥርየት አብቅቶና በትንሣኤ ሕይወት አድሶ፡ ለዘለዓለማዊ ህልውና ያዘጋጀው "ቤት"፥ ወይም፡ "ሕንፃ"፡ በፍጡር እጅና በተፈጥሮ ቍሳቍሶች የተሠራውን ሳይኾን፡ እርሱ፡ በአርአያውና በመልኩ የፈጠረው ራሱ፡ "ሰው" መኾኑ፡ ተረጋግጦ የሚታወስበት፥ የሚነገርበትና የሚታወቅበት ሰሞን፡ ከዚች ዕለተ እሑድ ጀምሮ ባለው ሳምንት በመኾኑ ነው፡፡

ይህንም እውነታ፡ ደቀ መዛሙርቱ የኾኑት ሐዋርያት ሳይቀሩ የተረዱትና የተገነዘቡት፡ መምህራቸው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል መከራው ሞቶ ከተነሣ፥ መንፈስ ቅዱስም ከወረደላቸውና ካደረባቸው በኋላ መኾኑን፡ በዕለቱ የሚዘመረው፥ የሚሰበከውና የሚነበበው፡ የነቢያቱ ትንቢትና የአዲስ ኪዳኑ ምሥራች፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት እያብራሩ ያመላክታሉ፦

*"እስመ ቅንዓተ ቤትከ በልአኒ፤ ትዕይርቶሙ፡ ለእለ ይትዔየሩከ ወድቀ ላዕሌየ፤ ወቀጻእክዋ በጾም ለነፍስየ፡፡" ማለትም፡ "የቤትህ ቅናት በልታኛለችና፤ የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቋልና፤ ሰውነቴን፡ በጾም ቀጣኋት፡፡" ደግሞም፡ "የአይሁድ የፋሲካቸው በዓል ቀርቦ ነበር፤ ጌታችን ኢየሱስም ወደኢየሩሳሌም ወጣ፡፡ በምኵራብም፡ ላሙን፥ በጉን፥ ርግቡን፡ የሚሸጡትን፥ የሚገዙትንም፥ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፡፡ ከገመድ የተሠራ አለንጋን አበጀ፤ በጉንም፥ ላሙንም፥ ኹሉንም፡ ከምኵራብ አስወጣ፤ የለዋጮችንም ወርቅ በተነ፤ መደርደሪያቸውንም አፈረሰ፤ የርግብ ሻጮችንም ወንበር ገለበጠ፡፡ ርግብ ሻጮችንም፡ 'ይህን፡ ከዚህ አውጡ! ወዲያ በሉ! የአባቴን ቤት፡ የገበያ ቦታ አታድርጉ!' አላቸው፡፡*

## ምዕራፍ ፮፣ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### የአጽዋማት ሰንበታት፦ ምኵራብ።

---

*"ደቀ መዛሙርቱም፡ 'የቤትህ ቅናት በላኝ፤' የሚል ቃል ተጽፎ እንዳለ፡ አስታወሱ። አይሁድም መልሰው፡ 'ለዚህ ድርጊትህ፡ ምን ምልክትን ታሳያለህ?' አሉት። ጌታችን ኢየሱስም፡ 'ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት! በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለሁ፤' ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም፡ 'ይህ ቤተ መቅደስ፡ በአርባ ስድስት ዓመታት ተሠራ፤ አንተስ፡ በሦስት ቀኖች ውስጥ ታነሣዋለህን?' አሉት። እርሱ ግን፡ "ቤት" ስለተባለው ስለሰውነቱ ቤተ መቅደስ ነገራቸው። ከሙታን በተነሣ ጊዜም፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ ስለዚህ፡ እንደነገራቸው አሰቡ፤ በመጻሕፍት ቃል፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ በነገራቸው ነገርም አመኑ።"*

ታላቅ ምሥጢራዊ መልእክት ያለውን፡ ይህን፡ የአምላክ ቃል ለማጠናከር፡ ተያይዘው ከሚጠቀሱት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት መካከል፡ እንዲህ የሚሉት ይገኛሉ፦

*"አንትሙሰ፡ ሕንፃ እግዚአብሔር አንትሙ! ...ኢተአምሩኑ፡ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ? ወመንፈሰ እግዚአብሔር ኅዱር ላዕሌክሙ።" ማለትም፡ "የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ...እናንተ፡ የእግዚአብሔር ታቦቱ፡ ቤተ መቅደሱም እንደኾናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም አድሮባችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም፡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ ቅዱስ ነውና፣ ያውም፡ እናንተ ናችሁ። ...ወይስ፡ ሥጋችሁ፡ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በእናንተ የሚኖረው፡ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደኾነ አታውቁምን? ... የእግዚአብሔር ታቦትንስ፡ በጣዖት ቤት የሚያኖር ማን ነው? እኛ፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና።"* ።

፡ "ምኵራብ" በተባለው፡ በዚህ ዕለተ እሑድና ተያይዞ ባለው ሳምንት ውስጥ፡ የእነዚህ ምሥጢራውያት ቃላት ማጠቃለያ ፍቺ፡ ተብራርቶና ተስፋፍቶ ይነገርበታል። ሰው የኾነውን አምላክ፡ እንዲያ፡ እንደእሳት፡ ያቃጠለው ቅንዓት የተነሣሣበት፡ የሰዎች እጅ በሠራውና "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ" ተብሎ፡ የርኵሰት ተግባር እየተፈጸመበት፡ በሚዘበትበት ሕንፃ ውስጥ ሲካኼድ ባየው አሳዛኝ ኹኔታ አለመኾኑ ይገለጽበታል፤ ነገር ግን፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር፡ የዘለዓለም ማደሪያው ይኾን ዘንድ፡ በመልኩ ፈጥሮ ያነፀው፡ ሰብአዊው አካል፡ የክፋት መንፈስ መፈንጫና መጫወቻ ኾኖ መኖሩን በማወቁ መኾኑ፡ ይተኮርበታል። እንዲሁም፡ ከገበያ የርኵሰት መደብርነት አጥርቶ፡ በቅድስናው ያነጻው፡ ያን፡ ሰው የሠራውንና የሚፈራርሰውን በድን ሕንፃ ሳይኾን፡ ራሱ የለበሰውን የሰውነት አካል የመሰለውን፡ የሰውን ኹሉ ሕያው ልቦና የመኾኑ ምሥራች ይታወጅበታል።

ለዚህ፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ፡ *"ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት! እኔም፡ በሦስተኛው ቀን አነሣዋለሁ፤"* ብሎ የተናገረውን የራሱን ቃል፡ ራሱ የፈጸመውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመምሰል፡ የመጀመሪያው መስካሪ ኾኖ፡ በሰማዕትነት ተሠውቶበታል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*ይህም፡ "'ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፡ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት፡ ለእኔ፡ ምን ዓይነት ቤትን ትሠራላችሁ?' ይላል ጌታ፡ 'ወይስ፡ የማርፍበት ሥፍራ፡ ምንድር ነው? ይህንስ ኹሉ፡ እጄ የሠራችው አይደለምን?' እንዳለ፡ ልዑል፡ የሰው እጅ በሠራችው አይኖርም።"* ሲል፡ ይኸው ሰማዕት፡ የነቢዩን ቃል እየጠቀሰ በተናገረው፡ ደግሞም፡ *"ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ኹሉ የፈጠረ አምላክ፡ እርሱ፡ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና፡ እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፡ እርሱም፡ ሕይወትንና እስትንፋስን፡ ኹሉንም፡ ለኹሉ ይሰጣልና፡ አንዳች እንደሚጐድለው፡ በሰው እጅ አይገለገልም።"*[፻፺፮] በሚለው በሐዋርያው ቃል ተረጋግጧል።

መፃጉዕ።

"*መፃጉዕ*"፡ በጾመ አርብዓ፡ ከ"ምኵራብ" ቀጥሎ ላለው፡ የእሑድ ሰንበትና ተያይዞ ለሚገኘው ሳምንት፡ የተሰጠ ስያሜ ነው። በግእዝ፡ "*መፃጉዕ*" ማለት፡ "ድውይ"፡ "በሕመም የሚማቅቅ"፡ "የዐልጋ ቍራኛ" ማለት ነው። ስያሜው፡ የደዌው ዝክረ ነገርና የፈውሱ ዜና መዋዕል በዚች፡ ዕለተ እሑድና በተከታዩ ሳምንት ከሚነገርለት በሽተኛ ተገኝቷል።

ከዚች ሰንበተ ክርስቲያን ጀምሮ፡ እስከሚቀጥለው ድረስ ባለው ሰሞን፡ በአንድ በኩል፡ የሰውን ልጆች፡ ከሥጋዊው ደዌ ይልቅ፡ በከፋ መጠን ስለሚያሠቃያቸውና ስለሚጎዳቸው፡ "ኀጢአት" ስለተባለው፡ ስለነፍሳዊው ደዌ፡ ረቂቅ በሽታነትና ጠንቀኛነት፡ በስፋትና በብዛት ይነገራል፡ በአንጻሩ ደግሞ፡ እኒሁ፡ የሰው ልጆች፡ ራሳቸው፡ ከ"እባቡ" እና ከ"ዘንዶው" ዲያብሎስ ጋር ተመሣጥረው ካመጡት፡ ለዘለዓለማዊው ሞት ካበቃቸው፡ ከዚሁ፡ ከኀጢአት ክፉ ጠንቅ፡ ፍጹም የኾነውን፡ መለኮታዊ ፈውስ ተቀብለው፡ መዳን ስለቻሉበት፡ አምላካዊ ቸርነትና ጸጋ ይታሰባል፡ ይሰበካል፡ ይዘመራል።

ይህም፡ ከመደበኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች መካከል በተጠቀሱት፡ ከዚህ በሚከተሉት፡ አምላካውያት ቃላት ውስጥ፡ በግልጽ ተመልክቶ ይታወቃል፡-

ከነቢያቱ መዝሙራት፡ *"ተሣሃለኒ እግዚኦ፡ እስመ ድውይ አነ፡ ወፈውሰኒ፡ እስመ ተሃውካ አዕፅምትየ፡ ነፍስየኒ፡ ተሃውከት ፈድፋደ።"* ማለትም፡ *"እኔ፡ በሕመም የምሠቃይ በሽተኛ ነኝና፡ አቤቱ፡ ይቅር በለኝ! አጥንቶቼም ታውከዋልና፡ ፈውሰኝ! ከዚህ የተነሣ፡ ነፍሴ፡ እጅግ ተጨነቀች።"* የሚለው አንዱ ነው።

ከወንጌላውያኑ መካከል ደግሞ፡ *"ወሀሎ ሀየ፡ አሐዱ ብእሲ፡ ዘሠላሳ ወሰመንቱ ክረምት እምዘደወየ፡"* ማለትም፡ *"በዚያም፡"* በግእዝ፡ *"ቀላየ አባግዕ"*፥ በዕብራይስጥ፡ *"ቤተ ሳይዳ"*፥ *በኢትዮጵያኛ፡ "የበጎች መዋኛ"* የሚል ትርጉም ባላት፥ *'ምጥማቃት ዘጽሩጻጥቄ' በምትባል*፥ የጠበል ኵሬ ዳር ተቀምጦ፡ የነበረ፡ *"ከታመመ፡ ሠላሳ ስምንት ዓመታት የኾነው፡ አንድ ሰው ነበር።"* በሚለው ቃል የሚጀምረው፡ የብሥራቱ ቃል ይጠቀሳል።

## ምዕራፍ ፮፣ በዓል::

### ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

### የአጽዋማት ሰንበታት:- መፃጉዕ፣ ደብረ ዘይት::

---

ቃሉም: እንዲህ እያለ ይቀጥላል:- *“የእግዚአብሔር መልአክ: ወደመጠመቂያው ወርዶ: ውኃውን በሚያናውጠው ጊዜ: ከውኃው መታወክ በኋላ: መጀመሪያ ገብቶ የሚጠመቀው በሽተኛ: ካለበት ደዌ ኹሉ ስለሚፈወስ: በኢየሩሳሌም በምትገኘው:”* በዚያች ኾሬ ዳር: *“ዕውሮች፥ አንካሶች፥ ልምሾዎች፥ ሰውነታቸው የሰለለ፥ የደረቀና ያበጠ: ብዙ ድውያን ተኝተው:* ይጠባበቁ ነበር::

*“ጌታችን ኢየሱስም: ያን ሰው: ከአልጋው ተጣብቆ አየና: በደዌ ታሥሮ: ብዙ ዘመን እንደቆየ አውቆ: 'ልትድን ትወድዳለህን?' አለው:: በሽተኛውም: 'አዎን: ጌታ ሆይ! ግን: ውኃው በተናወጠ ጊዜ: ወደመጠመቂያው የሚያወርደኝ ሰው የለኝም፡ እኔ በምመጣበት ጊዜም: ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል፣' አለው:: ጌታችን ኢየሱስም: 'ተነሥና: አልጋህን ተሸክመህ ኺድ!' አለው:: ያን ጊዜም: ያ ሰው ድኖ: አልጋውን ተሸክሞ ኼደ:: ያችም ቀን ቀዳሚት ሰንበት ነበረች:: አይሁድም: የዳነውን ሰው: 'ዛሬ ሰንበት ነው፤ አልጋህን ልትሸከም አይገባህም!' አሉት:: ...ከዚህ በኋላ: ጌታችን ኢየሱስ: ያን: የዳነውን ሰው: በምኩራብ አገኘው፤ 'እነሆ: ድነሃል፤ ግን: ከዚህ የባሰ እንዳያገኝህ: ዳግመኛ እንዳትበድል እወቅ!' አለው::”* በሚለው ቃል ይፈጸማል::[፻፺፰]

### ደብረ ዘይት::

“ደብረ ዘይት”: በጾመ አርብዓ እኩሌታ: ከ“መፃጉዕ” ቀጥሎ ባለው: የእሑድ ሰንበት ላይ ይውላል፤ “ደብረ ዘይት”: የሚለው ስያሜ ለዚች ሰንበተ ክርስቲያንና ተያይዞ ለሚገኘው ሳምንት የተሰጠው: ሐዋርያት: ስለዓለሙ ፍጻሜና ስለዳግም ምጽአቱ: ቀደም ብለው: ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላቀረቡት ጥያቄ: ምሥጢራዊ መልሱን: ገላልጾ የነገራቸው: “ደብረ ዘይት” በተባለው: የወይራ ዘይት አትክልት በነበረበት ተራራ ላይ በመኾኑ ነው::

በዚች ዕለትና በሳምንቱ ውስጥ: ስለዓለሙ መጨረሻና ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት: በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጻፉት የእግዚአብሔር ቃላት: እየተጠቀሰ ይነገራል፤ ይሰበካል፤ ይዘመራል:: ከእነዚህ መካከል: *“እግዚአብሔርሰ: ገሃደ ይመጽእ፤ ወአምላክነሂ ኢያረምም፤ እሳት ይነድድ ቅድሜሁ::”* ማለትም: *“እግዚአብሔር: በፊቱ: እሳት እየነደደ: በገሃድ ይመጣል፤ አምላካችን ዝም አይልም::”* የሚለው: ከነቢያት: አንዱ: በመዝሙራቱ የተነገረው ትንቢት ይገኛል::

ከዚህም ጋር: በዚህ ውይይታችን: የምሥጢረ ትንሣኤ ርእስ ሥር: የተሰጠው ሰፊ ሐተታ: ትዝ ይላችኋል:: ያም: *“ወእንዘ ይነብር ውስተ ደብረ ዘይት: ቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ: እንዘ ባሕቲቶሙ፤ ወይቤልዎ:- 'ንግረነ፤ ማእዜ ይከውን ዝንቱ? ወምንት ተአምሪሁ ለምጽአትከ? ወለኅልቀተ ዓለም?' ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ: ወይቤሎሙ፤”* በሚል ቃል የሚጀምረው ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

የዚህም ትርጉም፡ *"በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሣለ፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ ለብቻቸው፡ ወደእርሱ ቀረቡና እንዲህ አሉት፡- 'ንገረን! ይህ፡ መቼ ይኾናል? የመምጣትህና የዓለሙ ፍጻሜስ፡ ምልክቱ፡ ምንድር ነው?' ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡ እንዲህ አላቸው፡-" "ትጋሁ እንከ! እስመ ኢትአምሩ፡ በአይ ሰዓት ይመጽእ እግዚእክሙ::"* ማለትም፡ *"እንግዲህ፡ ጌታችሁ፡ በምን ሰዓት እንደሚመጣ አታውቁምና፡ ትጉ!"* ሲል በፈጸመው ሕያው ቃሉ የሚጠቃለለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዝርዝር የነገራቸው፡ የኹለተኛው አመጣጡና የዓለሙ መጨረሻ ነገር፡ ዓቢይ ርእስ ኾኖ ይተረጎማል::[፻፴]

ገብር ኄር::

በጾመ አርብዓ፡ ከ"ደብረ ዘይት" ቀጥሎ ያለው፡ የእሑድ ሰንበትና የተያያዘው ሳምንት፡ "ገብር ኄር" ይባላል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለዳግም ምጽአቱና ስለዓለሙ መጨረሻ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ ማብራሪያውን ትምህርት ከሰጣቸው በኋላ፡ በዚያን ጊዜ የሚደርሰው ኹኔታ፡ ምንን እንደሚመስል፡ ለወንዶችም፤ ለሴቶችም፡ በቀላሉ ሊገባቸው በሚችል ቃል፡ መልእክቱን፡ በምሳሌዎች አጉልቶ ገልጾላቸው እንደነበር፡ ካለፈው፡ የምሥጢረ ትንሣኤ ውይይታችን ተረድታችኋል:: ጌታ፡ በእነዚያ ምሳሌዎቹ ውስጥ፡ ያ፡ ከባለገንዘቡ የተቀበላትን አንዲት መክሊት፡ ምንም ሳይሠራባት በመቅረቱ፡ *"አንተ ሃኬተኛ ክፉ ባርያ!"* ተብሎ የተዘለፈው አገልጋይ፡ ተፈርዶበት፡ ወደሥቃይ እንደተጣለ ተናግሩዋል::

በቅንነታቸውና በትጋታቸው፡ በታማኝነታቸውም፡ ብቁ የኾኑ፥ ለሌሎችም መልካም አርአያ ኾነው የተገኙ፡ ኹለት እና አምስት መክሊቶችን፡ ከባለገንዘቡ የተረከቡ ኹለት አገልጋዮች መኖራቸውንም አስቀድሞ አውስቷል:: ለእነርሱም፡ ለእያንዳንዳቸው፡ ከባለገንዘቡ ጌታ የተዋለላቸው፡ *"ወይቤሉ እግዚኡ፡ 'አ ገብር ኄር፥ ወምእመን! ዘበውኁድ፡ ምእመነ ኮንከ! ዲበ ብዙኅ እሠይመከ! ባእ ውስተ ፍሥሐሁ ለእግዚእከ!'"* ማለትም፡ *"ጌታውም፡ 'አንተ፡ የታመንህ፥ ደግ አገልጋይ! በጥቂት የታመንህ ስለኾንህ፡ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደጌታህ ደስታ ግባ!' አለው::"* የሚለው የሙገሳ በረከት ስለኾነ፡ ዕለተ እሑዱና ሳምንቱ፡ "ገብር ኄር" ተብሏል::

በዳግም ምጽአቱና በዓለሙ ፍጻሜ ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ እንዲገቡባትና እንዲወርሷት፡ ለሚያምኑባት ሳይቀር፡ ራሷን፡ ስለምታቀርብበትና የመጨረሻውን ዕድል ስለምትሰጥበት ኹኔታ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ምሳሌ፡ በቅድሚያ፡ ለሴቶቹ የሚኾነውን ነበር፤ እርሱም፡ *"አሜሃ፡ ትመስል መንግሥተ ሰማያት፡ ዐሥሮን ደናግለ፥ እለ ነሥኣ መኃትዊሆን፤ ወወፅአ ውስተ ቀበላ መርዓዊ፤ ወኀምስ እምውስቴቶን አብዳት እማንቱ፤ ወኀምስ ጠባባት::"* ማለትም፡ *"ያን ጊዜ፡ መንግሥተ ሰማያት፡ መብራታቸውን ይዘው፡ ሙሽራን ለመቀበል፡ የወጡ፡ ዐሥሩን ደናግል፡ ትመስላለች፤ ከእነርሱም ውስጥ፡ አምስቱ፡ ሰነፎች፥ አምስቱ፡ ልባሞች ናቸው::"* በሚል ቃል ይጀምራል::

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል።

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።

### የአጽዋማት ሰንበታት፡- ገብር ኄር።

---

ሰነፎቹ ደናግል፡ እንደልባሞቹ ደናግል፡ ከሙብራታቸው ጋር፡ በማሰሮቻቸው፡ ዘይት ባለመያዛቸውና ላለቀባቸው ዘይት መተኪያውን ሊገዙ በመኼዳቸው፡ ዘግይቶ፡ በእኩለ ሌሊት የመጣውን ሙሽራ፡ መብራታቸውን አብርተው ለመቀበል ስላልቻሉ፡ የሠርጉ ቤት ደጃፍ፡ በእነርሱ ላይ ተዘግቶባቸው፡ በውጭ ሲቀሩ፡ ልባሞቹ ግን ሊገቡ መቻላቸውን፡ ምሳሌው፡ እንዲህ በሚል ብርቱ የማስጠንቀቂያ ቃል ይደመድማል፡- "እንዲሁ፡ እናንተ ደግሞ፡ በመጨረሻው የፍርድ ሰዓት፡ ይህን የመሰለው ጽዋ እንዳይደርስባችሁ፡ *"ትጉሁኬ፡ እስመ ኢተአምሩ፡ ዕለታ፡ ወሰዓታ፡ እንተ ባቲ ይመጽእ ወልደ እጓለ እመሕያው!"* ማለትም፡ *"እንግዲህ፡ የሰው ልጅ የሚመጣበትን ዕለቷንና ሰዓቷን አታውቁምና፡ ነቅታችሁ፡ ተግታችሁ ጠብቁ!"*

ለወንዶቹ የሚኾነውንም ምሳሌ፡ እንዲህ ሲል፡ በማከታተል አቅርቦታል፡- *"እስመ ከመ ብእሲ፡ ዘይነግድ፡ ወጸውዐ አግብርቲሁ፡ ወመሀቦሙ ንዋዮ ይትገበሩ ቦቱ። ቦ፡ ለዘመሀቦ፡ ኀምስተ መክሊተ፡ ወቦ፡ ለዘክልኤ፡ ወቦ፡ ለዘአሐደ፡ ወለለአሐዱ እምኔሆሙ፡ በአምጣነ ይክሉ ወሀቦሙ፡ ወነገደ በጊዜሃ። ...ወእምድኅረ ብዙኅ መዋዕል፡ አተወ እግዚኦሙ፡ ለእልኩ አግብርት፡ ወተሐሰበ ምስሌሆሙ፡"* ማለትም፡ በዚያን ጊዜ፡ መንግሥተ ሰማያት፡ *"ባላቴናዎቹን (አገልጋዮቹን) ጠርቶ፡ ያተርፉበት ዘንድ፡ ገንዘቡን፡ ከእነርሱ፡ ለእያንዳንዳቸው፡ በሚችሉት መጠን፡ ላአንዱ፡ አምስት መክሊት፡ ለአንዱ፡ ኹለት፡ ለአንዱ፡ አንድ ሰጥቶ፡ ወዲያው፡ ወደመንገድ እንደኼደው ሰው ነው፡"* ሲል ይጀምራል፤

እያይዞም፡ *"...ከብዙ ዘመን በኋላ፡ የእነዚያ አገልጋዮች ጌታ፡ ከኼደበት ተመልሶ፡ ተሳሰባቸው።"* ይልና፡ ኹለትና አምስት መክሊት የተቀበሉት አገልጋዮች፡ እያንዳንዳቸው፡ ዕጥፍ ዕጥፍ አትርፈው፡ ለባለገንዘቡ ጌታቸው በማስረከባቸው፡ በምርቃት ተሞግሰውና በክብር ተሹመው፡ በማዕርግ ተሸልመውና ባለሟልነትን አግኝተው፡ ወደዘለዓለማዊው የደስታ ሕይወት ሲገቡ፡ ያ፡ *"አንዲት መክሊትን የተቀበለው፡"* አገልጋይ ግን፡ ከጌታው ፊት ቀርቦ፡ *"ስለፈራሁህ፡ መሬት ቆፍሬ፡ ወርቅህን፡ በምድር ውስጥ ቀበርሁ፤ ገንዘብህም፡ እነሆ ገንዘብህ!"* አለው። *"ጌታውም መልሶ፡ ...ከዚያ ላሉት አገልጋዮቹ፡ ያህን መክሊት፡ ከእርሱ ተቀብላችሁ፡ ዓሥር መክሊት ላለው ስጡት! ...ከፉውን ሀኬተኛ ባርያ ግን፡ ወደውጭ አውጥታችሁ፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በአለበት፡ በጨለማ ወህኒ ቤት አግዙት!' አላቸው።"* በሚለው አስፈሪ የኰነኔ ቃል ይደመድማል።

በሴቶቹ ምሳሌ ውስጥ፡ በሙሽራ የተመሰለው፡ በወንዶቹም ምሳሌ ውስጥ፡ "ባለገንዘቡ ጌታ" የተባለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲኾን፡ በዓሥሩ ልባሞችና ሰነፎች ደናግል፤ እንዲሁም፡ በታማኞቹ ደጋግ አገልጋዮችና በሃኬተኛው ክፉ ባርያ የተመሰልነው፡ እኛ፡ ወንዶቹና ሴቶቹ፡ ማለትም፡ እናንተና እኔ መኾናችን፡ ለማንም ግልጽ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እያንዳንዳችን፡ በየትኛው ወገን ተመድበን እንዳለን እንናገር ዘንድ፡ በእየራሳችን፡ ለእያንዳንዳችን ለሚቀርብልን ጥያቄ፡ እያንዳንዳችን፡ ለእየራሳችን የምንሰጠው፡ ፈጣሪያችንና እየራሳችን የምናውቀው፡ የእየራሳችን መልስ፡ ምን፡ ወይም፡ የትኛው ዓይነት እንደኾነ፡ በትክክልና በእርግጠኛነት ለይተን መግለጽ የምንችለውም፡ እግዚአብሔርና እያንዳንዳችን ብቻ ነን።

በዚች የ"ገብር ኄር" ዕለተ እሑድ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየተጠቀሱ ከሚነበቡትና ከሚሰሰሙት፡ ከሚሰበኩትና ከሚዘመሩት የእግዚአብሔር ቃላት መካከል፡ *"አፉሁ ለጻድቅ፡ ይትሜሃር ጥበበ፡ ወልሳኑ፡ ይነብብ ጽድቀ፡ ወሕገ አምላኩ፡ ውስተ ልቡ።" ማለትም፡ "የእውነተኛ ሰው አፍ፡ ጥበብን ያስተምራል፡ አንደበቱም፡ እውነትን ይናገራል፡ የአምላኩ ሕግ፡ በልቡ ውስጥ ነው።"* የሚለው፡ የነቢዩ የምስባክ ጥቅስ ይገኛል።[፳፱]

### ኒቆዲሞስ።

**"ኒቆዲሞስ"፡ በጾመ አርብዓ፡ ከ"ገብር ኄር" ቀጥሎ ላለው፡ የእሑድ ሰንበትና ለተያያዘው ሳምንት፡ የተሰጠ ስያሜ ነው።**

*"በሌሊት፡ ወደጌታችን ኢየሱስ መጥቶ፡ 'መምህር ሆይ! እግዚአብሔር፡ ከእርሱ ጋር ከኾነ በቀር፡ አንተ የምታደርጋቸውን፡ እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና፡ መምህር ኾነህ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን።"* ብሎ የመሰከረውን፡ ከፈሪሳውያን ወገን፡ የአይሁድ አለቃና መምህር፡ የሸንጎቻቸውም አባል የኾነውን፡ "ኒቆዲሞስ" የተባለውን ሰው ለማዘከር፡ ይህች ሰንበተ ክርስቲያን፡ ከስሙና ጋር፡ በዚህ ጻድቅ ስም እንድትታወቅ ኾናለች።

በእርሷም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚሁ፡ በኒቆዲሞስ፡ የምስክርነት ቃል መነሻነት፡ ማናቸውም ሰው፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፡ ከሥጋዊው ልደቱ በላይ፡ በይበልጥ፡ ከእግዚአብሔር፡ እንደገና በመወለድ፡ መንፈሳዊ ልደት እንደሚያስፈልገው የገለጸበትና ለሰው ልጆች፡ ታላቅ ድኅነት የተገኘበትን፡ መለኮታዊ እውቀት፡ በሰፊው ዘርዝሮ ያስረዳበት፡ የምሥጢረ ጥምቀት ነገር፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየተጠቀሰና እየተተረጐመ፡ ይነገርባታል፡ ይሰማባታል፤ ይሰበክባታል፡ ይዘመርባታል።

ከእነዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች መካከል፡ ከዚህ የሚከተሉት ይገኛሉ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፡ በቅድሚያ፡ ከወላጆቹ ካገኘው፡ ከሥጋው ልደት ቀጥሎ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ መወለድ የሚያስፈልገው መኾኑን፡ ለኒቆዲሞስ፡ ምሥጢሩን፡ በተፈጥሮ ምሳሌዎች ማስረጃነት እያብራራ ገልጸለት እንደነበረ፡ ካለፈው የምሥጢረ ጥምቀት ውይይታችን ተረድታችሁታል።

## ምዕራፍ ፮፣ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### የአጽዋማት ሰንበታት፡- ኒቆዲሞስ።

ኒቆዲሞስ፡ ከጌታችን ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ፡ በጥምቀት ስለሚገኘው ኹለተኛ ልደት፡ ምሥጢሩ ገብቶት ሊቀበለው ስላዳገተው፡ "እፎ ይትከሃል፡ ዝንቱ ይኩን?" ማለትም፡ "ይህ ሊኾን፡ እንደምን ይቻላል?" እያለ፡ መላልሶ መጠየቁን ታስታውሳላችሁ። ለዚህ፡ ተደጋጋሚ ጥያቄው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ምላሽና፡ አክሎ ያስተማረው፡ የአዲስ ኪዳኑ የምሥራች ቃል፡ እንዲህ የሚል ነበረ፡- "በምድር ያለውን ስነግራችሁ፡ ካላመናችሁኝ፡ በሰማይ ያለውን ብነግራችሁ፡ እንደምን ታምኑኛላችሁ? በሰማይ ከሚኖረው፡ ከእርሱ፡ ከሰማይ ከወረደው፡ ከሰው ልጅ በቀር፡ ወደሰማይ የወጣ የለም። ሙሴ፡ በምድረ በዳ፡ እባቡን እንደሰቀለው፡ የሰው ልጅም እንዲሁ፡ የመነበት ኹሉ፡ ለዘለዓለም፡ ሕይወት ኖሮ እንዲኖር እንጂ እንዳይጠፋ፡ ይሰቀል ዘንድ አለው። እግዚአብሔር፡ የመነበት ኹሉ እንዳይጠፋ፡ የዘለዓለም ሕይወትንም እንዲያገኝ፡ አንድ ልጁን፡ ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ፡ ዓለሙን፡ እንዲሁ ወድዶታል። እግዚአብሔር፡ በእርሱ፡ ዓለሙን ሊያድነው ነው እንጂ፡ ዓለሙን ሊፈርድበት፡ ልጁን ወደዚህ ዓለም አላከውምና፡ በእርሱ የመነ፡ አይፈረድበትም፡ በእርሱ ያላመነ ግን፡ በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፡ ፈጽሞ ይፈረድበታል።

"ብርሃን፡ ወደዓለም መጥቷልና፡ ሰውም፡ ሥራው ክፉ ስለኾነ፡ ከብርሃን ይልቅ፡ ጨለማን ወድዷልና፡ ፍርዱ ይህ ነው። ሥራው ክፉ የኾነ ኹሉ፡ ብርሃንን ይጠላል፡ ሥራው ክፉ ስለኾነም፡ እንዳይገለጥ፡ ወደብርሃን አይመጣም፡ እውነትን የሚሠራ ግን፡ ስለእግዚአብሔር ብሎ ይሠራልና፡ ሥራው ይገለጥ ዘንድ፡ ወደብርሃን ይመጣል።"

በዚህ ዕለተ እሑድና ሰሞን ከሚደመጠው ከዚህ፡ ከአዲስ ኪዳኑ ምንባብ ጋር፡ ከነቢያቱ ቃል፡ "ሐወጽከኒ ሌሊተ፡ ወፈተንከ ለልብየ፡ አመከርከኒ፡ ወኢተረክበ ዓመፃ በላዕሌየ፡ ከመ ኢይንብብ አፉየ፡ ግብረ እጓለ እመሕያው።" ማለትም፡ "በሌሊት ጐበኘኸኝ፡ ልቦናዬንም፡ መረመርህ፡ በመከራም፡ ፈተንኸኝ፤ ዓመፅን ግን፡ አላገኘህብኝም፤ አንደበቴ፡ የሰውን ሥራ እንዳይናገር፡ ፈቃዴ ነው።" የሚለው፡ የብሉይ ኪዳኑ፡ የምስባክ መዝሙር አብሮ፡ ተጠቅሶ ይዘመራል።

## ሆሣዕና።

በጾመ አርብዓ፡ ከ"ኒቆዲሞስ" ቀጥሎ፡ ከ"ትንሣኤ" በፊት ያለውና ከ"ሕማማት" ሰኞ ጋር የተያያዘው የእሑድ ሰንበት፡ "ሆሣዕና" ተብሎ ተሠይሟል።

በዚህ ዕለት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት ተነግሮለት፡ ሱባዔ ተቆጥሮለት፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት የመጣው መሢሕ፡ እርሱ መኾኑ፡ በይፋ ተረጋግጦበታል። ይኸውም፡ ጌታ፡ በደቀ መዛሙርቱና በሕዝቡ፡ በሕፃናቱ አንደበት ሳይቀር፡ "ሆሣዕና በአርያም!" እየተባለ፡ በአህያ ላይ ተቀምጦ፡ በታላቅ አጀብ፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ በገባበት ትዕይንት የታየውና የኾነው ድንቅ ነገር ነው።

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚያ ትዕይንተ ሕዝብ፡ ለውድድር አሸናፊዎችና ለዘመቻ ድል አድራጊዎች የሚቀርበው የዘንባባ ዝንጣፊ ተይዞ እየተውለበለበለትና ተበትኖ እየተነጠፈለት፡ *"በልዋ ለወለተ ጽዮን! ነዋ ንጉሥኪ፡ ጻድቅ፡ ወየዋህ፡ ይመጽእ ኀቤኪ፡ እንዘ ይጼዐን ዲበ እድግት፥ ወዲበ ዕዋላ!"* ማለትም፡ *"የጽዮንን ልጅ፡ 'እነሆ፡ ጻድቅ፥ የዋህ ንጉሥሽ፡ በአህያዪቱና በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ፡ ወደአንቺ ይመጣል!' በሏት።"* የሚለውም የነቢያት ቃል፡ በእርሱ መፈጸሙን በማሳየት፡ በሠረገላ ሳይኾን፡ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ፡ ወደኢየሩሳሌም የገባው፡ በዚሁ ዕለት መኾኑ ይዘከራል።

የ"ሆሣዕና" በዓል፡ በተለይ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ የጠለቀና የመጠቀ፡ የረቀቀና የገዘፈ፡ እማናዊ ትርጉምና ሕይወታዊ መልእክት አለው፡ ይኸውም፡ በዚያች ዕለተ ሆሣዕናና ከዚያች ቀን ጀምሮ፡ እኛ፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረግነውና አኹንም እያደረግን ያለነው ሆሣዕናዊ አቀባበል፡ እግዚአብሔር በሚያየውና በሚወድደው፡ የ"እውነት መንፈስ" ኾኖ፡ እስከዛሬ፡ በዚያው የቀጠለ ሲኾን፡ በአይሁድ ዘንድ የነበረውና አኹንም ያለው አቀባበል ግን፡ በ"ሓሰት መንፈስ" ኾኖ፡ እስከዛሬም፡ በዚያው የቀጠለ መኾኑ፡ ይኸው በግልጽ እየታየ በመረጋገጥ ላይ ይገኛል።

አዎን! አይሁድ፡ በካህናትና በሕዝብ አለቆቻቸው ምክር፡ በዚያች የ"ሆሣዕና" ቀንና ከእርሷ በኋላ፡ እስከትንሣኤው ሌሊት ባለው፡ መላው ሳምንትና እስከዛሬ በእርሱ ላይ፡ ያለማቋረጥ የቀጠሉት፡ የጥላቻና የጭካኔ ግብራቸው፡ እያጋለጣቸው እንደሚገኝ፡ ይኸው በገሃድ ይታያል። ኢትዮጵያውያን ግን፡ ያ፡ ስለእርሱ፡ በነቢያቱ የተነገረውና በብሉያቱ የተጻፈው ቃል ኹሉ፡ በዚያች ዕለትም ኾነ፡ ከዚያ በፊት፥ ከዚያም በኋላ፤ እስከዛሬና ወደፊትም፥ ለዘለዓለምም፡ ለእርሱ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ደርሶ፥ በእርሱ የተፈጸመ መኾኑን አምነው፡ ይኸው፡ በእርሱ ንጉሥነትና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ንግሥትነት በምትመራው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር እየተዳደሩ ይኖራሉ።

ይህም፡ እኒሁ ኢትዮጵያውያን፡ በየዓመቱ፡ በዕለተ ሆሣዕና፡ ስለበዓሉ ከሚያካኺዱት፡ ከሃይማኖታዊውና ከምግባራዊው፡ ከጸሎቱና ከማኅሌቱ፡ ከቤተሰባዊውና ማኅበራዊው ሥርዓት ጋር፡ *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር"* እና *"ምዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚሉትን፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት፡ ብሔራዊና መንግሥታዊ ማኅተማቸው አድርገው፡ በሀገራዊውና በሕዝባዊው ሰንደቅ ዓላማቸውም ላይ አሥፍረው፡ እነሆ፡ በሕያውነት፡ ለዝንተ ዓለም፡ በይፋ ሲጠቀሙባቸው በመኖራቸው፡ ተረጋግጦ ታውቋል። **የሆሣዕናው በዓል፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚከበረው፡ በአይሁድ ዘንድ ተደርጎ በነበረው፡ በ"ሓሰት መንፈስ" እና "የሓሰት አባት በኾነው፡ በዲያብሎስ አምልኮ" ሳይኾን፡ እንዲህ፡ እግዚአብሔር በሚያየውና በሚወድደው፡ በ"እውነት መንፈስ" እና "ራሱ እውነት በኾነው፡ በወልደ አብ ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ አምልኮ" ነው።**

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል፡፡
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት፡፡
## ሆሣዕና፡፡

"ማኅትወ ሰንበት ዘሆሣዕና" ወይም፡ "ሠርክ ሰንበት ዘሆሣዕና እሑድ" በምትባለው፡ በሆሣዕና በዓል ዋዜማ፥ ማለትም፡ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት፡ ካህናቱ፡ በሠርክ ሰዓት ላይ (ወደምሽቱ ግድም)፡ በሚቆሙት ማኅሌት፡ የበዓሉን ሥርዓተ ጸሎት፡ ይጀምራሉ፡፡ ያም ሥርዓተ ጸሎት፡ ኢትዮጵያዊው ካህንና ማኅሌታይ፡ ቅዱስ ያሬድ፡ "በእምርት ዕለት በዓልነ፤ ንፍኑ ቀርነ፡ በጽዮን፡ ወስብኩ፡ በደብረ መቅደስየ፡፡ እስመ ይቤ፡ 'ዛቲ ዕለት፡ በዓለ እግዚአብሔር፡' ሆሣዕና በአርያም! ቡሩክ አንተ፡ ንጉሠ እስራኤል!" ማለትም፡ "ተአምር በታየባት በበዓላችን ቀን፡ በጽዮን፡ ቀንደ መለከቱን ንፉ! በመቅደሴ ተራራም ላይ ስበኩ! 'ይህች ዕለት፡ የእግዚአብሔር በዓል ናት፤' ይላልና፡፡ ሆሣዕና በአርያም! የእሥራኤል ንጉሥ አንተ፡ ቡሩክ ነህ!" ሲል፡ በደረሰው የዝማሬ ቃልና በቃኘው ጥዑም ዜማ እየታጀበ ይቀጥላል፡፡

ቅዱስ ያሬድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ፡ ይህን የምስጋና በረከት የደረሰው፡ "እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም!"፥ "ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ!"፥ "ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ!" ማለትም፡ "በንጉሥነቱ አምላኩ፡ በአምልኮ ለሚሰግዱለትና በእውነት ለሚገዙለት፥ እርሱም፡ ምግባቸውን አትረፍርፎ ለሚሰጣቸው፡ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧማ፡ እግዚአብሔር፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አንሥቶ፡ ምንጊዜም ንጉሣቸው ነው!" የሚለውን፡ የነቢዩን፡ የቅዱስ ዳዊትን መዝሙር መሠረት አድርጎ፡ "ዛሬም፡ እውነተኞቹ እሥራኤል ለኾንነው፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ንጉሣችን መኾንህን፡ በገሃድና በይፋ ታሳውቅ ዘንድ፡ እንደነቢያቱ ቃል፡ እንዲህ ተገልጸህ መጣህ!" ለማለት መኾኑን እንድታስተውሉት ያስፈልጋል፡፡

የሆሣዕና እሑድንም ሌሊት፡ "ወእንዘ ሰሙን፡ በዓለ ፋሲካ፡ ቀርቡ አርዳኢሁ፡ ለአምላክ ጽድቅ፡ ኀበ ደብረ ዘይት፡ ሙራደ ዐቀብ፡ ሀገረ እግዚአብሔር፡፡ ወተቀበልዎ፡ ሕዝብ ብዙኃን፥ አዕሩግ ወሕፃናት፤ ነሢኦም፡ አዕጹቀ በቀልት፤ እንዘ ይብሉ፡ 'ሆሣዕና በአርያም!' ተጽዒኖ ዲበ ዕዋል፤ ቦአ ሀገረ ኢየሩሳሌም፥ በትፍሥሕት፥ ወበሐሤት፤ ይሁቦሙ፡ ኃይለ፥ ወሥልጣነ፡፡" ማለትም፡ "የእውነት አምላክ [ኢየሱስ ክርስቶስ]፡ የፋሲካ በዓል በሚከበርባት ሳምንት ዋዜማ፡ የእግዚአብሔር አገር ወደኾነችው፡ 'ደብረ ዘይት' ወደምትባለው፡ የወይራ ዛፍ ተራራ ቍልቍለት ላይ በደረሰ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ ወደእርሱ ቀረቡ፤ ብዙ ሕዝብ፥ ታላላቆችና ሕፃናትም ተቀበሉት፤ እነርሱም፡ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘውና 'ሆሣዕና በአርያም!' እያሉ፡ አጅበውት፡ ኃይልና ሥልጣን የሚሰጣቸው እርሱ፡ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ፡ በታላቅ ደስታ፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ ገባ፡፡" በሚለው ያሬዳዊ መዝሙር ቀጥለው፡ ማኅሌቱ፡ በፍጹም ተመስጦና አንቃዕድዎ (ፊጣሪን በማሰብ) ደምቆ ያድራል፡፡

በነግህ፡ የቍርባን ሥርዓተ ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት፡ ማኅሌታውያኑ መዘምራን፡ "'ሆሣዕና በአርያም!' እየተባለ፡ በዕለተ ሆሣዕና፡ ወደኢየሩሳሌም የገባው፡ አማናዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህ ነው!" በማለት፡ መሥዋዕቱን፡ ከቤተ ልሔም ይዘው የሚመጡትን፡ ቀዳስያኑን ካህናት አጅበው፡ ኹሉም፡ በአንድነት፡ በቤተ ክርስቲያኑ የምዕራብ ደጃፍ አንጻር ይቆማሉ፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*በመሪጌታው መሪነት፡ ማኅሌታውያኑ፡ “ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ! ባኡ ውስተ ሀገር! መበዊአክሙ፡ ትረክቡ ዕዋለ አድግ እሡረ፤ ፍትሕዎ፥ ወአምጽእዎ ሊተ።” ደግሞም፡ “ሃሌ ሉ.ያ! አልጺቆ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም፡ ርእየ ለሀገር፤ ወይቤላ፡ 'ሶበ ተአምሪ ጽዮን! ነዋ ንጉሥኪ! በጽሓ ብርሃንኪ! ዮም ሰላምኪ! ተፈሥሒ በሕዝብኪ! ይትነፈሩ ጸላእትኪ! ዮም ሰላምኪ! ሰላምኪ ዮም፡ ሰላምኪ!'” ማለትም፡ “ለሀልውናህ፡ ጥንት፡ ፍጻሜ ለሌለህ፡ ለአንተ፡ ምስጋና ይገባሃል! ወደከተማ ግቡ! ስትገቡም፡ የታሠረ የአህያ ውርንጯን ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁም፡ አምጡልኝ፤”*

*“ጌታችን ኢየሱስ፡ ኢየሩሳሌም ሊደርስ ሲቃረብ፡ ከተማዪቱን አይቶ፡ 'ጽዮን ሆይ! አውቀሽ ብትቀበዪው፡ ንጉሥሽ፡ ይኸውልሽ! ብርሃንሽ፡ መጣልሽ! ሰላምሽ፡ ዛሬ ነው! በሕዝብሽ ደስ ይበልሽ! ጠላቶችሽ ይፈሩ! ሰላምሽ፡ ዛሬ ነው! አዎን፡ ዛሬ፡ የሰላምሽ ቀን ነው!'”* የሚለውን መዝሙር፡ እየተቀባበሉ ያዜማሉ።

ከዚህ በኋላ፡ የቤተ ክርስቲያኑ የምዕራብ ደጃፍ እንደተዘጋ፡ ከውጭ፡ ፍሬ ሰሞነኛው ዲያቆን፡ በመሶበ ወርቅ ያኖረውን፡ የመሥዋዕቱን ኅብስተ አኰቴት፡ በራሱ ላይ እንደተሸከመ፥ ሠራዒው ዲያቆንም፡ የቁርባኑን የወይን ጽዋ እንደያዘ፡ በመካከል ቆሞ፡ *“አርኅው ኆኃተ መኳንንት! አርኅው ኆኃተ መኳንንት! አርኅው ኆኃተ መኳንንት!”* ማለትም፡ *“እናንተ መኳንንት! ደጃፎችን ክፈቱ!”* የሚለውን ቃል፡ ከመዝሙራቱ ጠቅሶ፡ በዕዝል ዜማ፡ ለ፫ ጊዜያት ያሰማል። ዋናው ቀዳሽ ካህንም፡ ከመቅደሱ ውስጥ ኾኖ፡ *“መኑ ውእቱ ዝንቱ፡ ንጉሠ ስብሓት! መኑ ውእቱ ዝንቱ፡ ንጉሠ ስብሓት! መኑ ውእቱ ዝንቱ፡ ንጉሠ ስብሓት!”* ማለትም፡ *“ክብር ምስጋና የሚገባው፡ ይህ ንጉሥ፡ ማነው?”* እያለ በመጠየቅ፡ ከዚያው፡ ከመዝሙራቱ የሚጠቀሰውን ቃል፡ በዕዝል ዜማ፡ ለ፫ ጊዜያት እያሰማ ይመልስለታል።

በ፫ኛው ጊዜ፡ ዲያቆኑ፡ በዚያው የዜማ ስልት፡ *“እግዚአብሔር፡ አምላከ ኃያላን፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ንጉሠ ስብሓት!”* ማለትም፡ *“ክብር ምስጋና የሚገባው፡ ይህ ንጉሥ፡ የኃያላን አምላክ፡ እግዚአብሔር ነው!”* የሚለውን ቃል፡ ለ፫ ጊዜያት በማሰማት፡ ምላሹን ይሰጠዋል።

በመጨረሻ፡ ካህኑ፡ በልዩ የወረብ ዜማ፡ *“ይባእ ንጉሠ ስብሓት! ይባእ አምላከ ምሕረት!”* ማለትም፡ *“የምስጋናው ንጉሥ፡ ይግባ! የምሕረቱ አምላክ፡ ይግባ!”* እያለ፡ የቤተ ክርስቲያኑን ደጃፍ ይከፍተዋል። በዚህ ጊዜ፡ ቀዳስያኑም፥ መዘምራኑም፥ ካህናቱም፥ ሕዝቡም ኹሉ፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነውን መሥዋዕቱንና ቍርባኑን እንዳጀቡ፡ በኅብረት፡ ይህንኑ ዝማሬ፡ እያሰሙ፡ ወደቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ይዘልቃሉ፤ ከመቅደሱ በር ሲደርሱም፡ ቀዳስያኑ፡ ወደቅድስተ ቅድሳቱ ይገባሉ፤ መዘምራኑም፡ ወደቅኔ ማኅሌታቸው ይመለሳሉ።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### ሆሣዕና።

---

የሥርዓተ ቅዳሴው ጸሎት አልቆ፡ ወደፍሬ ቅዳሴው ከመግባታቸው በፊት፡ ለበዓሉ ከተመደቡት፡ ከአዲስ ኪዳኑ መልእክታት ምንባቦች በኋላና ከምሥራቹ (ከወንጌሉ) የአዋጅ ቃል ንባብ አስቀድሞ፡ ከብሉዩ ኪዳን መዝሙራት መካከል ተጠቅሶ የሚዘመረው ምስባክ፡ *"ቡሩክ ዘይመጽእ፡ በስመ እግዚአብሔር፡ ባረክናክሙ፡ እምቤተ እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር እግዚእ፡ አስተርአየ ለነ።" ማለትም፡ "በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ፡ ቡሩክ ነው፡ በእግዚአብሔር ቤት ኾነን፡ መረቅናችሁ፡ ጌታ እግዚአብሔር፡ ለእኛ ተገለጠ።"*[፻፲፯] የሚለው ነው።

## ትንሣኤ/ፋሲካ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባትን፡ የመታሰቢያ ዕለት፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በጥልቅ መንፈሳዊ የደስታ ስሜት እናከብራታለን። ይህም፡ ያለምክንያት አይደለም፡ ይህችው ዕለት፡ ፈጣሪ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዓላማ፡ ከግብ አድርሶ የፈጸመባት፡ ማለትም፡ የሰው ልጆችን የዘር ጠላቶች ደምስሶ፡ ለእኛ፡ ዘለዓለማዊ ድልን ያቀዳጀባት፡ ይኸውም፡ ከዲያብሎስ የአገዛዝ ባርነት አውጥቶ፡ ለእግዚአብሔር ነጻ ልጅነት፡ የኃጢአትን ቀንበር አስወግዶ፡ ለንስሓ ጽድቅ፡ የሞትን ፍዳ አጥፍቶ፡ ለዘለዓለም ሕይወት ጸጋ እንድንበቃ ያደረገባት ቀን በመኾኗ ነው።

"ፋሲካ" እየተባለ የሚጠራው፡ የትንሣኤ በዓል፡ በአገራችን በኢትዮጵያና በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከሌሎቹ በዓላት ይልቅ፡ እጅግ ጥልቅ በኾነ፡ የተለየ ሃይማኖታዊ ስሜትና ታሪካዊ ይዘት ይከበራል፡ አከባበሩም፡ ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ፡ በኹለት በተያያዘ ደረጃና መልክ ሲካኼድ ኖርዋል፡ ይኸውም፡-

፩ኛ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንቱኑ፡ ለአዳምና ሔዋን በሰጠው የተስፋ ቃሉ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ በአዲሱ ኪዳነ ምሕረት፡ እውነተኛው የፋሲካ በግ በመኾን፡ በመስቀል ላይ ከመሠዋቱ በፊት፡ ለዚያ፡ ለመጨረሻውና ለዘለዓለማዊው የሰው ልጆች ደኅንነት፡ መሸጋገሪያና ጥላ የኾነ የይቅርታ ቸርነቱን፡ በኪዳነ ኦሪቱ፡ ቀደም አድርጎ፡ ለእሥራኤል ልጆች በሠራው የፋሲካ ሥርዓት ሲሰጥ መቆየቱ ነው።

ያም ሥርዓት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ ከፈርዖን የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ ያወጣቸው ዘንድ፡ ሙሴን፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደግብፅ በላከው ጊዜ፡ በአንዲት አስደንጋጭ ሌሊት ከደረሰው ታላቅ መቅሠፍት የተገኘ ነበር፤ አዎን! ጣዖት አምላኪው ፈርዖን፡ እሥራኤላውያኑን ነጻ ይለቅቃቸው ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በሙሴ አማካይነት፡ በአገሩ ላይ፡ የተለያየ መዓትን አከታትሎ ቢያወርድበትም፡ እምቢተኛ ልቦናውን ይበልጥ በማደንደን፡ መለኮታዊዉን ትእዛዝ ተቀብሎ ለመፈጸም ፈቃደኛ አልኾነም።

ካለመፍቀዱም የተነሣ: በመጨረሻ: በየቤተሰቡ የተወለዱትን: ከሰው እስከእንስሳ ድረስ ያሉትን: የግብፃውያንን የበኩር (የመጀመሪያ) ልጆች ኹሉ የሚቀሥፍ መልአከ ሞት መጥቶ: የፈርዖን ዐልጋ ወራሽ በኾነው በኩር ላይ ሳይቀር: የግድያ ግዳጁን ከፈጸመበት መቅሠፍት የተገኘው ሥርዓት ነው::

በዚያን ጊዜ ግን: የእሥራኤል የበኩር ልጆች: ከዚያ የሞት መቅሠፍት የሚድኑበትን መንገድ: እግዚአብሔር አዘጋጅቶ ነበር፡ ይኸውም: ቀሣፊው መልአከ ሞት: በእያንዳንዱ የእሥራኤል ቤተሰብ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳያደርስ: የደም ምልክትን ብቻ እያየ: በሰላም ያልፍ ዘንድ: ለዚያ ቤተሰብ ቤዛ የሚኾን: የመሥዋዕት በግ: በዚያ ቤተሰብ ታርዶ: የዚያ በግ ደም: በዚያው ቤተሰብ የመኖሪያ ቤት በር: ኹለት መቃኖችና ጉበን ላይ: ለምልክትነት እየተረጨ እንዲቀባ: የዚያም ቤተሰብ አባሎች: የዚያን በግ: አጥንቱን ሳይሰብሩ: ሥጋውን ብቻ እየጠበሱ: በዚያው ሌሊት ጨርሰው እንዲበሉት: እግዚአብሔር: በሙሴ አማካይነት: ለእሥራኤል ልጆች የሰጣቸውና እነርሱም: ተቀብለው የፈጸሙት ትእዛዝ ነው::

በዚያች ሌሊት: በግብፃውያን ላይ: ታላቅ ድንጋጤንና ፍርሃትን ያስከተለው የቁጣው መቅሠፍት: በእሥራኤላውያን ላይ ግን: ታላቅ ደስታንና ሓሤትን ያወረደው: ያ: የእግዚአብሔር የማዳኑና የማጥፋቱ: የምሕረቱና የመዓቱ ኃይል: "ፋሲካ" ተብሎ: በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ: በየዓመቱ ሲታሰብና ሲከበር የሚኖር የዘለዓለም ሥርዓት ኾነ::

፪ኛ. ይህ "የፋሲካ ሥርዓት": በኪዳን አሪቱ መሠረት: እንዲህ: በየዓመቱ ሲፈጸም ከኖረ በኋላ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: የፋሲካው በግ በሚታረድባት: በዚችው የፋሲካ ሌሊት: በመስቀል ላይ ራቁቱን ተሰቅሎ: ደሙን በማፍሰስ: እውነተኛውና ዘለዓለማዊው የፋሲካ በግ ኾኖ: ለአንደኛውና ለመጨረሻው ጊዜ መሠዋቱ ነው::

ስለፋሲካው በግ ሥርዓት: እግዚአብሔር: ለእሥራኤል ልጆች: በሰጠው መመሪያ ውስጥ: *"አጥንቱን አትስበሩ!"* ያለው: የመለኮት የትንቢት ቃል: በዓለም መድኃኒትነቱ: ራሱን: የመጨረሻው የፋሲካ በግ አድርጎ ለሠዋው: ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ መኾኑ: በወንጌላዊው ዮሓንስ ተጽፎ ይነበባል፤ ይኸውም: ጌታ የሚወድደውና ከሓዋርያት: አንዱ የኾነው: ይህ ዮሓንስ: ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር: ከጌታ መስቀል አጠገብ ቆሞ: በዓይኖቹ ባየው: የመሰከረው ነው:: አዎን! ከጌታ መስቀል: በቀኙና በግራው አብረው የተሰቀሉት ወንበዴዎች: ስላልሞቱ: ከመምሸቱ በፊት: ከተሰቀሉበት ሊያወርዷቸው: በዚያ የነበሩት ወታደሮች: የኹለቱንም ወንጀለኞች: ጭንና ጭናቸውን ሰበሩዋቸው፤ ጌታ ግን: ቀደም ብሎ: ነፍሱ: በሰዓቷ: ከሥጋው ስለተለየች: መሞቱን ለማወቅ: ከወታደሮቹ አንዱ: "ለንጊኖስ" የሚባለው: ቀኝ ጎኑን: በጦር ከመውጋቱ በቀር: ከአጥንቱ: አንዱንም ሳለመስበራቸው: ይኸው ዮሓንስ: በዚያ: የዓይን ምስክርነቱ በጻፈው: የምሥራች ዜናው አረጋግጦታል::

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል::

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::

## ትንሣኤ/ፋሲካ::

---

የምስክርነት ቃሉም፡ እንዲህ የሚል ነው:-"*አይሁድ ግን፡ 'መሽቷልና፡ የዚች ሰንበት ቀንም፡ ታላቅ ናትና፡ እነዚህ አስከሬኖች፡ ስለሰንበት፡ በየተሰቀሉበት አይደሩ!' አሉ፡ ጭን ጭናቸውንም ሰብረው ያወርዷቸው ዘንድ፡ ጲላጦስን ለመኑት:: ወታደሮችም መጥተው፡ አብረውት ተሰቅለው የነበሩትን፡ የመጀመሪያውን ወንበዴ ጭን፡ የኹለተኛውንም ሰበሩ:: ወደ ጌታችን ኢየሱስም ኼደው፡ ፈጽሞ እንደሞተ ባዩት ጊዜ፡ ጭኑን አልሰበሩም:: ነገር ግን፡ ከወታደሮች አንዱ፡ የቀኝ ጎኑን በጦር ወጋው፡ ያን ጊዜም፡ ከእርሱ፡ ደምና ውኃ ወጣ:: ያየውም መሰከረ፡ ምስክርነቱም፡ እውነት ነው፡ እናንተም ታምኑ ዘንድ፡ እርሱ፡ እውነትን እንደሚናገር ያውቃል:: ይህ ኹሉ የኾነው፡ ከእርሱ፡ 'አጥንቱን አትስበሩ!' የሚለው፡ የመጽሐፍ ቃል፡ ይደርስ፡ ይፈጸም ዘንድ ነው::*"

ያ የበጉ ደም፡ የእሥራኤልን የበኵር ልጆች፡ ከመቅሠፍና ከሥጋ ሞት እንዳዳነ፡ ይህም፡ "*ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፡ ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም፡*" ማለትም፡ "*የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር በግ*" የተባለው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ ተሠውቶ፡ ባፈሰሰው ደሙ፡ እኛን፡ ከኃጢአትና ከዘለዓለም ሞት አዳነን:: እኒያ፡ የእሥራኤል ሕዝብ፡ በዚያን ጊዜ የታረደውን በግ፡ ደሙን፡ በቤታቸው የውጭ ደጃፍ ላይ ረጭተው በመቀባትና ሥጋውን፡ በቤታቸው ውስጥ በልተው፡ ከሰውነታቸው ጋር በማዋሐድ፡ የዚያ ቀሣፊ መልአክ ሠይፍ፡ ካስከተለው ሞት እንደዳኑ ኹሉ፡ እኛም፡ ዛሬ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ቅዱስ ሥጋውን በልተንና ክቡር ደሙን ጠጥተን፡ ለኃጢአታችን፡[፬፻፲] የዘለዓለም ስርየትን፡ ለሰውነታችንም፡ የዘለዓለም ሕይወትን እናገኛለን::

ይህን የፋሲካውን ሥርዓት፡ እንዲህ፡ እንደኪዳን አሪቱ፡ በየቤታችን፡ እንደኪዳን ምሕረቱ ደግሞ፡ በቤተ ክርስቲያናችን የምንፈጽም፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ነን:: ይህም ማለት፡ በዚህ የትንሣኤ በዓላችን፡ ለአዲስ ኪዳኑ ፋሲካችን፡ መሥዋዕት ኾኖ ቀርቦ፡ እንድንበላውና እንድንጠጣው የታዘዝነው፡ ለሥጋ ምግብነት፡ በየቤታችን የታረደውን ፍሪዳና የተጠመቀውን መጠጥ ሳይኾን፡ ለኹለንተናችን የሕይወት ምግብ ይኾነን ዘንድ፡ ከሰማይ የወረደውንና ከምድር የተገኘውን፡ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው የፋሲካ በጋችን የኾነውን፡ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መኾኑን አውቀን፡ በየዓመቱ በምትመጣው፡ የትንሣኤ ሌሊት፡ የዚሁ አምላካዊ ጸጋና በረከት ተካፋዮች በመኾን፡ በፍጹም ሥጋዊ ደስታና መንፈሳዊ ሐሤት ልናከብራት ይገባል::

### የትንሣኤ ፍጹም ደስታና ሐሤት የሚገለጽበት ሥርዓት::

አዎን! እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚያች የትንሣኤ ሌሊት፡ እያንዳንዳችን፡ በኢትዮጵያዊነታችን የሚሰማን ሥጋዊ ደስታና መንፈሳዊ ሐሤት፡ እውነትም፡ በቃላት ሊገለጽ ከቶ አይቻልም::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህም የኾነውና የሚኾነው፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም፡ መሠረታዊና ጽኑ የኾነ ምክንያት አለ፡ ይኸውም፡ መስከረም ፩ ቀን በሚውለው፡ በእመቤታችን ድንግል ማርያም እና በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሚጀምረው፡ የእነርሱንም ፈለግ በመከተል፡ ከእነርሱ ጋር፡ በሥጋና በነፍስ፡ በመንፈስም አብረን ኾነን የምናደርገው፡ ዓመታዊው የሃይማኖት ጉዟችን፡ በአጽዋማቱ ሠረገላነትና በበዓላቱ ምዕራፍነት እየተጠናከረና እየታደሰ መጥቶ፡ በተለይ፡ ከዓቢይ ጾም እስከሕማማቱ ዕለተ ዓርብ ስቅለቱና ሞቱ ድረስ፡ በልዩው የጾም፡ የጸሎትና የስግደት ምግባሮቻችን አማካይነት፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከቅድስት እናቱ፡ በሥጋና በነፍስ፡ በመንፈስም ሳይለይ፡ አብሮ፡ ከእነርሱ ጋር ከተቀበረ በኋላ፡ በዚያች ሌሊት ከእናትና ልጁ ጋር አብሮ ስለሚነሣ ነው።

ያ፡ በቤት የሚቀጥለው ሥጋዊ ደስታ፡ ነፍሳዊ ተድላና መንፈሳዊ ሐሤት፡ በዚያች የትንሣኤ ሌሊት፡ በቅድሚያ፡ በቤተ ክርስቲያን በሚካኼዱት፡ የጸሎት፡ የማኅሌትና የቅዳሴ ሥርዓታት፡ ተገልጾ ይታያል። የትንሣኤው ሥርዓተ በዓል፡ ካህናቱና ምእመናኑ፡ የመቅደስ መስቀሉን እየተሳለሙና እንዲህ እያሉ፡ በጋለ የደስታ ስሜት፡ በቃል በሚለዋወጡት፡ የምሥራች አዋጅ ይጀመራል፡-

ካህኑ፡ "ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን!" ምእመኑ፡ "በዓቢይ ኀይል ወሥልጣን!" ካህኑ፡ "ዐሠሮ ለሰይጣን!" ምእመኑ፡ "አግዐዞ ለአዳም!" ካህኑ፡ እምይእዜሰ!" ካህኑና ምእመኑ (በኅብረት)፡ "ኮነ ፍሥሓ ወሰላም!" ማለትም፡ "ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! በታላቅ ኀይልና ሥልጣን! ሰይጣንን ዐሠረው! የሰውን ልጅ ነጻ አወጣው! ከዛሬ ጀምሮ፡ ደስታና ሰላም ኾነ!"

ደግመኛም፡ "ክርስቶስ፡ ተንሥአ እሙታን! ሞተ፡ ወኬዶ ለሞት! ለእለ ውስተ መቃብር፡ ወሀበ ሕይወተ፡ ዘለዓለም ዕረፍተ!" ማለትም፡ "ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! ሞቶም፡ ሞትን ድል አደረገው! በመቃብር ላሉትም፡ የዘለዓለም ዕረፍት የኾነውን ሕይወት ሰጣቸው!" የሚለውን የአዋጅ ቃል፡ በዜማ እየተቀባበሉና ታላቁን ምሥራች፡ በሐሤትና በይባቤ ድምፅ ያሰማሉ።

ከዚያም፡ ዲያቆኑ፡ ከዳዊት መዝሙር፡ "ወተንሥአ እግዚአብሔር፡ ከመ ዘንቃህ እምንዋም፡ ወከመ ኀያል፡ ወንዳገ ወይን፡ ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ።" ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ ከእንቅልፍ እንደሚነቃ፡ የወይን ስካርም እንደተወው ጀግና ተነሣ! ጠላቱንም፡ አሳድዶ ደመሰሰው!" የሚለውን፡ የበዓሉን መደበኛ ምስባክ፡ ለኹለት ጊዜያት፡ በሉዓላዊ ድምፅ ያዜማል፡ ካህናቱና ሕዝቡም፡ ከእርሱ ተቀብለው፡ ለሦስት ጊዜያት መላልሰው ያዜሙታል።[፻፳፬]

በቤተ መቅደሱ የሚካኼደው ሥርዓተ ጸሎት እንዳበቃ፡ የቅኔ ማኅሌቱ ሥርዓት፡ "ምልጣን" በሚባለው የድጓ ዜማ እንዲህ እያለ፡ በመዘምራኑ ይቀጥላል፡-

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት። ትንሣኤ/ፋሲካ።
### የትንሣኤ ፍጹም ደስታና ሐሤት የሚገለጽበት ሥርዓት።

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ! በሰንበተ ክርስቲያን፡ እስመ ተንሥአ ክርስቶስ እሙታን። ቀደሳ ወአክበራ እምኵሉን መዋዕል፡ አልዓላ፡ አማን፡ ተንሥአ እምነ ሙታን። ...ወዮምሰ ዓባይ ፍሥሓ በሰማያት፡ ወምድርኒ፡ ትገብር ፋሲካ፡ ተነሢአ በደመ ክርስቶስ። ...አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን፡ ተንሥአ እምነ ሙታን፡ ተንሥአ እምነ ሙታን።" ማለትም፡ "ዛሬ፡ በዚች ሰንበተ ክርስቲያን፡ ደስታ ኾነ! ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ተንሥቷልና። እርሷንም፡ ከዕለታቱ ኹሉ ይልቅ፡ ቀደሳት! አከበራትም! ከፍ ከፍ አደረጋት! አዎን፡ በእውነት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! ...ዛሬ፡ በሰማያት፡ ታላቅ ደስታ ኾነ! ምድርም፡ በክርስቶስ ደም ስለታጠበች፡ ፋሲካዋን ታደርጋለች። ...ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱ፡ እውነት ነው፡ አዎን፡ ክርስቶስ፡ በእውነት፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ!"*

በመጨረሻ፡ ማኅሌታውያኑ መዘምራን፡ "ትንሣኤከ ለእለ *አመነ! ብርሃንከ ፈኑ ዲቤነ!"* የሚለውን ወረብ ወርበው፡ በጸናጽልና በከበሮ ታጅበው እያሸበሸቡ፡ ካህናቱና ሕዝቡም፡ እየንዳንዳቸው፡ የጧፍ መብራትን ይዘው፡ በይባቤና በእልልታ፡ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ዑደት ያደርጋሉ።

ከዚህ በኋላ፡ ካህናቱም፡ ምእመናኑም፡ ይህን የትንሣኤ በዓላቸውን፡ አማናዊ የሚያደርጉበትን፡ አማናዊነቱንም፡ ለየራሳቸው፡ ለሰብእዊው ወገናቸውና ለፈጣሪያቸው የሚያረጋግጡበትን ሥርዓት ይፈጽማሉ፡ ይኸውም፡ በታላቅ መሥዋዕትነት ጠብቀውትና ሕያው አድርገውት ለኖሩበት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው፡ መታወቂያ ማኅተምና የህልውና ዘውድ የኾነው ሰማያዊው ግብር፡ በመላእክት ሥርዓት ተከኺዶ፡ በሚከናወነው የቅዳሴ ጸሎት፡ በተሰናዳበት፡ በቅዱሱ ገበታ ዙርያ ተሰባስበው መቅረባቸው ነው፤ ከዚያም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶና አማናዊው የፋሲካ በግ ኾኖ በመስቀል ላይ የታረደውንና ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም "በእውነተኛው አምልኮና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ" ኾነው ለመቀበል መብቃታቸው ነው።

"የሰንበት ጌታ" የኾነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመቃብር ውስጥ ሳይቀር በማረፍ፡ እንደጥንታዊው አምላካዊ ትእዛዙ ያከበራትን፡ አንዲትና ቀዳሚት ኾና የኖረችውን "ሰንበት"፡ በዚህ፡ አማናዊ ትንሣኤው፡ እንግዲህ ወዲህ፡ ዘለዓለማዊት ኾና፡ በሰንበትነቷ እንድትቀጥል በማድረጉ፡ አማኞቹና አገልጋዮቹ፡ የቃል ኪዳን ሕዝቦቹና ባለአደራዎቹ የኾንነው፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ በምንገኝበት ህልውናችን፡ ሞት የሌለበትን፡ የመጀመሪያውን የመንፈስ ትንሣኤ ተቀዳጅተን ለመኖር በቃን! "ቀዳሚት ሰንበት" ብለን እናከብራት የነበረችውንም፡ ያችኑ፡ አንዲቱንና የመጀመሪያዪቱን "የእግዚአብሔር ሰንበት"፡ በጌታ ትንሣኤ፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" ብለን ሠይመን፡ በአንዲት ሰንበትነቷ፡ በቀጠለችበት ዘለዓለማዊነቷ እንድንኖርባት አስቻለን።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ስለዚህ፡ በአለንበት፡ በዚህ የዓመተ ምሕረት ዘመን፡ እስከዕለተ ምጽዓት፡ ከዚያም በኋላ በዘለዓለም ሕይወት የምንኖርባት ሰንበት፡ ያችው፡ “የእግዚአብሔር ሰንበት” ኾና የኖረችው፡ አንዲቷ ሰንበት እንጂ፡ “ቀዳሚት ሰንበት”፡ ወይም፡ “ሰንበተ አይሁድ” እና “ዳግሚት ሰንበት”፡ ወይም፡ “ሰንበተ ክርስቲያን” ተብለው የሚጠሩ፡ ኹለት ሰንበታት ያሉን በማስመሰል አለመኾኑን፡ እናንተም አውቃችሁት፡ በዚህ እውነታ የተከሠተላችሁንም የሃይማኖታችሁን ምሥጢር ተገንዝባችሁት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የምትኖሩትን፡ የኢትዮጵያዊነታችሁን የሕይወት ጸጋ እውን አድርጋችሁ ትጠቀሙበት ዘንድ አሳስባችኋለሁ፡፡

### ማዕዶት፡፡

“ማዕዶት”፡ በግእዝ፡ “ዐደወ” = “ተሻገረ” ከሚለው ግሥ ተገኝቶ፡ “መሻገር”፡ “ሽግግር” ማለት ነው፡ “ማዶ”፡ ወይም፡ “ከወንዝ ማዶ” የሚለው ዘይቤ የተገኘው፡ ከዚሁ “ማዕዶት”፡ ከሚለው ቃል መኾኑ፡ በቀላሉ ይታወቃል፡፡

የእሥራኤል ልጆች፡ በእግዚአብሔር ተጠራ፡ በሙሴ መሪነት፡ ቀይ ባሕርን ተሻግረው፡ ከግብፅ ባርነትና ከፈርዖን ገዢነት፡ ከእኒህ ጠላቶቻቸውም ሠራዊት ጦር እንደዳኑ ኹሉ፡ “እኛም፡ ኢትዮጵያውያን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዲያብሎስ ገዢነት፡ ወደእግዚአብሔር ልጅነት፡ ከኀጢኣት ቀንበር፡ ወደጽድቅ ክብር፥ ከሞት ፍዳ፡ ወደትንሣኤ ሕይወት ተሸጋገርን!” በማለት፡ የፋሲካ እሑድ ማግሥት የኾነውን፡ የ“ሰኞ”ን ዕለት፡ “ማዕዶት” ብለን እናከብረዋለን፡፡

### ዳግማዊ ትንሣኤ፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ እያለን፡ በዚህ ዓለም የምንኖረው ኑሮ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ለመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ በበቃንበት ሕይወት መኾኑን፡ ካለፉት ውይይቶቻችን ተረድታችሁታል፡፡ ከዚህ በኋላ፡ በዚሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ አዲስ አካልን ለብሰንና የዘለዓለም ሕይወትን ወርሰን እንድንኖርበት የተዘጋጀልን፥ በትንሣኤ ዘጉባኤ የምንነሣበት፡ ኹለተኛ ትንሣኤ መኖሩንም፡ አውቃችኋል፡፡ ይህን፡ የመጨረሻውን ትንሣኤ ለማስታወስ፡ ከፋሲካው የትንሣኤ እሑድ ቀጥሎ ያለውን ዕለተ እሑድ፡ “ዳግማዊ ትንሣኤ” ብለን እናከብረዋለን፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በፋሲካው ዓርብ ተሰቅሎና ሞቶ፥ ተቀብሮም፡ “ቅዳሜ ስዑር” በተባለችው፡ በቀዳሚት ሰንበት፡ በመቃብር ዐርፎ ከቆየ በኋላ፡ ሞትን ድል አድርጎና ሙስና መቃብርን (በመቃብር መበስበስን) አጥፍቶ፡ እኩለ ሌሊት ላይ፡ ለእሑድ አጥቢያ ተነሥቷል፡፡

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።

### *ዳግማዊ ትንሣኤ።*

---

ይህን ትንሣኤውን፡ በመጀመሪያ ለማየት የበቃችው፡ *ማርያም* *መግደላዊት* ስትኾን፥ ከእርሷ ቀጥለው፡ ለዚህ ክብር የታደሉት ሐዋርያት ናቸው። ይህ በኾነ በሳምንቱ እሑድ፡ በመጀመሪያዋ የትንሣኤ ዕለት ያልነበረው ቶማስ በተገኘበት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለኹለተኛ ጊዜ፡ ለሐዋርያት ስለተገለጠላቸውና በዚያን ጊዜ፡ የቶማስን ጥርጣሬ ማስወገድ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ *"ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!"* የሚለውን፥ በተለይ፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ በአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ ምክንያት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ቅድሚያ ተፈጻሚነትን ያገኘው የምሥራች ቃሉን ስላሰማባት፡ ይህች እሑድ፡ "*ዳግማዊ ትንሣኤ*" የሚለውን ስያሜ አግኝታለች።

## በዓለ ዕርገት።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡ በምድር ላይ ምስክሮቹ እንዲኾኑ ለመደባቸው ደቀ መዛሙርቱ፡ አርባ ቀን ሙሉ፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢር ሲነግራቸውና ሲያስረዳቸው፡ በሃይማኖታቸውም ሲያጸናቸው ቆየ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላም፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ፡ ከእነርሱ ጋር አብሮአቸው እንደሚኾንም አበሠራቸው። ይህ እስከሚኾን ድረስ ግን፡ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዝዟቸው፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ባለችበት፡ እያዩት፡ ወደሰማያት ዐረገ።

በዓለ ዕርገት፡ ይህችን ዕለት በማዘከር የምናከብርባት፡ እኛም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን፡ በትንሣኤ ሕይወት የኖርን፡ የትንሣኤ ልጆች ስለኾን፥ በክርስትና ጥምቀታችንም፡ ለመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ የበቃንበትን መንፈሳዊ አካል ስለለበስን፡ እያንዳንዳችን፡ ጽዋችን ደርሶ፡ በዕረፍተ ሥጋ፡ ከዚህ ዓለም በምንለይበት ጊዜ፡ የመሪያችንን ፈለግ ተከትለን፡ እንዲህ፡ በአርባ ቀናችን፡ ነፍሳችን፡ ወደሰማያት የምታርግ መኾኗን የምናስታውስባት ዕለት ናት።

ይህንም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ፡ ለማርያም መግደላዊት፡ *"ገና ወደአባቴ አላረግሁምና፡ አትንኪኝ! ነገር ግን፡ ወደወንድሞቼ ኼደሽ፡ 'እኔ፡ ወደአባቴና ወደአባታችሁ፡ ወደአምላኬና አምላካችሁም ዐርጋለሁ!' ብለሽ ንገሪያቸው፤"* ብሎ ያሰማት የመልእክት ቃል፡ ከትንሣኤው በኋላ እንዲያዩት የተዘጋጀላቸው፡ ሌላው የእግዚአብሔር ድንቅ ኃይል፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ያመለክታል።

ደግሞም፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ጌታ፡ በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዙርያ የተሰበሰቡትን፡ *"የመረጣቸውን፡ ሐዋርያትን፡ በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ፡ እስከዐረገበት ቀን ድረስ፡ ...አርባ ቀን እየታያቸው፡ ስለእግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፡ በብዙ ማስረጃ፡ ከሕማማቱ በኋላ፡ ሕያው ኾኖ፡ ለእነርሱ፡ ራሱን አሳያቸው። ከእነርሱም ጋር አብሮ ሣለ፡ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*“ነገር ግን፡ ከእኔ የሰማችሁትን፡ አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል፡ ጠብቁ! ዮሐንስ፡ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን፡ ከጥቂት ቀን በኋላ፡ በመንፈስ ቅዱስ ታጠምቃላችሁ!' አለ።*

*“እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፡ 'ጌታ ሆይ! በዚህ ወራት፡ ለእሥራኤል፡ መንግሥትን ትመልሳለህን?' ብለው ጠየቁት። እርሱም፡ 'አብ፡ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ፡ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፥ ነገር ግን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም፡ በይሁዳም ኹሉ፥ በሰማርያም፡ እስከምድር ዳርም ድረስ፡ ምስክሮቼ ትኾናላችሁ፥' አለ።*

*“ይህንም ከተናገረ በኋላ፡ እነርሱ እያዩት፡ ከፍ ከፍ አለ፥ ደመናም ተቀበለችው። እርሱም ሲኼድ፡ ወደሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፡ እነሆ፡ ነጫጭ ልብስን የለበሱ፡ ኹለት ሰዎች፡ በአጠገባቸው ቆሙ፡ ደግሞም፡ 'የገሊላ ሰዎች ሆይ! ወደሰማይ እየተመለከታችሁ፡ ስለምን ቆማችኋል? ይህ፡ ከእናንተ፡ ወደሰማይ የወጣው፡ ኢየሱስ፡ ወደሰማይ ሲኼድ እንዳያችሁት፡ እንዲሁ፡ ይመጣል!' አሏቸው።”* የሚለው፡ የወንጌላዊው ቃል፡[፻፺፯] ስለዕርገት ምሥጢር የተነገረውን እውነታ፡ በበለጠ ያረጋግጣል።

## ርክበ ካህናት።

“ርክበ ካህናት”፡ በበዓለ ትንሣኤና በበዓለ መንፈስ ቅዱስ እኩሌታ ላይ፡ ማለትም፡ ትንሣኤ በተከበረ በ፳፭ኛው ቀን፡ ወይም፡ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ሊከበር፡ ፳፭ ቀን ሲቀረው፡ ባለው “ዕለተ ረቡዕ” የሚውል፡ የተቀደሰ የጉባኤ ቀን ነው።

መጀመሪያ፡ በኪዳን ልቦና ተመሥርቶ፥ በመካከሉ፡ በኪዳን አሪት በተጠናከረው፥ በመጨረሻም፡ በኪዳን መንፈስ ቅዱስ በተፈጸመው፡ በኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ዘርፎች ውስጥ፡ በምርጫም ኾነ፡ በመደበኛነት የሚያገለግሉት ኹሉ፡ “ካህናት” ይባላሉ፤ “የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች” ማለት ነው። እነዚህ ኹሉ፡ በታላቁ ጥንታዊ ጉባኤያቸው፡ በአንድነት ተሰብስበውና በማናቸውም ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ተመካክረው ውሳኔ ይሰጣሉ። ያን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ለማዘከር፡ ይህ ዕለት፡ “ርክበ ካህናት” ተብሎ፡ በበዓል መልክና በተቀደሰ ስብሰባ ይከበራል።

ይኸውም፡ ሐዋርያት፡ ቀደም ብሎ፡ እስከዕርገት፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መንበርነት፥ ከዕርገት በኋላም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰብሳቢነት፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተገኘችበት፡ ያደርጉት የነበረውን ስብሰባ የመሰለ ነው።

## ምዕራፍ ፮፡ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።

### በዓለ መንፈስ ቅዱስ።
### (በዓለ ሃምሳ)

እግዚአብሔር፡ በዘመነ ብሉይ፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ላስደሰቱት፡ ለአብርሃም፡ ለይስሐቅና ለያዕቆብ፡ በቃል ኪዳን የሰጣቸውን ተስፋ ሊፈጽም፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ በታላቅ ክንዱ፡ ከግብፅ አውጥቶ፡ ምድረ ከነዓንን ካወረሳቸው በኋላ፡ ሕዝቡ እንዲያከብራቸው፡ ያዘዛቸው፡ ሦስት ታላላቅ የዓመት በዓላት ነበሩ። ከእነዚህ በዓላት መካከል፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው፡ "በዓለ ሃምሳ"፡ ወይም፡ "በዓለ ሠዊት"፡ ወይም፡ "የእሸት በዓል" ነው። የመጀመሪያው በዓል፡ "በዓለ ናእት"፡ ወይም፡ "የቂጣ በዓል"፡ ወይም፡ "የፋሲካ በዓል" ሲኾን፡ ኹለተኛው በዓል ደግሞ፡ "በዓለ መጸለት"፡ ወይም፡ "የዳስ በዓል" የሚባለው ነው።

"በዓለ ፋሲካ"፡ የእሥራኤል ልጆች፡ ተጨቊነው የኖሩበት፡ የባርነት አገዛዝ አብቅቶ፡ ከግብፅ ምድር ነጻ ያወጣቸውን፡ የእግዚአብሔርን የማዳን ኀይሉን፡ በዚህ ዕለት፡ ለመሥዋዕትነት አርደው በሚበሉት የበግ ደም፡ የሚያስታውሱበት በዓል ነው።

"በዓለ መጸለት"፡ እግዚአብሔር፡ የእነዚህኑ ሕዝብ፡ ሃይማኖትና ምግባር ሊፈትን፡ በድንኳን ብቻ እንዲኖሩ አድርጎ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በሲና ምድረ በዳ በመንከራተት የኖሩበትን የስደት ጉዞ እንዳይዘነጉ፡ በውጭ በሜዳ፡ ዳስ ሠርተው እንዲያከብሩት ያዘዘው በዓል ነው።

"በዓለ ሃምሳ"፡ የሕዝቡ ወገን የኾነው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ እግዚአብሔር፡ አዘጋጅቶ ከሰጠው ነጻ አገርና ለምለም ምድር፡ በየዓመቱ፡ ሠርቶ ካመረተው ሰብሉ፥ ወይም፡ ሀብቱ ላይ፡ "በኵራቱን"፡ ማለትም፡ የመጀመሪያውን ፍሬ፡ ለበረከት በማቅረብ፡ ይህን ቸርነት ያደረገለትን ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት በዓል ነው።

እነዚህ ሦስት ታላላቅ የእግዚአብሔር በዓላት፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ኪዳነ ምሕረት፡ ታድሰውና ተሸልመው፡ እውነተኞቹ እሥራኤል በኾኑት ኢትዮጵያውያን ዘንድ፤ በአዲስ ኪዳኑ በዓላት ተተክተው ይከበራሉ። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

"በዓለ መጸለት"፡ በ"ጥምቀት በዓል" ተተክቷል። ይህም፡ ካህናት ተሸክመውና ሕዝቡ አጅበው፡ ወደወንዙ ውኃ በሚያወርዱት፥ በዚያም፡ ዳስ ሠርተው በሚያሳድሩት ታቦታቸው የተመሰለውን፡ መንፈስ ቅዱስም፡ በርግብ አምሳል፡ በራሱ ላይ ረብቦ የታየበትን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ *"በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወድደው ልጄ፡ ይህ ነው!"* በሚል ቃል፡ ድምፁን ከሰማያት ያሰማለት እግዚአብሔር አብ፡ ወላዲነቱና አሥራፂነቱ፡ በምሥጢረ ሥላሴ የተገለጸበት አስተርእዮው፡ በማኅሌት የሚወደስበትና በቅዳሴ የሚመሰገንበት በዓል ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

"በዓለ ፋሲካ"፡ በ"ትንሣኤ በዓል" ተተክቷል። ይህም፡ አማናዊው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ ተሰቅሎና ደሙን አፍስሶ፤ ሞቶና ተቀብሮ፡ ዲያብሎስንና ኀጢአትን፡ ሞትንና ሲኦልን ድል ነሥቶ፡ ከሙታን ተለይቶ በተነሣው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ "ትንሣኤ" ማለት ነው።

"በዓለ ሃምሳ"፡ በ"በዓለ መንፈስ ቅዱስ" ተተክቷል። ይህም፡ "*'በዓለ ሃምሳ' የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ፡ ኹሉም* [ሐዋርያት]፡ *በአንድ ልብ ኾነው፡ አብረው ሳሉ፡ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ፡ ከሰማይ ድምፅ መጣ፡ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ኹሉ ሞላው። እንደእሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩዋቸው፡ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በኹሉም፡ መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። መንፈስም፡ ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው፡ በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*" በሚለው፡ የወንጌላዊው ቃል ተረጋግጧል።

ወንጌላዊው ሉቃስ፡ በ"በዓለ ሃምሳ" ስለኾነው ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ የገለጸውን፡ ይህን ዜናውን በመቀጠል፡ "*ከሰማይ በታች ካሉ ሕዝብ ኹሉ፡ በጸሎት የተጉ አይሁድ፡ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፡ ይህም ድምፅ በኾነ ጊዜ፡ ሕዝቡ ኹሉ ተሰበሰቡ፡ እያንዳንዱም፡ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር፡ የሚሉትን አጡ፡ ተገርመውም፡ ተደንቀውም፡ እንዲህ አሉ፦ 'እነሆ፡ እነዚህ የሚናገሩት ኹሉ፡ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን፡ የተወለድንበትን፡ የገዛ ቋንቋችንን፡ እንዴት እንሰማለን?'*" ሲል ጽፏል፤ አያይዞም፡ የእነዚህን ሕዝብ ማንነት፡ ኹሉንም፡ በያገራቸው ስም እየለየ ሲዘረዝር፡ ከአይሁድ አስቀድማ፡ በኪዳን ልቦና፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር አገር የኾነችውን፡ የኢትዮጵያን ስምና ብሔራዊ ቋንቋ ብቻ ሳያወሳ በመቅረቱ፡ የኪዳን አሪቱ ማዕከል ለኾነችው፡ ለታቦተ ጽዮን ታማኝ ባለአደራዎች የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያን፡ በዚያ በዓል ላይ አለመኖራቸውን ማመልከቱ መኾኑ ይታወቃል።

ይኹን እንጂ፡ ወንጌላዊው፡ ለዚህ የዜና አቀራረቡ፡ በቂ ምክንያት አለው። ይኸውም፡ እኒያ፡ የተለያየ ቋንቋ ያላቸው፡ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች የኾኑት ሕዝብ ኹሉ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የለገሠውን የመጨረሻውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዚች ዕለት፡ በዓይናቸው አይተው እንዲያምኑ የኾነው፡ ልክ፡ የጌታን ትንሣኤ፡ በገሃድና በግዘፍ አይተው እንዳመኑት፡ እንደሐዋርያት፡ ይልቁንም፡ ከእነርሱ፡ እንደአንዱ እንደኾነው፡ እንደቶማስ፡ "በማየት" ሲኾን፡ "*እናንተ፡ ስላያችሁኝ፡ አምናችኋል፤ 'ብፁዓን' ግን፡ ሳያዩ የሚያምኑብኝ ናቸው!*" ባለው፡ መለኮታዊ ቃሉ፡ የበቁ ኾነው፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በቀዳሚ አርአያነት እንዲያገለግሉት ያዘጋጃቸው፡ ኢትዮጵያውያን መኾናቸውን፡ ሊያመለክት በመፈለጉ መኾኑ ግልጽ ነው።

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::
## በዓለ መንፈስ ቅዱስ (በዓለ ሃምሳ)::

---

ይህ እውነታ: ምንም ዓይነት የሚታይ ምልክት: ወይም የሚጨበጥ ማስረጃ ሳያስፈልገው: በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ: በእጁ ካለው: ከቅዱስ መጽሐፉ ባነበበውና ከሐዋርያው ፊልጶስ አንደበት በሰማው የምሥራቹ ቃል ብቻ አምኖ: ወዲያው በተጠመቀው: በዚያ "አቤሜሌክ" በተባለው: ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ሃይማኖታዊ ምግባር: እውን ኾኖ[፪፻፺] መፈጸሙን: ወንጌላዊው: አከታትሎ በገለጸው ዜናው: በይፋ አሳውቋል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: *"ለምኑ! ይሰጣችሁማል፡ ፈልጉ! ታገኙማላችሁ፡ መዝጊያን አንኳኩ! ይከፈትላችሁማል:: የሚለምን ኹሉ: ይቀበላልና፡ የሚፈልግም: ያገኛል፡ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳ: ይከፈትለታል፡"* ሲል: ለደቀ መዛሙርቱ ስለጸሎት: በብዙ ምሳሌ ካስተማራቸው በኋላ: በመጨረሻ ያሰማቸው: *"እንኪያስ: እናንተ: ክፉዎች ስትኾኑ: ለልጆቻችሁ: መልካም ስጦታን መስጠትን ካወቃችሁ: በሰማይ ያለው አባት: ለሚለምኑት: እንዴት አብልጦ: መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው!?"* ብሎ የደመደመው ቃሉ: በዚች ዕለት መፈጸሙ: ይፋ ኾኖ ተጀመረ::

አዎን! እግዚአብሔር: ለሰው ልጆች ሊሰጥ ያዘጋጀው: የመጨረሻው ጸጋ: ሥጋዊው ገንዘብና ሀብት፡ እውቀትና ጥበብ፡ ኃይልና ክብር ሳይኾን: ከእነዚህ ኹሉ የሚበልጥና የሚሻል፡ እነዚህ ኹሉ በረከቶች: አስቀድመው: በሥነ ፍጥረት: ከፈጣሪ: ተትረፍርፈው: ለሰው ልጆች፡ በነጻ የተሰጡ መኾናቸውን የሚገልጽ፡ ካገኙት የማይታጣ፡ ማንም: ሠርቆ፡ ወይም: ነጥቆ ሊወስደው የማይቻል: ሌላ: ረቂቅ ስጦታ መኾኑ: በዚች ዕለት: በእርግጥ ታወቀ!

፡ አዎን! እግዚአብሔር: ለሰው ልጆች: ሊለግሥ ያዘጋጀው: የመጨረሻው ጸጋ: ከእነዚህ: ከምድራውያኑ ሀብታት ይልቅ: እጅግ የሚጠቅመው፡ በብዛት ሊቆጠርና በመጠን ሊሠፈር፡ በክብደት ሊመዘንና በዋጋ ሊተመን የማይቻለው: ልዩውና ዘለዓለማዊው ገንዘብና ሀብት፡ እውቀትና[፪፻፳] ጥበብ፡ ኃይልና ክብር መኾኑ: በዚች ዕለት፡ እውን ኾኖ: በገሃድ ታየ!

አዎን! ያ: በዚያች ዕለት: በእርግጥ የታወቀው፡ እውን ኾኖም: በገሃድ የታየው: እግዚአብሔር: በለጋሥነቱ: ለሰው ልጆች የሰጠው: የመጨረሻ ጸጋው: *መንፈስ ቅዱስ* ነው::

በዘመነ ብሉይ ኪዳን: በመከሩ ወራት ከሚውለው: ከ"በዓለ ሠዊት" በኋላ: ሰባት ሱባዔ: ማለትም: ሰባት ሳምንት ተቆጥሮ: ባለው ማግሥት: የሚውለው ሰንበት: "በዓለ ሃምሳ": ወይም: በግሪክኛ: "ጴንጠቆስጤ" ተብሎ ይከበር እንደነበረ ኹሉ: እንዲሁ: በዘመነ አዲስ ኪዳንም: ከ"በዓለ ትንሣኤ" በኋላ: ሰባት ሱባዔ: ማለትም: ሰባት ሳምንት ተቆጥሮ: ባለው ማግሥት: የሚውለው ሰንበት: "በዓለ መንፈስ ቅዱስ": ወይም: በግሪክኛ: "ጰራቅሊጦስ" ተብሎ የሚከበር ኾኗል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህ ቀን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በተገኘው ጸጋ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በሰው ላይ፡ በምልዓት ወርዶ ሲያድር የታየበት ዕለት ነው፡ ለዚህ ጸጋ የታደሉትም፡ ፲፪ቱ ሐዋርያት ናቸው። እግዚአብሔር፡ በመለኮታዊ ዕቅዱ፡ ለሰው ልጆች፡ በነፍስ ወከፍ ሊሰጥ ያዘጋጀውን፡ የዘለዓለማዊ ሕይወት ጸጋ፡ ከፍጹምነት ደረጃ ያደረሰው መኾኑን፡ በዚህ ዕለት፡ ባደረገው ቸርነቱ ስላረጋገጠ፡ እነሆ፡ *"በዓለ መንፈስ ቅዱስ"፡ የዓመቱ በዓላት ኹሉ፡ ዘውድ ኾነ።* ስለዚህ፡ የበዓላቱ ኹሉ ርእስና መደምደሚያ የኾነውን፡ ይህን ቀን፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ ኾነን፡ በጠለቀና በመጠቀ ፍጹም የደስታ ስሜት እናከብረዋለን።

እንግዲህ፡ ከ"መርዓዊ" ዕለተ እሑድ ጀምሮ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በሰዎች ላይ መውረዱ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ለዓለሙ፡ በይፋ እስከተገለጠባት እስከዚች፡ የሰንበተ ክርስቲያን ዕለተ እሑድ ድረስ ባሉት ወራት፡ ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ የሚገኝበት ኹኔታ፡ በዓመቱ የዕድሜ ዑደቱ ጊዜ፡ በሚሰማው የህልውና ስሜት ዓይነት ይኾናል፡ ይህም ስሜት፡ ኢትዮጵያዊው፡ አኹን፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ በሕይወተ ነፍሱ ጭምር፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሳይለይ፡ በእውነትና በመንፈስ፡ አብሮ ባሳለፈው የሕይወት ጉዞ ተንጸባርቆ ይታያል።

ይህም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በፍጹም መታመን እንደሚጋደል፡ ቆራጥ አርበኛ፡ ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት፡ ከዲያብሎስ እየተፈተነ፡ በገዳመ ቆሮንቶስ ካሳለፈው ጾም ጀምሮ፡ አያሌ የመስቀል ሥቃዮች ተቀብሎ፡ እስካረፈባት፡ እስከሐሙስ ዕለተ ዓርብ ድረስ፡ ዐብሮት በመዋረድ፡ በመታሠር፡ በመራቆት፡ በመገረፍ፡ የእሾህ አክሊልን በመቀዳጀት፡ በመሰቀል፡ በመሞት፡ በጦር ተወግቶ ደሙን በማፍሰስ፡ በመቀበር፡ በመነሣትና በማረግ፡ ያ ኢትዮጵያዊ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ፡ የጌታውና የእመቤቱ ጽዋ ተሳታፊ ለመኾን በመብቃቱ ማለት ነው።

## ዘመነ ክረምት።

በበዓለ መንፈስ ቅዱስ ማግሥት ባለው ሰኞ፡ ጾመ ሐዋርያት፡ ከዚያ በሚቀጥለው ዕለተ ረቡዕ ደግሞ፡ ጾመ ድኅነት፡ ተከታትለው የሚገቡ ከመኾናቸው ጋር፡ ሰኔ ፳፮ ቀን በሚጀምረው፡ በክረምቱ ወራት የሚከበሩት በዓላት፡ በፍልሰታው ሱባዔ ከሚውሉት በቀር፡ ኹለት ኾነው ይገኛሉ፡ እነዚህም፡ የአዲስ ኪዳኑ፡ ቅዱሳን ሐዋርያት፡ የቅዱስ ጴጥሮስና የቅዱስ ጳውሎስ፡ እንዲሁም፡ የብሉይ ኪዳኑ አብርሃም ሥላሴ ናቸው።

የእነዚህን ቅዱሳን፡ በዓላታቸውን በምናከብርበት፡ ዜና ዝክራቸውንም በምናስታውስበት ጊዜያት ኹሉ፡ እናንተም፡ እኔም፡ አጠንክረን ልንገነዘበው የሚገባን ታላቅ ቁም ነገር አለ።

# ምዕራፍ ፯፡ በዓል፡፡
## ዓበይትና ንኡሳን በዓላት፡፡
## ዘመነ ክረምት፡፡

---

ይህም፡ የዛሬዎቹ ሓዋርያትና የዛሬዎቹ አብርሃም፡ እያንዳንዳችን፡ በእየራሳችን፡ እኛው መኾናችንን አውቀንና ተረድተን፡ እኛም እንደነርሱ ኾነን መገኘትና ለእነርሱ፡ ከፈጣሪያቸው የተሰጣቸውን መመሪያ ተከትለን መፈጸም ያለብን መኾናችንን ከልባችን፡ በእውነት መገንዘቡ ነው፤ ይኸው ቊም ነገር፡ በእውነት ታላቅ ስለኾነ፡ በሥራ ላይ አውላችሁ፡ ለፍሬ እንድታበቁት እንጂ፡ ለአንዲት አፍታም እንኳ ቢኾን እንዳትዘነጉት፡ በብርቱ አደራ እላችኋለሁ፡፡

### ጴጥሮስ ወጳውሎስ፡ ቅዱሳን ሓዋርያት፡፡

የመጀመሪያው በዓል፡ መለኮታዊው መምህር፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ሥልጣን ኹሉ፡ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡ እንግዴህ፡ ኺዱና አሕዛብን ኹሉ፡ በአብ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፡ ያዘዝኋችሁንም ኹሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው፡ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፡፡ እነሆ፡ እኔ፡ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ኹልጊዜ፡ ከእናንተ ጋር ነኝ!"* ብሎ፡ ለ፲፪ቱ ሓዋርያት የሰጣቸውን ተልእኮ፡ በሰማዕትነት ገድል የፈጸሙት፡ ቅዱሳን ጴጥሮስና ጳውሎስ የዕረፍታቸው መታሰቢያ፡ ከጾመ ሓዋርያት ማብቂያ ጋር የሚከበርበት፡ ሓምሌ ፭ ቀን ነው፡፡

ይህ፡ አኹን የጠቀስሁላችሁ፡ የጌታ መመሪያ፡ ሓዋርያት፡ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ፡ ወደአሕዛብ እንዲኼዱ ያዘዘበት የመጨረሻው ሲኾን፡ ከዚያ ቀደም ብሎ፡ *"በአሕዛብ መንገድ አትኺዱ! ወደሳምራውያንም ከተማ አትግቡ! ይልቅስ፡ የእሥራኤል ቤት ወደሚኾኑ፡ ወደጠፉት በጎች ኺዱ እንጂ፡፡"* ብሎ የሰጣቸው፡ በአጠቃላይ፡ እነርሱ፡ በጊዜያቸው፡ ሓዋርያዊ ተልእኳቸውን በመፈጸም፡ እየራሳቸውን፡ ለሰማዕትነት ገድል ያበቃቸው፤ እኛም፡ በፋንታችን፡ የእነርሱን አርአያነት ተከትለን ልናደርገው የሚገባን፡ የታላቁ መምህር መለኮታዊ መመሪያ፡ እነሆ፡ ለእናንተም፡ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቦላችኋል፡-

*"ኼዳችሁም፡ 'መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች!' እያላችሁ አስተምሩ! ሕሙማንን ፈውሱ! ሙታንን አስነሡ! ለምጻሞችን አንጹ! አጋንንትን አውጡ!*

*"ያለዋጋ የተቀበላችሁትን፡ ያለዋጋ ስጡ! በልግሥና የተቀበላችሁትን፡ በልግሥና ስጡ! በመቀነታችሁም፡ ወርቅ፡ ወይም፡ ብር፡ ወይም፡ መሓለቅ አትያዙ! ለመንገድም፡ ኰረጆ፡ ወይም፡ ኹለት ልብስ፡ ወይም፡ ጫማ፡ ወይም፡ በትር አይኑራችሁ!*

*"ለሠራተኛ፡ ዋጋው ይገባዋልና፡ በምትገቡባት፡ በማንኛዪቱም ከተማ፡ ወይም፡ መንደር፡ 'ሰላም፡ ለማን ይገባዋል?' ብላችሁ ጠይቁ! እስክትወጡም ድረስ፡ ከዚያ ተቀመጡ! ወደቤትም በገባችሁ ጊዜ፡ ሰላምታ ስጧቸው! ሰላማችሁ፡ ለዚያ ቤት የሚገባው ቢኾን፡ በእርሱ ይደርበት! የማይገባው ቢኾን ግን፡ ሰላማችሁ፡ ወደእናንተ ይመለስ!*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*“ላልተቀበላችሁ፡ ነገራችሁንም ላልሰማ ግን፡ ከዚያች አገር ወጥታችሁ፡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ! ከዚያች አገር ይልቅ፡ የሰዶምና የገሞራ ምድር፡ ዕረፍት እንደሚያገኙ፡ በእውነት እነግራችኋለሁ።*

*“እነሆ፡ እኔ፡ እንደበጎች፡ በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ፡ እንግዲህ፡ እንደእባብ ብልሆች፡ እንደርግብም የዋሆች ኹኑ! ከክፉዎች ሰዎች ተጠበቁ! ወደሸንጎዎች ይወስዷችኋልና፡ በምኵራባቸውም ይገርፏችኋልና። በእነርሱና በአሕዛብ ላይ ምስክር ይኾንባቸው ዘንድ፡ ስለእኔ፡ ወደገዢዎች፡ ወደነገሥታትም፡ ከስሰው ይወስዷችኋል። ከስሰው በሚወስዷችሁ ጊዜ፡ ስለምትሉትና ስለምትናገሩት፡ አታስቡ! በዚያን ጊዜ፡ የምትናገሩት ይሰጣችኋልና፡ የምትናገሩት፡ እናንተ አይደላችሁምና፡ የሰማዩ አባታችሁ መንፈስ፡ እርሱ፡ በእናንተ ላይ አድሮ ይናገራል እንጂ።*

*“ወንድም፡ ወንድሙን፡ ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፡ አባትም፡ ልጁን፡ እንዲሁ፡ አሳልፎ ይሰጣል፡ ልጆችም፡ በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ፡ ይገድሏቸዋልም። ስለስሜ፡ በሰው ኹሉ ዘንድ፡ የተጠላችሁ ትኾናላችሁ። ይህን ኹሉ፡ እስከመጨረሻው የታገሠ፡ እርሱ ይድናል።*

*“ከዚያች አገር ቢያሳድዷችሁ፡ ወደሌላዪቱ ሽሹ! እውነት እላችኋለሁ፡ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ፡ የእሥራኤልን አገሮች አዳርሳችሁ አትጨርሱም።*

*“ከመምህሩ የሚበልጥ ደቀ መዝሙር፡ ከጌታው የሚበልጥ አገልጋይ የለም። የደቀ መዝሙር መጠኑ፡ እንደመምህሩ ከኾነ፡ የአገልጋይም መጠኑ እንደጌታው ከኾነ፡ ይበቃዋል። ባለቤቱን፡ 'በሰይጣናት አለቃ፡ ሰይጣናትን ያወጣል!' ያሉት ከኾነ፡ ቤተሰቡንማ፡ እንደምን፡ ከዚህ አብልጠው አይናገሩዋቸው?!*

*“እንግዲህ፡ አትፍሩዋቸው! የማይገለጥ፡ ሽፍን፡ የማይታወቅም፡ ሥውር የለምና። በጨለማ፡ ለብቻችሁ የነገርኋችሁን፡ በብርሃን ተናገሩት! በጆሮአችሁ፡ በሹክሹክታ፡ ያስሰማኋችሁንም፡ በሰገነት ላይ አስተምሩት!*

*“ሥጋችሁን የሚገድሉትን፡ ነፍሳችሁን ግን፡ ሊገድሏት የማይቻላቸውን አትፍሩዋቸው! ይልቅስ፡ በኹለንተናችሁ ላይ ሥልጣን ያለውን፡ ከገደለም በኋላ፡ ነፍስንም፡ ሥጋንም፡ አንድ አድርጎ፡ በገሃነም ማጥፋት የሚቻለውን፡ እርሱን፡ ፍሩት እንጂ።*

*“ኹለት ወፎች፡ በኹለት መሓለቅ ይሸጡ የለምን? ከእነሱ፡ አንዲቱ እንኳ፡ የሰማዩ አባታችሁ ሳያውቅ፡ በምድር ላይ አትወድቅም፡ የእናንተስ፡ የራስ ጠጕራችሁ ኹሉ፡ የተቈጠረ ነው። እንኪያስ አትፍሩ! እናንተ፡ ከብዙ ወፎች ትበልጣላችሁና።*

*“በሰው ፊት፡ የሚያምንብኝን ኹሉ፡ እኔም፡ በሰማይ ባለው፡ አባቴ ፊት አምነዋለሁ። በሰው ፊት የካደኝን ግን፡ እኔም፡ በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ።*

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል፡፡
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት፡፡
### ጴጥሮስ ወጳውሎስ፡ ቅዱሳን ሐዋርያት፡፡

---

*"ለምድር፡ ሰላምን ያመጣሁ አይምሰላችሁ! ሰይፍን እንጂ፡ ሰላምን ለማምጣት፡ አልመጣሁም! የመጣሁትስ፡ ወንድ ልጅን፡ ከአባቱ፡ ሴት ልጅንም፡ ከእናቷ፡ ምራትንም፡ ከአማቷ ልለይ ነው፡፡ ለሰው፡ የራሱ ቤተሰብ ጠላት ይኾነዋል፡፡*

*"ከእኔ ይልቅ፡ አባቱን፡ ወይም፡ እናቱን የሚወድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባም፡ ሊያገለግለኝም አይችልም፡ ከእኔ ይልቅ፡ ወንድ ልጁን፡ ወይም፡ ሴት ልጁን የሚወድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባም፡ ሊያገለግለኝም አይችልም፡፡ ወደእኔ የሚመጣ፡ ሊከተለኝም የሚወድ፡ አባቱንና እናቱን፡ ሚስቱንና ልጆቹን፡ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፡ የራሱ የኾነችውን፡ ሰውነቱንም እንኳ ሳይቀር፡ የማይጠላ፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም፡፡ ለሞት የሚያበቃውን፡ የመስቀል መከራ ለመቀበል እስከመጨከን ቆርጦ፡ እኔን ያልተከተለ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባም፡ ሊያገለግለኝም አይችልም፡፡ ሰውነቱን፡ 'የእኔ ናት!' የሚል፡ ያጣታል፡ ራሱን፡ ስለእኔ አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያገኛታል፡፡"* [፻፶፱]

## የአብርሃሙ (የሐምሌ) ሥላሴ፡፡

ኹለተኛው በዓል፡ "ሥሉስ ቅዱስ" ተብሎ የሚጠራው፡ እግዚአብሔር፡ በቤተ አብርሃም፡ በዚሁ አንድነቱና ሦስትነቱ፡ በእንግድነት ተገኝቶ፡ በሰው ልጆች ዘንድ ሥውር ኾኖ የኖረውን፡ የእግዚአብሔርን የአንድነት ባሕርይና የሦስትነት ህልውና ምሥጢር፡ በበለጠ አግዝፎ ማሳየትን የቀጠለበትን፥ ደግሞም፡ የማይታየው እግዚአብሔር፡ በሃይማኖታዊ ምግባራቸው በቅተው ለሚገኙ የሰው ልጆች፡ ራሱን ገልጦ የሚያናግራቸውና ፍላጎታቸውን የሚፈጽምላቸው መኾኑን አረጋግጦ ያሳየበትን ታላቅ ሥራውን በማዘከር የምናከብረው፡ ሐምሌ ፯ ቀን ነው፡፡ በዓሉ፡ በዘልማድ፡ "የአብርሃሙ ሥላሴ" ይባላል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ እግዚአብሔር፡ ለአብርሃምና ለሣራ ያደረገውን መለኮታዊ ቸርነት፡ ዛሬም፡ ለተማመኑበት ፍጡሮቹ ኹሉ፡ መላልሶ የሚያደርገው መኾኑን አምነን፡ ይህችን በዓላችንን፡ በጽኑ ሃይማኖታዊ ስሜት እናከብራታለን፡፡ በዚያች ዕለት፡ የአብርሃምና የሣራ ሃይማኖት የፈጸመውን ተአምራዊ ትንግርት፡ በዓይነ ሕሊና፡ መለስ ብለን ልንመለከት እንችል ዘንድ፡ ሕያው ዜናው፡ ለአባቶቻችንና እናቶቻችን ደርሷቸው፡ እነርሱ ለእኛ፡ ለዛሬዎቹ ልጆቻቸው፡ በትውፊት ስላስተላለፉልን፡ እዚህ ላይ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

"አብርሃም፡ መኖሪያውን ከተመሳቀለ ጎዳና ሠርቶ፡ የወጣ የወረደውን፡ ያለፈ ያገደመውን ሲቀበል ይኖር ነበር፡ ሰይጣን ተመቅኝቶ፡ ራሱን ገምሶ፡ ደሙን አፍስሶ፡ አጥንቱን ከስክሶ፡ ከጎዳና ቆይቶ፡ ወደአብርሃም ሠፈር የሚያቀኑትን መንገደኞች ኹሉ፡ "ወዴት ትኼዳላችሁ?" ይላቸዋል፡፡ "ከአብርሃም ቤት!" ይሉታል፡፡ ሰይጣንም መልሶ፡ "የወትሮው አብርሃም መሰላችሁን? እኔ፡ 'ያበላኛል፥ ያጠጣኛል!' ብዬ ብኼድ፡ ራሴን ገምሶ፡ ደሜን አፍስሶ፥ አጥንቴን ከስክሶ፥ ልብሴን ገፍፎ ሰደደኝ!" ይላቸዋል፡፡

"ሰይጣን: እንዲህ እያለና ይህን እያደረገ: አብርሃምን: እንግዳ ከለከለበት:: አብርሃምም: "ማዕደ እግዚአብሔርን: እንዴት ያለምስክር እመገባለሁ!?" ብሎ: ግብር ሳያገባ: ሦስት ቀን አደረ::"

በሦስተኛው ቀን የኾነውን ዕፁብ ድንቅ ነገር: የቅዱሳት መጻሕፍቱ ጥቅስ: እንዲህ እያለ ይተርከዋል:-

*"በቀትር ጊዜ: እርሱ (አብርሃም) በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ: እግዚአብሔር: በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት:: ዓይኑንም አነሣ: እነሆም: ሦስት ሰዎች: በፊቱ ቆመው አየ: ባያቸውም ጊዜ: ሊቀበላቸው: ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ: ወደምድርም ሰገደ፡ እንዲህም አለ:- "አቤቱ: በፊትህስ ሞገስን አግኝቼ እንደኾነ: ባሪያህን አትለፈኝ!" ብዬ እለምናለሁ፡ ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ! እግራችሁን ታጠቡ! ከዚችም ዛፍ በታች ዕረፉ! ቊራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ! ልባችሁንም ደግፉ! ከዚያም በኋላ ትኼዳላችሁ! ስለዚህ: ወደባሪያችሁ መጥታችኋልና::*

*"እነርሱም: "እንዳልህ አድርግ!" አሉት::*

*"አብርሃምም: ወደድንኳን: ወደሣራ ገባና: "ሦስት መሥፈሪያ የተሰለቀ ዱቄት: ፈጥነሽ አዘጋጂ! ለውሺውም! እንጎቻም አድርጊ!" አላት::*

*"አብርሃምም: ወደላሞቹ ሮጠ፡ እጅግ የሰባም ታናሽ ጥጃ የዘና ለብላቴናው ሰጠው: የዘጋጅም ዘንድ: ተቻኰለ:: እርጎና ወተት: የንም: የዘጋጀውን ጥጃ አመጣ፡ በፊታቸውም: አቀረበው፡ እርሱም: ከዛፉ በታች: በፊታቸው ቆሞ ነበር፡ እነርሱም በሉ::*

*"እነርሱም: "ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት?" አሉት::*

*"እርሱም: "በድንኳኑ ውስጥ ናት፡" አላቸው::*

*"እርሱም: "የዛሬ ዓመት: እንደዛሬው ጊዜ: ወደአንተ: በእውነት እመለሳለሁ፣ ሚስትህ ሣራም: ልጅን ታገኛለች፡" አለ::*

*"ሣራም: በድንኳን ደጃፍ: በስተኋላው ሣለች: ይህንን ሰማች:: አብርሃምና ሣራም: በዕድሜአቸው ሸምግለው፡ ፈጽመው አርጅተው ነበር፣ በሴቶች የሚኾነውም ልማድ: ከሣራ ተቋርጦ ነበር:: ሣራም: በልቧ: እንዲህ ስትል ሣቀች:- "ካረጀሁ በኋላ: በውኑ ፍትወት ይኾንልኛልን? ጌታዬም: ፈጽሞ ሸምግሎአል::"*

*"እግዚአብሔርም: አብርሃምን አለው:- "'ካረጀሁ በኋላ: በውኑ: እወልዳለሁን?' ስትል: ሣራ: ለምን ሣቀች? በውኑ: ለእግዚአብሔር: የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት: እንደዛሬው ጊዜ: ወደአንተ እመለሳለሁ፡ ሣራም: ልጅን ታገኛለች::" ሣራም ስለፈራች: "አልሣቅሁም!" ስትል ካደች:: እርሱም: "አይደለም! ሣቅሽ እንጂ!" አላት::*

*"ሰዎቹም: ከዚያ ተነሥተው: ወደሰዶም አቀኑ፣ አብርሃምም: ሊሸኛቸው: አብሮአቸው: ኼደ::*

# ምዕራፍ ፮፡ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
### የአብርሃሙ (የሐምሌ) ሥላሴ።

"እግዚአብሔርም አለ፦ "እኔ የማደርገውን፡ ከአብርሃም እሠውራለሁን? አብርሃም፡ በእውነት፡ ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይኾናልና፡ የምድር አሕዛብም ኹሉ፡ በእርሱ ይባረካሉና። ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ፡ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ፡ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ፡ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁና።" ይህም፡ እግዚአብሔር፡ በአብርሃም ላይ የተናገረውን ነገር ኹሉ ያመጣ ዘንድ ነው። እግዚአብሔርም አለ፦ "የሰዶምና የገሞራ ጩኸት፡ እጅግ በዝቷልና፡ ኀጢአታቸውም፡ እጅግ ከብዷልችና፡ እንግዲህስ፡ ወደእኔ እንደመጣች፡ እንደጩኸቷ አድርገው እንደኾነ፡ ወርጄ አያለሁ፡ እንዲሁም ባይኾን፡ አውቃለሁ።

"ሰዎቹም፡ ከዚያ፡ ፊታቸውን አቀኑ፡ ወደሰዶምም ኼዱ። አብርሃም ግን፡ ከእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር። አብርሃምም ቀረበ፡ አለም፦ "በውኑ፡ ጻድቁን፡ ከኀጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን? ዐምሣ ጻድቃን፡ በከተማዪቱ ውስጥ ቢገኙ፡ በውኑ፡ ኹሉን ታጠፋለህን? ከተማዪቱንስ፡ በእርስዋ ስለሚገኙ ዐምሣ ጻድቃን አትምርምን? ይህ፡ ከአንተ ይራቅ! ጻድቁን፡ ከኀጢአተኛ ጋር ትገድል ዘንድ፡ ጻድቁም፡ እንደኀጢአተኛ ይኾን ዘንድ፡ እንደዚህ ያለው አድራጎት፡ ከአንተ ይራቅ! የምድር ኹሉ ፈራጅ፡ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?"

"እግዚአብሔርም፦ "በሰዶም፡ በከተማዪቱ ውስጥ፡ ዐምሣ ጻድቃን ባገኝ፡ ሥፍራውን ኹሉ፡ ስለእነርሱ እምራለሁ።" አለ።

"አብርሃምም መለሰ፡ አለም፦ "እኔ፡ አፈርና ዐመድ ስኾን፡ ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ፡ እነሆ፡ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፡ ከዐምሣው ጻድቃን፡ አምስት ቢጎድሉ፡ ከተማዪቱን ኹሉ፡ በአምስቱ ምክንያት ታጠፋለህን?"

"እግዚአብሔርም፦ "ከዚያ፡ አርባ አምስት ባገኝ፡ አላጠፋትም።" አለ።

"ደግሞም ተናገረው፡ እንዲህም አለ፦ "ምናልባት፡ ከዚያ፡ አርባ ቢገኙስ!?"

"እርሱም፦ "ለአርባው ስል አላደርገውም!" አለ።

"እርሱም፦ "ጌታዬ አይቆጣ! እኔም እናገራለሁ፡ ምናልባት፡ ከዚያ፡ ሠላሳ ቢገኙስ!?" አለ።

"እርሱም፦ "ከዚያ፡ ሠላሳ ባገኝ አላጠፋም!" አለ።

"ደግሞም፡ "እነሆ! ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ፡ አንድ ጊዜ ጀመርሁ፡ ምናልባት፡ ከዚያ፡ ሃያ ቢገኙስ!?" አለ።

"እርሱም፦"ከዚያ፡ ሃያ ቢገኙ፡ ስለሃያው አላደርገውም!" አለ።

"እርሱም፦ "እኔ ደግሞ፡ አንድ ጊዜ ብቻ ብናገር፡ ጌታዬ አይቆጣ! ምናልባት፡ ከዚያ፡ ዐሥር ቢገኙስ!?" አለ።

"እርሱም፦"ስለዐሥሩ አላጠፋትም!" አለ።

"እግዚአብሔርም፡ ከአብርሃም ጋር ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ኼደ፡ አብርሃምም፡ ወደ ሥፍራው ተመለሰ።"

## ደብረ ታቦር።

ከታላላቅ በዓሎቻችን፡ አንዱ የኾነው፡ ***በዓለ ደብረ ታቦር*** የሚውለው፡ በነሐሴ ፲፫ ቀን በመኾኑ፡ ለጾመ ፍልሰታ ሱባዔ ልዩ ምስራፍ ኾኖ፡ በታላቅ መንፈሳዊ ተመስጦና ማኅሌት ይከበራል።

ይህ በዓል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዓጸደ ሥጋ አብረውት ከነበሩት ደቀ መዛሙርቱ መካከል፡ ጴጥሮስንና ያዕቆብን፡ ወንድሙንም ዮሐንስን፡ በዓጸደ ነፍስ ካሉት ባለሟሎቹ ደግሞ፡ ሙሴንና ኤልያስን፡ "ታቦር" በተባለው የወይራ ዛፍ ተራራ ላይ አምጥቶ፡ የባሕርይ አምላክነቱን፡ በመግለጥ፡ ታማኞች አገልጋዮቹ፡ ሊያዩ የተመኙትን፡ እንዲያዩ፡ ሊሰሙ የተመኙትንም፡ እንዲሰሙ ያደረገበት ቸርነቱና ኃይሉ የሚዘከርበት ነው።

ይህንም፡ እርሱ፡ ለሕዝቡ፡ በምሳሌ የሚያስተምራቸው፡ ነቢዩ ኢሳይያስ፡ እያዩ፡ ስለማያዩ፡ እየሰሙም ስለማይሰሙ፡ ስለማያስተውሉትም ወገኖች፡ የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ መኾኑን፡ ጌታችን፡ ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ፡ መልስ በመስጠት ያስረዳቸው ቃሉ፡ በሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎት ላይ ዘወትር ይወሳል፡ ይህም፡ *"የእናንተ ግን፡ ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ፡ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ፡ ብፁዓን ናቸው። እውነት እላችኋለሁ? ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን፡ ነገሥታትም፡ የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው፡ አላዩም፡ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው፡ አልሰሙም።"* ሲል፡ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ነው።

በዚያ የታቦር ተራራ ላይ የታየውንም ተአምራት፡ እንዲህ የሚለው፡ የምሥራቹ ዜና አጠቃልሎ ይገልጸዋል፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ጴጥሮስንና ዮሐንስን፡ ያዕቆብንም ይዞ፡ ሊጸልይ፡ ወደተራራ ወጣ። ሲጸልይም፡ የፊቱ መልክ ተለወጠ፡ ልብሱም፡ ተብለጭልጮ፡ ነጭ ኾነ። እነሆም፡ ኹለት ሰዎች፡ እነርሱም፡ ሙሴና ኤልያስ፡ ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፡ በክብርም ታይተው፡ በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው፡ ስለመውጣቱ ይናገሩ ነበር።*

*"ነገር ግን፡ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት፡ እንቅልፍ ከበደባቸው፡ ነቅተው ግን፡ ክብሩንና ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩትን ኹለት ሰዎች አዩ። ከእርሱም ሲለዩ፡ ጴጥሮስ፡ ኢየሱስን፡ "አቤቱ፡ በዚህ መኾን፡ ለእኛ፡ መልካም ነውና፡ አንድ፡ ለአንተ፡ አንድ፡ ለሙሴ፡ አንድ፡ ለኤልያስ፡ ሦስት ዳሶችን እንሥራ!" አለው፡ የሚለውንም ኢያውቅም ነበር።*

*"ይህንም ሲናገር፡ ደመና መጣና ጋረዳቸው፡ ወደደመናው ሲገቡ ግሉም፡ ፈሩ። ከደመናውም፡ "የመረጥሁት ልጄ፡ ይህ ነው፡ እርሱን ስሙት!" የሚል ድምፅ መጣ። ድምፁም ከመጣ በኋላ፡ ኢየሱስ፡ ብቻውን ኾኖ ተገኘ። እነርሱም፡ ዝም አሉ፡ካዩትም ነገር፡ በዚያ ወራት፡ ምንም፡ ለማንም* ዮየ፲፮ *አልተናገሩም።*

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል::
# ዓበይትና ንዑሳን በዓላት::
# ደብረ ታቦር::

---

## ቡሔ::

የደብረ ታቦር በዓል: በሕዝባዊው ዘይቤ: "ቡሔ" ተብሎ ይከበራል:: በበዓሉ ዋዜማ: በየቤቱ: ችቦ ከበራ በኋላ: ከሠርክ ጀምሮ: በምሽቱ ጊዜ: ወጣቶች ወንዶች ልጆች: በየሠፈራቸው: በቡድን: በቡድን እየኾኑና በትር በትራቸውን ይዘው: ጅራፍ ሠርተው እያጮሁ: ለበዓሉ የተለመደውንም: "ቡሔ በሉ! ሆ! ልጆች ኹሉ! ሆ! እዚያ ማዶ: ጭስ ይጨሳል! አጋፋሪ: ይደግሳል! ያንን ድግሥ: ውጬ ውጬ! በድንክ አልጋ: ተገልብጬ! ያች ድንክ: ዓመለኛ! አላንድ ሰው: አታስተኛ!" የሚለውን የጭፈራ ሆታ: በመቀባበል እያሰሙ: "እንኳን አደረሳችሁ!" ለማለት: በመንደራቸው መኖሪያ ቤቶች ኹሉ ይዘዋወራሉ::

በየገቡበት ቤትም: ዙሪያውን ከብበው: በበትራቸው ወለሉን እየደቁና ከአንዱ አውራጅ ጓደኛቸው: "ሆ.ያ ሆዬ! ሆ! የኔ ጌታ! የሰጠኝ ሙክት! መስከረም ጠባ! ያንን ሳነክት! ..."ሆ.ያ ሆዬ! ሆ! የኔ እመቤት! የፈተለችው! የሸረሪት ድር! ያስመሰለችው! ..." የሚለውን የሆታ ዜማ እየተቀበሉ: የቤቱን አባወራና እመቤት ያሞግሳሉ:: ባለቤቶቹም: "እንኳን አብሮ አደረሰን! ደግሞም: ለሚመጣው ዓመት: እንዲሁ: በሰላም ያድርሰን! የዘንድሮውም: የቡሔ ዳቧችሁ ይኸውላችሁ!" ብለው: ትኩሱን ሙልሙል የቡሔ ኅብስት አበርክተውላቸውና መርቀዋቸው ያሰናብቷቸዋል:: ልጆቹም: ያንን ተቀብለው: "ዓመት በውድ ዓመት: ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! የጌታዬ ቤት! ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! እንደዚሁ እንዳላችሁ! ሆ! አይለያችሁ!" እያሉ መልካም ምኞታቸውን በመግለጽ እጅ እየነሡ ይወጣሉ::

"ቡሔ" ማለት: "ቡሔዬ": ብርሃኔ፥ መብራቴ ማለት ነው፤ በደብረ ታቦር: እንደመብረቅ የብልጭታ ብርሃን: ቧ ብሎ የተገለጠውን: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን: የፊቱን ጸዳል: የልብሱንም እንደበረዶ ነጭ መኾን ያስረዳል፡ የችቦው መብራት ምሳሌ: ይህ ነው:: ደግሞም: በኢትዮጵያኛ: "ለከት" ማለት: "ታናሽና ሞላላ: የሊጥ መፈተኛ: ጢብኛ: የዳቦ እንጎቻ" ማለት ሲኾን: እረኞች: "አክሥቴ ቤት: አለኝ ለከት!" ከሚሉት ሙልሙል የተነሣ: "ቡሔ": በግእዝ: "ብሖእየ": ማለትም: "ቡሖዬ" ተብሎ ስለሚተረጐም: የደብረ ታቦር በዓል ዕለት: ተቦክቶ የሚጋገረውን ኅብስት ያሳያል፤ ስለዚህ: "የቡሔ ዳቦ" የሚባለው ኅብስት: ባሕርየ መለኮቱን: በደብረ ታቦር የገለጠው: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ መኾኑን ማስተዋል ይገባል::

በዘመነ ብሉይ: ሙሴ: ከባለሟልነቱ የተነሣ: አምላኩን እግዚአብሔርን: *"እባክህ: ፊትህን (ክብርህን) አሳየኝ!"* ባለው ጊዜ: የሰጠው የተሰፋ መልስ: *"ሰው: አይቶኝ አይድንምና: ዛሬ: ፊቴን ማየት አይቻልህም፡ የምታይበት ጊዜ ግን ይመጣል!"* የሚል ነበረ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤

## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ዮ፡ የተሰፋ ቃል ተፈጽሞለት፡ ሙሴ፡ በዚያን ጥያቄው ጊዜ፡ በመለኮትነቱ ባሕርይና ግርማ ሊያየው ያልቻለውን፡ በኋላ ዘመንም፡ "ይህ ሥጋዬ ነው፡ ብሉት!" ብሎ፡ ራሱን፡ ኅብስት አድርጎ ያቀረበውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በታቦር ተራራ ላይ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ገዝፎ ሊያየው ችሏል::

እንግዲህ፡ የወንዶቹ ልጆች የሆኑት ጭፈራ የሚያዘክረው፡ ከደስታውና ከድንጋጤው የተነሣ፡ "የሚያደርገውን አያውቅም ነበር!" የተባለውን፡ የቅዱስ ጴጥሮስንና የቀሩትን ሐዋርያት አድራጎት ሲኾን፡ የጅራፉ ጩኸት ደግሞ፡ በዚያ ተራራ ላይ፡ ከጋረዳቸው ደመና ውስጥ ብርሃን መለኮቱን ለመግለጽ ከታየው መብረቃዊ የብልጭልጭታ ብርሃን ጋር[፻፶፱] ለተሰማው ነጎድጓዳዊ የመለኮት ድምፅ ምሳሌ ነው::

## በዓለ ፍልሰታ ለማርያም::

ለመጨረሻው፡ ለኹለንተናዊውና ለዘለዓለማዊው ትንሣኤ፡ በኵር ከኾነው፡ ከልጇ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥላ፡ በአዲስ ኪዳኑ የትንሣኤ አካል፡ ከሙታን ተለይቶ የመነሣትን ክብር ያገኘች፡ የዘመነ ኦሪቷ ጽላተ ኪዳን ታቦት፡ ምሳሌዋ የኾነችው፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት:: በዚያች ጽላተ ኪዳን ላይ የተቀረጸው እግዚአብሔር ቃል፡ የተቀረጸባትን ጽላት፡ የራሱ አካል አድርጎ፡ መለኮታዊ ክብሩን እንደገለጸባትና አምላካዊ ኃይሉን እንደፈጸመባት፡ ኋላም፡ በባሕርያዊ ጥበቡ እንደሠወራት ኹሉ፡ ከሥጋዋ ሥጋ፡ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ የተዋሐዳትን ቅድስት ድንግል ማርያምንም እንዲሁ፡ በትንሣኤው እውነኛ ገሃድ ያደረገውን፡ አማናዊውንና ዘለዓለማዊውን ክብሩን፡ ኃይሉንና ጥበቡን አጐናጽፎ፡ ለፍጹሙ ሕያው ማንነት አብቅቷታል::

የዚህም መነሻ፡ ድንግል ማርያም፡ "ትፀንሲ!"፡ ማለትም፡ "ትፀንሻለሽ!" ያላትን፡ የመልአኩን የቅዱስ ገብርኤልን የምሥራች ቃል ተቀብላ፡ "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ!" ማለትም፡ "እንዳልኸኝ (እንደቃልህ) ይኹንልኝ!" ባለችበት ቅጽበት፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" ማለትም፡ "አምላክ ሰው ኾነ!" በሚለው የሥጋዌ ምሥጢር የተፈጸመ ሲኾን፡ መድረሻው ደግሞ፡ "በሰማይም ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ! የኪዳኑም ታቦት፡ በመቅደሱ ታየ!" በሚለው በዮሐንስ ራእይ ተረጋግጦ እንደተነገረው፡ በሙሴ አማካይነት ለእሥራኤል ተሰጥታ ቆይታ፡ ወደኢትዮጵያውያን ተዛውራና በአደራ ተጠብቃ የኖረችው ታቦተ ጽዮን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት፡ ወደሰማያት ተመልሳ[፻፷] በምትገኝበት ምሥጢራዊ እውነታ የተገለጠ በመኾኑ ይታወቃል::

# ምዕራፍ ፮፤ በዓል።
## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት።
## በዓለ ፍልሰታ ለማርያም።

---

በዚህ ረገድ፡ በዚህ ውይይታችንና በቀደመውም የተብራራውን በማስታወስ፡ ቍም ነገሩን፡ በጥቂት ቃል ሳጠቃልልላችሁ ይቻላል፡ ይኸውም፡-

በቅድሚያ፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢርና ጥበብ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ላይ ዐርፎ የተፀነሰው፡ ያው፡ በጽላቷ ላይ ተቀርጾ የነበረው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፡

ቀጥሎ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የኾነችው፡ ጽላተ ኪዳንና የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው፡ የጽላቷ ማደሪያ ታቦት (ማጥን)፡ ኹለቱም፡ በምድር ላይ ከነበሩበት ግዙፍ ህልውናቸው ተሠውረው፡ በሰውነት መገለጻቸውን፡

በመጨረሻም፡ በሕይወተ ሥጋ ኖረው፡ ተልእኳቸውንም ፈጽመው፡ በአዲሱ ኪዳን የትንሣኤ አካል፡ ከሙታን ተለይተው ከተነሡ በኋላ፡ በዚያ ሕያው አካላቸው፡ ወደሰማይ ዐርገው፡ ዛሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በሰማይና በምድር በሰፈነችው በዘለዓለማዊቷ መንግሥታቸው ነግሠውና በሰማያዊው ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መኾናቸው ነው።

የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰቷ፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ!" ማለትም፡ "እንደልጇዋ ትንሣኤ ነው፡ *ስለዚህ፡ እንደልጇ ትንሣኤ በዓል አድርገው ያክብሩት!*" ሲሉ፡ አባቶቻችን በደነገጉት ውሳኔ መሠረት፡ የፍልሰታዋ በዓል፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እንደልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ በታላቅ ሓሤትና ይባቤ ይከበራል። እነርሱም፡ በዚህ በዓላቸው ላይ፡ የሚሰማቸው ደስታ፡ በቃላት ሊገለጽ የማይቻለውን፡ በልጇ ትንሣኤ በዓል ጊዜ የሚሰማቸውን ይመስላል። ይህ የተመሰጠ ስሜታቸው ከሚገለጽባቸው የማኅሌትና የመዝሙር በረከቶቻቸው መካከል፡ ትርጉሙ፡ "የሰማይና የምድር ንግሥት የኾነችው የድንግል ማርያም ትንሣኤና ዕርገቷ፡ እንደልዑል አምላክ ልጇ ትንሣኤና ዕርገት፡ እውን ኾኖ ተፈጸመ!" የሚል የኾነው፡ "*ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! ተፈጸመ ትንሣኤሃ፡ ተፈጸመ ትንሣኤሃ ወዕርገታ ዘልዑል!*" የሚለው ዝማሬ ይገኛል።

የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ከኾነው፡ ከመስከረም ፩ ቀን የልደት በዓል በፊት፡ የዓመቱ የመጨረሻ ታላቅ በዓል ኾኖ የሚከበረው፡ ይህ፡ በዓለ ፍልሰታ ለማርያም ሲኾን፡ እርሱም፡ ከነሐሴ ፩ እስከ፲፮ ቀን ድረስ በሚቆየውና ካህናት፡ ትላልቆች ወንዶችና ሴቶች፡ ጨቅላ ልጆችና ብላቴኖች ብቻ ሳይኾኑ፡ ሕፃናት ጭምር እየጾሙ፡ እያስቀደሱና እየቆረቡ፡ በቤተ ክርስቲያን በሚያሳልፉት፡ የኹለት ሳምንት ሱባዔ ፍጻሜ ላይ ይውላል።

በክረምት ዝናምና በመንፈሳዊ ትጋህ ሲካኼድ የሚቆየው ይህ ሱባዔ በሚፈጸምበት፡ በነሐሴ ፲፮ቱ ቀን ዕለተ በዓል፡ የእናታችንና የንግሥታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ዜና ልደቷ፡ ሕይወቷና ዕረፍቷ፡ እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ እርሷን ምክንያት አድርጎ፡ ራሱን፡ ለፍጥረቱ የገለጸበትና ፍጥረቱን ያዳነበት፡ የሥጋዌው ምሥጢር ተብራርቶ ይነገርበታል። ቅዱሳን ሓዋርያት፡ ይህን ሱባዔ፡ ለምን እንደጀመሩት፡ በዓመቱም እንዴት እንደቀጠሉት፡ ዝክረ ነገሩ ይወሳል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

### የፍልሰታ በዓል ስማያዊ ልዕልና፡፡

**ጥያቄ፡-** *የ ዝክረ ነገር ምን እንደኾነ፡ ምናልባት ካለፈው ውይይታችን የቀረ እንዳለ፡ እዚህ ላይ፡ ያንን ጭምር አካትተህ ብትጨርስልን?*

**መልስ፡-** የ ዝክረ ነገር፡ በጥር ፳፩ ቀን ከኾነው ከቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት በኋላ ተያይዞ የሚነገረው ዜናዋ ነው፡፡ ይኸው፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን የሚነገረው ዜናዋ፡ አያሌ ድንቆችን የያዘ ሲኾን፡ ዋና ዋናዎቹን፡ ከዚህ ቀጥዬ፡ ባጭሩ አቀርብላችኋለሁ፡፡

እነዚህም፡-

-በጥር ፳፩ ቀን ከኾነው ከድንግል ማርያም ዕረፍት በኋላ፡ አይሁድ በተለመደ ጠላትነታቸው፡ አስከሬኗን፡ "እናቃጥላለን!" ማለታቸው፡

-በዚያን ጊዜ ግን፡ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ኾኖ የተፀነሰበት፡ እስኪወለድ የኖረበትና ጠብቶ፡ በእቅፏ ያደገበት መቅደስ ሥጋዋ፡ እንደታቦተ ጽዮን፡ ሰብአዊ ፍጡር ሊነካው የማይቻለው ስለኾነ፡ በቅዱሳን መላእክት ተነጥቆ፡ ወደገነት መወሰዱ፡

-ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ ይህንኑ ምሥጢር ያየ ሲኾን፡ ሌሎቹ ሐዋርያት ባለማየታቸው፡ በነሐሴ ፩ ቀን ሱባዔ መግባታቸውና ምሥጢሩ ተገልጦላቸው፡ ቅዱስ ሥጋዋን፡ እንደገና ተቀብለው፡ በነሐሴ ፲፬ ቀን መቅበራቸው፡

-በሦስተኛውም ቀን፡ የልጇ ትንሣኤ ባስገኘው፡ በአዲሱ የትንሣኤ አካል፡ እንደእርሱ፡ ከሙታን ተለይታ መነሣቷና በ፫ኛው ቀን ማረጓ፡

-ልጇ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለትንሣኤና ለዕርገት በኵርና ቀዳማዊ ኾኖ፡ እርሷ፡ ለዚያ፡ ለትንሣኤውና ለዕርገቱ ብኵርናና ቀዳሚነት፡ ዳግማዊትና ተከታይ ለመኾን የበቃችበትን፡ ያን የመለኮት ድንቅ ሥራ፡ እርሷም፡ ያገኘችውን ክብር፡ በዚያን ጊዜ፡ ቀዳሚ ኾኖ ለማየትና ምስክር ለመኾን፡ ከሐዋርያት መካከል የታደለው፡ ለጊዜው፡ ሐዋርያው ቶማስ ብቻ ስለነበረ፡ ከዚህ የተነሣ፡ "እርሱ (ቶማስ)፡ ትንሣኤሽንና ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ለዚህ ዕድል፡ እንዴት ሳንበቃ እንቀራለን?" በማለት፡ ሐዋርያት አዝነው፡ በዓመቱ፡ ኹሉም፡ ቶማስ ጭምር፡ በነሐሴ ፩ ቀን፡ ለኹለተኛ ጊዜ ሱባዔ መግባታቸው፡

# ምዕራፍ ፯፣ በዓል።

## ዓበይትና ንዑሳን በዓላት። በዓለ ፍልሰታ ለማርያም።

### የፍልሰታ በዓል ሰማያዊ ልዕልና።

---

-በመጨረሻ፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን በሚውለው በትንሣኤዋ መታሰቢያ ዕለት፡ ሐዋርያት፡ ወደሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና ማየታቸው፡

-እዚያም፡ በመንበረ ጸባዖት፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሷን፡ እናቱን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ መንበር፡ ራሱን፡ ሠራዒ ቄስ፡ ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስን፡ ረዳት ካህን፡ ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፡ እርሱ ራሱ ተቀብሎ፡ እናቱን ማቀበሉ፡ እነርሱን፡ ሐዋርያትንም ማቊረቡ ናቸው።

እግዚአብሔር፡ በድንግል ማርያም ሰውነት የፈጸማቸው፡ እነኚህ ድንቅ ሥራዎቹ፡ ቀደም ብለው፡ በሱባዔው ዕለታት፡ በየአርእስቱ ተከፋፍለውና በዝርዝር ተተንትነው የሚነገሩ ከመኾናቸው ጋር፡ በተለይ በዚች በዓል ላይ ተጠቃልለው ይወሳሉ።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ዛሬ፡ በየዓመቱ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን፡ በያለንበት በምናከብረው፡ የፍልሰታ ለማርያም በዓላችን ላይ፡ የምንፈጽመው ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ዮሐንስ፡ በራእዩ ያየውን፡ ያንን ሥርዓተ ሰማይ፡ በምድርም ላይ እውን አድርገን፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰማያዊት መቅደሱ፡ ቅድስት ንግሥት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን ታቦት፡ መንበር አድርጎ፡ ቀድሶ፡ ሐዋርያትን እንዳቆረበ፡ እንዲሁ፡ እኛም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ ዕለቲቱን በማዘከር፡ መንፈሳዊት በኾነችው፡ ምድራዊት መቅደሱ፡ ያንኑ ሰማያዊ ሥርዓት፡ መልሰን መፈጸማችን መኾኑን ማመን ይገባናል።

በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የእመቤታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የእናትነቷና የንግሥትነቷ፡ የአገርነቷም ፍቅር፡ የቱን ያህል የጠለቀና የመጠቀ መኾኑ፡ በተለይ፡ በእነዚህ፡ ኹለት የፍልሰታ ሱባዔ ሳምንታት፡ ካህናቱና ምእመናኑ፡ ማለትም፡ ትልልቆቹ ወንዶችና ሴቶች ብቻ ሳይኾኑ፡ ወጣቶቹና ሕፃናቱ ጭምር፡ በሚፈጽሙት ሃይማኖታዊ ምግባር፡ በይፋ ተረጋግጦ ይታወቃል።

ስለዚህ፡ ቅዱሳን ሐዋርያት፡ ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ባላቸው ፍቅር፡ በጾም፡ በጸሎትና በምጽዋት ተጠምደው፡ ኹለት ጊዜያት ያካኼዱትን፡ የኹለት ሳምንታት ሱባዔ፡ እኛም ኢትዮጵያውያን፡ ሕፃናቱ ሳይቀሩ፡ ስለእርሷ ባለን ፍጹም ፍቅር፡ በዚሁ መልክ፡ በሱባዔ ተወስነን ከቆየን በኋላ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን የሚውለውን፡ የትንሣኤና የዕርገት በዓሏን፡ ልክ እንደልጇ ትንሣኤና ዕርገት አድርገን፡ በታላቅ ሐሤትና ይባቤ እናከብረዋለን።

በዚያ በዓላቸውም ላይ፡ *"ተንሥአት እሙታን፡ ማርያም ድንግል! ከመ ትንሣኤ ወልዳ ዘልዑል!"* ማለትም፡ "ድንግል ማርያም፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች! ይኸውም፡ ልዑል አምላክ ልጇ እንደተነሣው ትንሣኤ ነው!" የሚለውን የምሥራች ቃል፡ እንለዋወጣለን። ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ እንደልጇ ዘመነ ትንሣኤ፡ እስከነሐሴ ፳፩ ቀን ድረስ ይቀጥላል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እግዚአብሔር፡ ለሰብአዊ ፍጡሩ ዐቅዶ ያዘጋጀው የቸርነት ሥራው፡ ለመጨረሻው ዘውድ የበቃ መኾኑ፡ በእርሷ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም የተረጋገጠበት፡ የዚህ ሰውብ ድንቅ ተአምሩ ዜና፡ ቀደም ብሎ፡ በየአግባቡ ቦታ፡ ስለ ፍልሰታ ጾምና "እስተርእዮ ማርያም" ስለሚባለው፡ ጥር ፳፩ ቀን ስለሚውለው፡ የሰረፍቷ በዓል፡ በተሰጠው ሐተታ ውስጥ፡ በሚበቃ መነገሩ ይታወሳል።

\+ + +

# ምዕራፍ ፯::

## መንፈስ - ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ - ቤተ ክህነት::

*ጥያቄ:- "ፈጣሪዬ!" የምለው: እግዚአብሔር ማነው?" ለሚለው: ለዚህ: ለተነሣንበት: መሠረታዊ ጥያቄ: በትርጓሜና በሐተታ እያስደገፍህ በሰጠኸን ዝርዝር መልሶችህ ረክተናል:: በዚህ ረገድ: እስካኹን ላገኘነው: ለነፍሳችንና ለሥጋችን: ለመንፈሳችንም እውቀት: ማጠናከሪያ የሚኾነንን ማጠቃለያ አሳብህን: እንደተለመደው ትለግሠን ዘንድ እንድንጠይቅህ ትፈቅድልናለህ?*

መልስ:- ለዚህማ: ያዟል እንጂ: ምን ፈቃድ ይጠየቃል? አይጠየቅም:: አዎን! ላለፈው: ለመጀመሪያው ውይይታችን: ርእስ ያደረግነው ታላቅ ቁም ነገር: "'እኔ' የምለው እኔነቴ ማነው?" የሚለውን እንደነበረ ታስታውሳላችሁ:: በእያንዳንዳችን ዘንድ: መልስ ሊሰጠው አስፈላጊና ተገቢ ለኾነው: ለዚያ: ዓቢይ ጥያቄ: በተሰጠው መልስ ውስጥ: የራስን ማንነት በማወቅ: የዚያ ማንነት አስገኚ የኾነውንም ፈጣሪ ማወቅ እንደሚቻል የሚያስረዳውን እውነታ: እንዴት እንዳረጋገጥነው: የቅርብ ጊዜ ትዝታችሁ ነው::

"'ፈጣሪዬ!' የምለው: እግዚአብሔር ማነው?" ለሚለው: ለዚህ: ለኹለተኛው የውይይታችን ርእስ: ምላሽ ይኾን ዘንድ: አኹን የደረስንበት የእውቀት ግብ: በዚህ ረገድ: ቀደም ብላችሁ አግኝታችሁት የነበረውን: ያን እውቀት: ፍጹም የተጠናቀቀና የተሟላ እንዳደረገላችሁ አምናለሁ::

ከዚህ: ከፍጹሙ የእውቀት ግብ ሊያደርሰን የቻለው: ሃይማኖታችን መኾኑንም: ይኸው: እየራሳችሁ ተገንዝባችሁት! በይበልጥ: በሃይማኖታችን አማካይነት: እግዚአብሔርን ለማወቅ ደግሞ: አስቀድመን: ስለዚሁ ሃይማኖታችን: ማወቅ እንደተገባን አስተውላችሁታል::

እንዲህ አድርገን: ስለሃይማኖታችን: በሚበቃ በመጠየቃችን: እነሆ: *"የጥበብ መጀመሪያ: እግዚአብሔርን ማወቅ ነው!"* የሚያሰኘውን: ፍጹሙን እውቀት አገኛችሁ! ከዚህ የተነሣም: በዚህ ሃይማኖታችን አማካይነት: እያንዳንዳችን: በተፈጥሮ ኀሊናችን: ለየራሳችን ሳይቀር: ለምናቀርበው ጥያቄ: መልስ በማግኘት: ፈጣሪያችሁን: እግዚአብሔርን ስላወቃችሁት: እጅግ ደስ ይበላችሁ!

ይህ እውቀታችሁ: እሙን የሚኾነው: በሥጋዊው ብቻ ሳይኾን፥ ከዚያ ይልቅ በሚበልጠው: በመንፈሳዊው አእምሮአችሁ: በየራሳችሁ ፍጹም ፍላጎትና ፈቃድ ስትቀበሉት ነው:: ነፍሳችንንና ሥጋችንን አንድ አድርጎ: እግዚአብሔርን በእውነት እንድናውቀውና እንድናመልከው የሚያስችለን: ይኸው መንፈሳዊ አእምሮአችን ደግሞ: በክርስትና ጥምቀታችን ጊዜ: ከእግዚአብሔር በተወለድንበት የልጅነት ጸጋ፥ እንደሥጋዊው አካልና ባሕርይ: በረቂቅ መልክ የምንለብሰው መኾኑን: "'እኔ' የምለው: እኔነቴ ማነው?" በሚለው: በመጀመሪያው ሰፊ ውይይታችን ጊዜ: በሚበቃ ተረድታችሁታል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ለቸሩ ፈጣሪያችን ክብር ምስጋና ይድረሰውና፡ ለዚህ ኹሉ ጸጋ ልንበቃ የቻልነው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ሰውነት ተወልዶ፡ በመሥዋዕትነቱና በቤዛነቱ ባስገኘው የምሕረት ቃል ኪዳን ነው፤ ያም፡ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ በዚህ ዓለም፡ ለምናሳልፈው የሥጋ ኑሮአችን፡ የመጀመሪያውን የመንፈስ ትንሣኤ፥ በሚመጣውም ዓለም፡ ለምንቀጥለው የዘለዓለም ሕይወት፡ የመጨረሻውን የትንሣኤ አካል እንድንቀዳጅ ባበቃን፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ መኾኑንም፡ በዚያ ውይይታችን፡ በሚበቃ አውቃችሁታል።

ይህን ኹሉ ጸጋ፡ የሰው ልጆች አውቀውትና አምነውበት ይቀበሉት፥ ይጠቀሙበትም ዘንድ፡ እንድታስተምራቸው፡ አክብረውና ጠብቀውትም ይኖሩ ዘንድ እንድታጸናቸው፡ ኃላፊነቱንና አደራውን የተቀበለችው፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ መንፈሳዊቷ ዘርፍ የኾነችው ቤተ ክህነት ናት።

እንዲህ ባለ መልክ፡ በሃይማኖት ያወቅነውን እግዚአብሔርን፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኳችን አማካይነት፡ በቀጥታ እየተገናኘነው የምናነጋግረው፡ በጸሎት መኾኑን፡ እርሱ ላደረገልን ቸርነቱ፡ ለሰጠንም ጸጋ፡ ባለውለታዎቹ መኾናችንን በመግለጽ፡ ምስጋናችንን የምናቀርብለት፡ ደስታችንንም የምንፈጽመው፡ በበዓሎቻችን መኾኑን፡ ጸሎትና በዓላት ደግሞ፡ እየራሳቸው፡ ምን እንደኾኑ፡ እነዚህን የመሰሉትንና አግባብነት ያላቸውን ቍም ነገሮች ኹሉ አያይዘን በመጠቃቀስ፡ በዚሁ፡ ባለንበት የውይይት መድረክ ላይ፡ በሚበቃ ተነጋግረንባቸው፡ እነሆ፡ በውጤቱ መርካታችሁን እመለከታለሁ።

እንግዴህ፡ በሰማይና በምድር ሰፍና ለምትኖረው፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሕያዋን መገለጫዎች የኾኑትን፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊዉን ለማስገኘት፡ "መንፈስ"፡ ከነፍስና ከሥጋ ጋር፥ "ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ"ም፡ ከኪዳነ ልቦናና ከኪዳነ አሪት ጋር፥ እንዲሁም፡ "ቤተ ክህነት"፡ ከቤተ ሕዝቡና ከቤተ ምልክናው ጋር፡ ባለሲሦ ተሳታፊዎች መኾናቸው፡ "ፈጣሪዬ!" የምለው፡ እግዚአብሔር ማነው?" በሚለው፡ በዚህ፡ በኹለተኛው ሰፊ ውይይታችን ውስጥ፡ ይኸው፡ በሚበቃ ተገልጾ ቀርቦላችኋል።

ይህም፡ የኾነው፡ "'እኔ' የምለው፡ እኔነቴ ማነው?" ከሚለው፡ ከመጀመሪያው ሰፊ ውይይታችን ጋር፡ በሚቻል መጠን፡ አስፈላጊውና ተገቢው ማብራሪያ፡ ማሚያ ኾኖ እንዲታከልበት በመደረጉ መኾኑን፡ እናንተም፡ በማስተዋል እንደተመለከታችሁት አምናለሁ።

ከዚህ የሚቀረው ኹሉ፤ በተለይም፡ ስለቤተ ምልክናው፡ "'ባልንጀራዬ' የምለው ፍጡር ማነው?" በሚለው፡ በሚቀጥለው፡ በሦስተኛው ሰፊ ውይይታችን ላይ፡ ተስፋፍቶና ተሟልቶ እንደሚቀርብ አረጋግጥላችኋለሁ።

\+ + +

---

## ጊዜያዊ መሰናበቻ

“ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው? የሚለው፡ የዚህ ውይይት፡ ኹለተኛው ክፍል፡ በዚህ አበቃ።

ይኸው ውይይት፡ “‘ባልንጀራዬ’ የምለው ፍጡር ማነው?” በሚለው፡ በሦስተኛው ክፍል፡ በዚሁ መልኩ እንዲቀጥል፡ ከአዳምና ሔዋን ጋር ተስማምተን፡ ከዚህ ያደረሰን ቸሩ እግዚአብሔር፡ ለሚቀጥለው ቀጠሮአችንም እንዲያበቃን፡ እንጸለፈው ጊዜ አብረን ጸልየን፡ በተለመደው አሸኛኘት፡ በፍቅር ተሳስመን፡ ተለያየን።

\+ \+ \+

## ክፍል ሦስት፤

## “ባልንጀራዬ” የምለው ፍጡር ማነው?

በሚል አርእስት የተዘጋጀው፡ የመጨረሻው፡

ሦስተኛው መጽሐፍ፡

በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት፡

ከዚህ ቀጥሎ ታትሞ ይወጣል።

## የክፍል ኹለት፡

### ጥቅሶችና ማብራሪያዎች።

፩ "ጉያ"፡ በኢትዮጵያኛ፡ "የውስጥ ዕቅፍ"፡ በግእዝ ደግሞ፡ "ሰደት" ማለት ነው፡ ይህ መጽሐፍ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፡ በፈተናና በመከራ፡ እየተሰደደና እየተንገላታ፡ እየታገለም ላለ ሰው፡ ሲቀመጥ፡ ከእጁ፡ ሲጓዝ፡ ከጉያው፡ ሲተኛ፡ ከራስጌው የማይለየው፡ ጓዱ ስለኾነ፡ "የጉያ መጽሐፍ" ተብሏል።

፪ "ኢትዮጵያዊ" እና/ወይም "ኢትዮጵያውያን" ተብሎ፡ በዚህ መጽሐፍና በሌሎቹም ድርሰቶቼ ውስጥ፡ በወንድ አንቀጽ የተጻፈው ኹሉ፡ በነጠላና በብዙ፡ የሴትንም ያጠቃልላል። ይህም የኾነው፡ *"እግዚአብሔርም፡ ሰውን፡ በመልኩ ፈጠረ፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው!"* የሚለውን የመጽሐፍ ቃል በመከተል ነው። ዘፍጥ. ፩፡ ፳፯። ኤር. ፲፫፡ ፳፫።

፫ ዮሐ. ፲፯፡ ፳፩ ፳፪።

፬ ዘፍጥ. ፱፡ ፰ ፲፯።

፭ መዝ. ፷፯፡ ፴፩፡

፮ ዘፍጥ. ፲፱፡ ፲፯ ፳። መዝ. ፻፱፡ ፬። ራእ. ፭፡ ፭።

፯ ማር. ፲፪፡ ፴።

፰ ዘፍጥ. ፩፡ ፩-፴፩። ሮሜ ፰፡ ፳፰።

፱ ማቴ. ፭፡ ፫።

፲ ዘጸአ. ፳፡ ፩-፲፪።

፲፩ ፩ቆሮ. ፪፡ ፲፬-፲፮።

፲፪ ሐዋ. ፲፬፡ ፲፭-፲፯። ሉቃ. ፲፭፡ ፩-፴፪።

፲፫ እግዚአብሔር፡ በኤር. ፴፩፡ ፴፩-፴፬፡ በዮሐ. ፮፡ ፵፭፡ በዕብ. ፰፡ ፰-፲፪፡ በ፩ቆሮ. ፫፡ ፲፮-፲፯፡ በ፪ቆሮ. ፮፡ ፲፮፡ በገላ. ፩፡ ፲፩-፲፪ እንዳናገረውና እንዳጻፈው፡ እንደ ቃል ኪዳኑ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ልቦና ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ ከመዘገበው።

፲፬ ከመጽሐፈ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘሐዋርያት ።

፲፭ ከመጽሐፈ ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምዕት።

፲፮ የግራኝ አሕመድ ወረራ -ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ ፲፱፻፳፮ ዓ. ም.፡ ገጽ ፯፻፹፭-፯፻፹፮።

፲፯ ማቴ.፳፮፡ ፳፮-፳፱።

፲፰ መዝ. ፻፲፯ (፻፲፰)፡ ፳፪።

፲፱ ፩ቆሮ. ፮፡ ፲፱፡ ገላ. ፭፡ ፮።

፳ ሮሜ. ፲፬፡ ፫-፳፡ ማቴ. ፲፭፡ ፲፮-፲፰።

---

፹፩ ቅዳሴያተ ማርያም: ጐሥዓ - መዓዛ ቅዳሴ:: በንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገ/ማርያምና በም/አፈ ንጉሥ ጥበቡ በየነ: በኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ማተሚያ ቤት: በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. በአሥመራ ከተማ: እንዲሁም: በቀኛዝማች ተስፉ ገብረ ሥላሴና በም/አፈ ንጉሥ ጥበቡ በየነና: በተስፉ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት: በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. አዲስ አበባ የታተመ::

፹፪ ኤር. ፴፩: ፴፩-፴፬::

፹፫ ፪ቆሮ. ፫: ፪-፮::

፹፬ የሐዋ. ፭: ፴፫-፴፱::

፹፭ መዝ. ፷፯: ፴፩: ፸፩: ፱: ፸፫: ፲፪-፲፬::

፹፮ ዕብ. ፲፩: ፳፬-፳፯::

፹፯ ራእ. ፭: ፭:: ፩ኛ ዜና. ፲፯: ፲፩-፲፬::

፹፰ ዘፍ. ፵፱: ፰-፲፪:: ራእ. ፭: ፭::

፹፱ አሞ. ፱: ፯::

፺ ጸሎተ ኪዳን: ከሠርኩ ክፍል: የመጨረሻው::
“ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት -አንደኛ መጽሐፍ”: በን.እ. ኤርምያስ ከበደ ወ/ኢየሱስ: ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.: ገጽ ፹፪-፹፭: “ጴጥሮስ! ያቺን ሰዓት!” የጸጋዬ ገብረ መድኅን ተውኔት::

፺፩ ፩ዮሐ. ፬: ፩-፫::

፺፪ ኤር. ፴፩: ፴፩-፴፬:: ዮሐ. ፮: ፶፮:: ማቴ. ፮: ፴፫: ፳፫: ፮-፯::

፺፫ ዘጸ. ፬: ፳፩-፳፮::

፺፬ ዘጸ. ፲፱: ፮::

፺፭ ማቴ. ፲፬: ፲፩-፴፪::

፺፮ “ደቂቀ እስጢፋኖስ”: ትርጉም: በጌታቸው ኃይሌ: ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. ገጽ ፪፻፹፯ የግርጌ ማስታወሻ ቍጥር ፴::

፺፯ መዝ. ፷፯: ፸፩- ፸፫:: አሞ. ፱: ፯:: ሉቃ. ፲፬: ፲፩-፴፪::

፺፰ ዘፍጥ. ፭: ፩-፴፪: ፲፩: ፩-፴፪::

፺፱ ፩ሳሙ. ፫: ፱-፳፪::

፻ “ኢትዮጵያ: የዓለሙ መፋረጃ!” በን.እ. ኤርምያስ ከበደ ወ/ኢየሱስ: ፲፱፻፺፰ ዓ. ም.: ገጽ ፩፻፴፯-፩፻፴፰::

፻፩ የዛሬውን የግብፅን: ብሔራዊና መንግሥታዊ ሰንደቅ ዓላማ ይመለከቷል::

፻፪ መዝ. ፴፫ (፴፩): ፯-፰::

፻፫ የ፳ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ: ፩ኛ መጽሐፍ: ከጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ: ገጽ ፹-፹፬ እና ፺፯::

፻፬ ዘፍጥ. ፩: ፳፯::

፻፭ ዘፍጥ. ፲፩: ፯-፰::

፻፮ መዝ. ፴፪(፴፫): ፭-፮::

፻፯ ኢሳ. ፮: ፫::

፹፰ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት -አንደኛ መጽሐፍ"፡ በን.እ. ኤርምያስ ከበደ ወ/ኢየሱስ፡ ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.፡ ገጽ፡ ፻፹፱- ፩፻፴፡፡

፹፱ ዮሐ. ፲፡ ፴፡ ፲፬፡ ፳፯፡፡

፺ ዘፍ. ፩፡ ፳፯፡፡ መዝ. ፴፫፡ ፲፫ ፲፯፡፡ ኢሳ. ፳፯፡ ፩፡፡

፺፩ ዘጸአ. ፴፫፡ ፲፯-፳፫፡ ዮሐ. ፲፬፡ ፰ ፲፩፡፡

፺፪ ዮሐ. ፲፰፡ ፴፯፡፡

፺፫ አቡሻክር -የቀን መቍጠሪያ፡ ሓምሌ ፴ ቀን፡ ፲፱፻፸፪ ዓ. ም. አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም፡ ቀ. ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት፡ ገጽ ፲፬፡፡

፺፬ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በን.እ. ኤርምያስ ከበደ ወ/ኢየሱስ፡ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.፡ ገጽ ፩፻፴፫ ፩፻፵፡፡

፺፭ ዮሐ. ፩፡ ፩ እና ፲፬፡፡

፺፮ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በን.እ. ኤርምያስ ከበደ ወ/ኢየሱስ፡ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.፡ ገጽ ፩፻፳፯-፩፻፳፱፡፡

፺፯ ሮሜ ፫፡ ፲፡ ፩ኛ ዮሐ. ፫፡ ፩፡፡

፺፰ ዮሐ. ፫፡ ፯፡፡

፺፱ ማቴ. ፫፡ ፲፫-፲፯፡፡ ዮሐ. ፩፡ ፳፱-፴፬፡፡

፻ ቈላ. ፪፡ ፲፬-፲፭፡፡

፻፩ ዮሐ. ፩፡ ፲፪-፲፫፡፡

፻፪ ዘፍ. ፫፡ ፯-፲፪፡፡

፻፫ ዘፍጥ. ፩፡ ፪፡፡

፻፬ ዮሐ. ፫፡ ፩-፲፪፡፡

፻፭ ማር. ፲፮፡ ፲፭-፲፮፡፡

፻፮ ማቴ. ፳፰፡ ፲፱-፳፡ የሐዋ. ፩፡ ፰፡፡

፻፯ ማቴ. ፲፡ ፩-፯፡ ፲፩፡ ፳፱፡፡

፻፰ ማቴ. ፲፫፡ ፫፡ ማር. ፲፡ ፲፫ ፲፯፡፡

፻፱ ዘሌዋ. ፲፪፡ ሉቃ. ፪፡ ፳፩-፳፬፡፡

፻፲ ዮሐ. ፲፱፡ ፴፩-፴፯፡ ፩ኛ ዮሐ. ፭፡ ፯-፰፡፡

፻፲፩ ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፡ ዮሐ. ፫፡ ፫-፯፡፡

፻፲፪ ዘፍጥ. ፲፯፡ ፱-፲፬፡ ዘሌዋ. ፲፪፡ ዮሐ. ፫፡ ፩-፲፪፡፡

፻፲፫ ማቴ. ፳፮፡ ፳፮-፳፱፡፡

፻፲፬ ዮሐ. ፬፡ ፳፩-፳፬፡፡

፻፲፭ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በን.እ. ኤርምያስ ከበደ.ወ/ኢየሱስ፡ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.፡ ገጽ ፻፯-፩፻፫፡፡

፻፲፮ ዮሐ. ፬፡ ፲፫፡ ፰፡ ፳፬-፳፱፡ ፯፡ ፴፰-፵፫፡፡

፻፲፯ ዮሐ. ፯፡ ፫፡

፻፲፰ ፩ቆሮ. ፪፡ ፲፬-፲፯፡፡

፻፲፱ ማቴ. ፳፮፡ ፳፮-፳፱፡

፻፳ ዮሐ. ፮፡ ፳፱፡፡

፻፳፩ ሥርዓተ ቅዳሴ፡ መግቢያው፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?
### የክፍል ኹለት፡ ጥቅሶችና ማብራሪያዎች።

---

፹፪ ቅዳሴ ሐዋርያት፡ የቅዱስ ቁርባኑ ዝግጅት ጸሎት።
፹፫ ሉቃ. ፲፯ ፡ ፳-፳፩።
፹፬ ሮሜ ፯ ፡ ፳፪-፳፭።
፹፭ ማቴ. ፱ ፡ ፲፪-፲፫፡ ሉቃ. ፲፭፡ ፯-፲።
፹፮ ዮሐ. ፲፡ ፯-፲፫።
፹፯ የሐዋ. ፪፡ ፳፪-፳፬፡ ፭፡ ፳፯-፴፪።
፹፰ ማቴ. ፳፪፡ ፵፩-፵፮።
፹፱ ማቴ. ፳፫፡ ፩-፴፱።
፺ ዮሐ. ፰፡ ፳፱። የሐዋ. ፯፡ ፵፰-፶፡ ፰፡ ፳፮-፴፰።
፺፩ ማቴ. ፰፡ ፪-፬።
፺፪ ዘሌዋ. ምዕ. ፲፪-፲፭።
፺፫ ማቴ. ፲፮፡ ፲፫-፳፡ ፲፰፡ ፩-፲፰። ዮሐ. ፳፡ ፳፩-፳፫።
፺፬ መዝ. ፯፡ ፷፭-፷፮፡ ማቴ. ፲፪፡ ፵፡ ፳፡ ፲፰-፲፱፡ ሉቃ. ፳፬፡ ፴፮-፵፫፡
ዮሐ. ፲፡ ፲፯-፲፰፡ ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፡ ፬።
፺፭ ሕዝ. ፫፡ ፲፮-፲፱።
፺፮ ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፡ ፳-፳፫።
፺፯ ሉቃ. ፳፫፡ ፵፬-፶፮፡ ፳፬፡ ፩-፱፡ ፲፫-፶፫፡ ዮሐ. ፳፡ ፫- ፲፰፡ ፳፬-፳፱።
፺፰ ዮሐ. ፲፩፡ ፩-፵፭፡ ፲፪፡ ፱-፲፩።
፺፱ ማቴ. ፰፡ ፳፩-፳፪፡ ሉቃ. ፱፡ ፶፱-፷።
፻ ዮሐ. ፭፡ ፳፰- ፳፱፡ ማቴ. ፳፪፡ ፳፫-፴፪።
፻፩ ማቴ. ፲፫፡ ፳፬-፵፫፡ ፳፬፡ ፳፱-፴፩።
፻፪ ዮሐ. ፲፪፡ ፳፬። ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፡ ፴፭-፵፱።
፻፫ ዮሐ. ፭፡ ፳፬-፳፱፡ ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፩-፶፬ ፡ ፩ኛ ተሰ. ፬፡ ፲፫-፲፰።
፻፬ ራእ. ፳፡ ፩-፲።
፻፭ ዘፍጥ. ፪፡ ፯፡ ፫
፻፮ ራእ. ፳፩፡ ፫-፬።
፻፯ መዝ. ፫፡ ፭-፮፡ ፳፯፡ ፲፰። ዮሐ. ፲፩፡ ፩-፵፬። የሐዋ. ፩፡ ፩-፲፩።
፻፰ ሉቃ. ፮፡ ፳፭።
፻፱ ማቴ. ፲፫፡ ፵-፵፫። ሉቃ. ፳፡ ፳፯-፴፰። ራእ. ፳፡ ፯-፲፭፡ ፳፩፡ ፩-፰።
፻፲ መዝ. ፵፱፡ ፪-፫። ማቴ. ፳፬ እና ፳፭። ሉቃ. ፳፫፡ ፳፯-፴። ያዕ. ፪፡ ፲፱።
፻፲፩ ማቴ. ፲፮፡ ፳፮-፳፯፡ ራእ. ፳፪፡ ፯-፲፪።
፻፲፪ የሐዋ. ፩፡ ፮-፱።
፻፲፫ ማቴ. ፲፪፡ ፵፩-፵፪።
፻፲፬ ሉቃ. ፲፭፡ ፩-፲።
፻፲፭ ዮሐ. ፫፡ ፲፯-፲፰።
፻፲፮ የሐዋ. ፲፬፡ ፲፭-፲፯፡ ፲፯፡ ፳፪-፴፩። ሮሜ ፪፡ ፲፩-፲፭።
፻፲፯ ማቴ. ፳፭፡ ፴፩-፵፮፡ ማር. ፲፩፡ ፳፭-፳፮፡ ሮሜ ፲፪፡ ፲፱-፳፩።
፻፲፰ ዮሐ. ፬፡ ፳፫-፳፬።
፻፲፱ ማር. ፲፫፡ ፴፪-፴፯፡ ኤፌ. ፮፡ ፲-፳።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

፻፳ ማቴ. ፯፥ ፮-፯::
፻፳፩ ሉቃ. ፲፩፥ ፩-፬::
፻፳፪ መዝ. ፺፮: ፩፥ ፺፯:፩፥ ፻፵፱: ፩::
፻፳፫ ፩ዮሐ. ፫: ፩::
፻፳፬ ሉቃ. ፲፩: ፱-፲፫:: ማቴ. ፳፫: ፱-፲::
፻፳፭ ዮሐ. ፲፬: ፲፮-፲፯፥ ፳፫::
፻፳፮ ሉቃ. ፰: ፳፯-፴፱:: ፲፯፥ ፲፩-፲፱:: ዮሐ. ፲፯: ፩-፯፥ ፲፯-፲፱::
፻፳፯ ማቴ. ፫: ፩:: ማር. ፩: ፲፬-፲፮:: ዮሐ. ፲፰፥ ፴፫-፴፯::
፻፳፰ ሉቃ. ፲፯ : ፳-፳፩::
፻፳፱ ማቴ. ፲፫ : ፳፬-፶፪:: ፲፰ : ፩-፬: ፳፩-፴፮:: ፲፱: ፲፫-፳፬:: ፳: ፩-፲፯:: ፳፩: ፩-፲፯: ፴፫-፵፫:: ፳፪: ፩-፲:: ማር. ፲፩: ፱-፲:: ሉቃ. ፲፱ : ፴፯-፵:: ዮሐ. ፲፪ : ፲፪-፲፯::
፩፻፴ ማቴ. ፳፫: ፲፫፥ ፲፩: ሉቃ. ፶፪: ፲፪: ፴፪-፵::
፻፴፩ ማቴ. ፳፬: ፵፪-፶፩:: ፳፭: ፩-፵፯::
፻፴፪ ራእ. ፲፪: ፩-፲፯::
፻፴፫ ዮሐ. ፰: ፵፬-፵፯:: ፲፪: ፴፩-፴፪:: ፲፬: ፩: ፳፯-፴:: ፲፮: ፲፰-፲፱:: ፲፯: ፯-፲፩፥ ፴፫:: ፲፰: ፴፯-፴፱::
፻፴፬ ማቴ. ፳፯: ፴፱-፵፪::
፻፴፭ ማቴ. ፯: ፮-፰: ፳፮-፴፬::
፻፴፮ ሉቃ. ፲፩: ፲፫::
፻፴፯ ማቴ. ፳፯: ፵፩-፵፮:: ዮሐ. ፲፯: ፴፫::
፻፴፰ መዝ. ፰፯: ፴፩:: ራእ. ፮: ፮::
፻፴፱ ማቴ. ፳፰: ፲፰::
፩፻፵ ዮሐ. ፩፥ ፳፱: ፲፯: ፴፫:: የሐዋ. ፰: ፴፪:: ፩ቆሮ. ፩: ፳፬::
፻፵፩ ማቴ. ፳፩: ፲፮-፲፯:: ሉቃ. ፲፱: ፴፯-፵::
፻፵፪ ዮሐ. ፲፱: ፳፯::
፻፵፫ ፩ኛቆሮ. ፪: ፲፬-፲፮::
፻፵፬ የዓርብ ውዳሴ ማርያም::
፻፵፭ የቅዱስ ኤፍሬም: የረቡዕ ውዳሴ ማርያም፡ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ: የሌሊት ሰዓታት ጸሎት::
፻፵፮ ዮሐ. ፩፥ ፲፰፥ ፲፬፥ ፯-፲::
፻፵፯ ዘፍጥ. ፫፥ ፲፬-፳::
፻፵፰ ዘፍጥ. ፯፥ ፯፥ ፳፮፥ ፳፩-፳፫:: የሐዋ. ፱: ፮:: ሮሜ ፱: ፲-፲፫:: የማግሰኞና የረቡዕ ውዳሴ ማርያም::
፻፵፱ ማቴ. ፲፩፥ ፳፰-፳፱::
፻፶ ዘፍጥ. ፫፥ ፲፯፥ ዘሌዋ. ፲፪: ፩-፮::
፻፶፩ ሮሜ ፯: ፬-፯:: ገላ. ፫፥ ፲-፲፫::
፻፶፪ ሉቃ. ፩፥ ፵፯-፶፮::
፻፶፫ ዘፍጥ. ፩፥ ፳፰፥ ማቴ. ፲፱፥ ፯::
፻፶፬ ዮሐ. ፲፥ ፴፩-፴፰::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?
### የክፍል ኹለት፡ ጥቅሶችና ማብራሪያዎች::

---

፻፶፭ ማቴ. ፲፥ ፺-፺፪:: ዮሓ. ፲፬፥ ፲፪::

፻፶፮ ማቴ. ፲፪፥ ፲፩-፲፪፤ ማር. ፪፥ ፳፯፤ ፫፥ ፩-፭፤ ሉቃ. ፲፬፥ ፩-፮፤ ፲፫፥ ፲-፲፯::

፻፶፯ ዘፍጥ. ፩፥ ፲፬-፲፰::

፻፶፰ መጽሐፈ ስንክሳር፡ ከመስከረም እስከየካቲት፡ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ፡ ገጽ ፪::

፻፶፱ ማቴ. ፲፮፥ ፳፮፥ ፲፥ ፴፬-፴፱:: ሉቃ. ፲፬፥ ፳፮-፳፯::

፻፷ የሓዋ. ፯፥ ፶፭-፷::

፻፷፩ ሉቃ. ፩፥ ፲፱-፳::

፻፷፪ ዘጸ. ፳፥ ፰:: ማቴ. ፲፪፥ ፴፰-፵:::

፻፷፫ ሉቃ. ፪፥ ፰-፲፬::

፻፷፬ የሓዋ. ፲፯፥ ፳፩-፴፩:: Encyclopaedia Britannica, CD 2000 Christmas.

፻፷፭ ሉቃ. ፪፥ ፩-፰፤ ማቴ. ፪፥ ፭-፮::

፻፷፮ ዮሓ. ፲፰፥ ፲፰፤ ሉቃ. ፪፥ ፰::

፻፷፯ Encyclopaedia Britannica, CD 2000, Egyptian, Julian & Gregorian Calendar; Week; Months of the year.

፻፷፰ ራእ. ፳፥ ፩-፲::

፻፷፱ ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ! ፲፱፻፹ ዓ. ም. በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡ ገጽ ፩፻፴፬-፩፻፵::

፻፸ የተአምረ ማርያም መቅድምና መጽሐፈ ስንክሳር፡ ከመስከረም እስከየካቲት፡ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ፡ ፲፱፻፺፬ ዓ. ም.፡ ገጽ ፶፱ ::

፻፸፩ መጽሐፈ ስንክሳር፡ ከመስከረም እስከየካቲት፡ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ ፲፱፻፺፬ ዓ. ም.፡ ገጽ ፬፻፳፯ ::

፻፸፪ ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ! ፲፱፻፹ ዓ. ም.፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡ ገጽ ፩፻፴፰-፩፻፵::

፻፸፫ ማር. ፩፥ ፪-፫:: ዮሓ. ፫፥ ፳፰-፴::

፻፸፬ ዘፍጥ. ፪፥ ፰-፲፫፤ ፫፥ ፲፬-፲፭::

፻፸፭ ፪ሳሙ. ፯፥ ፲፪-፲፯፤ ማቴ. ፲፪፥ ፵፪::

፻፸፮ መዝ. ፹፯፥ ፴፩::

፻፸፯ ዘፍጥ. ፴፪፥ ፴፰፤ አሞ. ፱፥ ፯፤ ሆሴ. ፲፩፥ ፩፤ ማቴ. ፪፥ ፲፭::

፻፸፰ ዮሓ. ፯፥ ፳፪-፳፬፤ ፲፱፥ ፲፭-፳፪::

፻፸፱ ፩ነገ. ፲፥ ፩-፲፫:: መዝ. ፸፯፥ ፫-፬:: ሉቃ. ፩፥ ፭፥ ፲፫፥ ፴፯፥ ፶፱-፷፫:: የሓዋ. ፰፥ ፳፯-፴፱::

፻፹ ሉቃ. ፪፥ ፳፩::

፻፹፩ ዘፀአ. ፲፫፥ ፩-፪፤ ዘሌዋ. ፲፪፥ ፩-፰፤ ሉቃ. ፪፥ ፳፪-፴፰::

፻፹፪ ማቴ. ፲፯፥ ፳፬-፳፭፤ ፩ኛ ቆሮ. ፩፥ ፲፰-፴፩::

---

፻፹፫ *ደብረ ሥልጣን በኢየሩሳሌም፥ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ታሪክ ማስታወሻ፡* በአባ ማቴዎስ፡ ሊቀ ጳጳሳት፥ በ፲፱፻፹፰ ዓ. ም. የታተመ፥ ገጽ ፮-፯፡ ፲፮ እና ፹፬::

፻፹፬ ድርሳነ መስቀል፡ በሚጣቅ አማኑኤል ገዳም፡ በሰኔ፡ ፲፱፻፸፫ ዓ. ም. የታተመ፡ ገጽ ፶፪-፶፫፡ ፳፯-፸፪::

፻፹፭ ሉቃ. ፩፡ ፲፱፡ ፹፯፡ ፴፩-፴፰:: ኢሳ. ፯፡ ፲፬፡ ማቴ. ፩፡ ፹፪-፹፫::

፻፹፮ ከቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ::

፻፹፯ ዳን. ፫፡ ፹፬-፹፮::

፻፹፰ ፩ኛ ዮሐ. ፫፡ ፩::

፻፹፱ ፩ጴጥ.. ፫፡ ፹-፹፩:: ኢያ. ፫፡ ፩-፲፯:: ዮሐ. ፫፡ ፩-፲፮::

፻፺ ዮሐ. ፪፡ ፩-፲፩::

፻፺፩ ዘፍ. ፪፡ ፹-፹፮:: ማቴ. ፲፱፡ ፫-፮::

፻፺፪ ዘጸአ. ፴፪፡ ፯-፲፬::

፻፺፫ ማቴ. ፲፡ ፶-፶፪::

፻፺፬ ማቴ. ፱፡ ፲፬-፲፮፡ ፹፮፡ ፩-፲፫:: ዮሐ. ፫፡ ፲፬-፲፮:: መዝ. ፲፰፡ ፮-፯:: ሉቃ. ፲፰፡ ፴፩-፴፬::

፻፺፭ ዘጸ. ፲፱፡ ፹-፹፮፡ ፴፪፡ ፩-፲፮:: ዮሐ. ፫፡ ፲፫::

፻፺፮ ፩ኛ ጴጥ. ፩፡ ፲፮-፲፯፡ ፩ኛ ተሰ. ፬፡ ፯፡ መዝ. ፪፡ ፲፩-፲፪፡ ማቴ. ፮፡ ፹፬::

፻፺፯ መዝ. ፳፰፥ ፱-፲:: ዮሐ. ፪፡ ፲፫-፹፪:: ፩ቆሮ. ፫፡ ፱፡ ፲፯-፲፯፡ ፮፡ ፲፱:: ፪ቆሮ. ፮፥ ፲፮:: የሐዋ. ፯፡ ፵፰-፶፡ ፲፯፥ ፹፬-፹፮::

፻፺፰ መዝ. ፮፡ ፪-፫:: ዮሐ. ፭፡ ፩-፲፮::

፻፺፱ መዝ. ፶፱፡ ፪-፫:: ማቴ. ፹፬፡ ፩-፶፬::

፪፻ መዝ. ፵፮፡ ፵-፵፩:: ማቴ. ፹፭፡ ፩-፵::

፪፻፩ መዝ. ፲፯፡ ፫-፬:: ዮሐ. ፫፡ ፩-፹፩::

፪፻፪ መዝ. ፹፫፡ ፯-፲፡ ፳፯፡ ፵፩፡ ፸፩፡ ፱፡ ፸፫፡ ፲፪-፲፬፡ ፻፲፯፡ ፹፮-፹፯:: ማቴ. ፹፩፡ ፩-፲፯:: ማር. ፲፩፥ ፩-፲፩:: ሉቃ. ፲፱፡ ፹፰-፶፰:: ዮሐ. ፲፪፥ ፲፪-፲፮::

፪፻፫ ዘጸ. ፲፪፥ ፶፮፡ ፩-፶፩:: መዝ. ፵፫፡ ፹:: ዮሐ. ፲፱፡ ፵፩-፵፮::

፪፻፬ መዝ. ፸፮፥ ፳፭-፳፮::

፪፻፭ ዮሐ. ፰፥ ፲፮-፲፰:: የሐዋ. ፩፥ ፩-፲፬::

፪፻፮ ዘሌዋ. ፹፫፥ ፩-፶፬::

፪፻፯ ዮሐ. ፰፥ ፲፬-፹፱፡ የሐዋ. ፪፥ ፩-፲፩፡ ፳፥ ፹፮-፶::

፪፻፰ ሉቃ. ፲፩፥ ፱-፲፫::

፪፻፱ ማቴ. ፲፥ ፯-፵፱፡ ፹፰፥ ፲፰-፹:: ሉቃ. ፲፱፥ ፹፮-፹፯::


፪፻፲ ዘፍጥ. ፲፰፥ ፩-፵፫::

፪፻፲፩ ማቴ. ፲፫፥ ፲፫-፲፯:: ሉቃ. ፱፥ ፹፰-፵፮::

፪፻፲፪ ዘጸ. ፵፫፥ ፲፪-፹፫:: ማር. ፱፥ ፪-፰::

፪፻፲፫ ዮሐ. ፩፥ ፲፬:: ሉቃ. ፩፥ ፵-፵፰:: ራእ. ፲፩፥ ፲፱፡ ፲፪::

\+ + + + + + +




ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፥ ንጉሠ ጽዮን
ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest, King of Zion and
King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ወእምነ፥ ንግሥተ ጽዮን
ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

## ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት



# ኢትዮጵያ
## እና
# ኢትዮጵያዊነት



ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ



ሐምሌ ፫ ቀን፥ ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በአዲስ አበባ መካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የተወለዱት፡ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፡ ገና በትምህርት ቤት ሳሉ፡ በአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜያቸው፡ "**ምናሴ፥ የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!**"፥ በሥራ ዓለምና በደርግ፡ የእሥራትና የግዞት፥ ኋላም የስደት ዘመን ሳሉም፡ ከደረሷቸው መጻሕፍት መካከል፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"፥ Ethiopia: The Classic Case እና "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት" የተባሉትን፡ ለኅትመትና ለንባብ አብቅተዋል።

በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. የመጀመሪያውን፡ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር፡ ከጥቂት ደራስያን ጋር አቋቁመው፡ እስከ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ድረስ፡ በዋና ጸሐፊነት፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎታቸውን አበርክተዋል።

በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. በአዲስ አበባ፡ ደቡብ ሕዝብ ተመርጠው፡ የመናገሻ ከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት አባል፥ በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. የቀድሞው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል፥ በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. በንቡረ እድነት ማዕርግ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት ሙሉ ተጠሪ በመኾን፡ የአኵስም ጽዮን አስተዳዳሪ፥ በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. የቀድሞው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፥ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በቀድሞው የኢትዮጵያ ቤተ ምልክና፡ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ኾነው አገልግለዋል።

በዚያ አገልግሎት ላይ እያሉ፡ በሰኔ ፳፬ ቀን፥ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የሙት በቃ ብያኔ ወደተሰጠበትና ከሰባት ዓመታት በላይ ወደቆዩበት፡ የደርግ እሥር ቤት ገቡ። በመጨረሻ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ከዚያ ፈተናና መከራ ተርፈው፥ ከእሥርም ተፈትተው፡ ለብዙ ዓመታት፡ በአገራቸው፡ በግዞት፥ በባዕዳን አህጉር ደግሞ፡ በፈቃደኝነት የስደት ኑሮ፡ ተልእኳቸውን በመቀጠል ከቆዩ በኋላ፡ በቅርቡ፡ ወደኢትዮጵያ ለመመለስ በቅተዋል።

ከወይዘሪት ሬሔል ዘካርያስ ጋር፡ በሐምሌ ፫ ቀን፥ ፲፱፻፵፰ ዓ. ም.፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት ከፈጸሙት ጋብቻቸውና የትዳር ኑሮአቸው፡ ሦስት ወንዶችንና አምስት ሴቶች ልጆችን አፍርተዋል።

ዋጋው $ 35.00

ቲምበር ማተሚያ ቤ